የፍትሕ ሚኒስቴር
MINISTRY OF JUSTICE

# የፍትሕ ሚኒስቴር

# የ2014 በጀት ዓመት መሪ እቅድ

ሐምሌ 2013 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## ማውጫ


መግቢያ ..... 1
ክፍል አንድ ..... 2
1. የራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች ..... 2
ክፍል ሁለት ..... 3
2.የውጫዊና ውስጣዊ ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ ..... 3
2.3. የ2013 በጀት ዓመት የእቅድ አፈፃጸም የሁኔታ ግምገማ ..... 9
3. **ፍትህ ሚኒስቴር** የ2014 በጀት ዓመት እቅድ ..... 31
3.1. የእቅዱ ዋና ዓላማ ..... 31
3.2. የእቅዱ ዝርዝር ዓላማዎች ..... 31
3.4. በትግበራ ምዕራፍ የሚከናወኑ ተግባራት ..... 32
3.4.1. ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች (Strategic Themes) ..... 32
ስትራቴጂያዊ ግቦች/strategic Objectives/ ..... 33
ከተገልጋይ እይታ አንፃር ..... 34
ግብ 1 የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ፣ ..... 34
ግብ 2 የህብረተሰብ/ የሲቪል ማህበረሰብ/ ተሳትፎን ማሳደግ ..... 34
ከፋይናንስ እይታ አንፃር ..... 34
ግብ 3 የሐብት አጠቃቀም ውጤታማነት ማሻሻል ..... 34
ከዉስጥ አሰራር እይታ አንፃር ..... 35
ግብ 4 የወንጀልና የወንጀል ስጋትን መቀነስ ..... 35
ንዑስ ግብ 4.1. የወንጀል መከላከል አቅምን ማሳደግ፣ ..... 35
ንዑስ ግብ 4.2. የህገወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከል አቅምን ማሳደግ፣ ..... 36
ንዑስ ግብ 4.3፡- የወንጀል ህግ አፈፃፀም ውጤታማነት ማሳደግ፣ ..... 36
ንዑስ ግብ 4.4. በወንጀል የተገኘ ሃብት የማስመለስ ውጤታማነት ማሳደግ ..... 37
ንዑስ ግብ 4.5. የይቅርታ አመክሮ አፈፃፀም ክትትልና ውጤታማነት ማሻሻል፣ ..... 38
ግብ 5. የመንግስትና የህዝብ ጥቅምን የማስጠበቅ ውጤታማነትን ማሻሻል ..... 38
ንዑስ ግብ 5.1. የመንግስትና የህዝብ ፍትሐብሔራዊ ጥቅም ማሳደግ ..... 38
ንዑስ ግብ 5.2. በህግ እና ፍትህ ጉዳዮች አለም አቀፍ ትብብርን ማሳደግ ..... 39
ግብ 6. የሰብዓዊ መብት ማክበርና ማስከበር አፈፃፀምን ማሻሻል ..... 40
ግብ 7. የህግ ተገዥነትን ማሳደግ ..... 40
ንዑስ ግብ 7.1. የዜጎችን ንቃተ ህግ ማሳደግ፣ ..... 40
ንዑስ ግብ፡- 7.2. የፌዴራል ህጎች ተፈፃሚነት ማሳደግ፣ ..... 41

ግብ 8. የሕግ ጥናትና ማርቀቅ አፈፃፀም ማሻሻል ........ 42
ግብ 9፡ የአገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽነትን ማሳደግ ........ 42
ንዑስ ግብ 9.1.በክልሎች የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አገልግሎት ተደራሽነትን ማስፋት ........ 42
ንዑስ ግብ 9.2. የነፃ ህግ ድጋፍ አገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽነት ማሻሻል ........ 42
ግብ 10፡ የፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማሳደግ ........ 43
ንዑስ ግብ 10.1. የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀምን ማሳደግ ........ 43
ንዑስ ግብ 10.2. በፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግ ........ 44
ንዑስ ግብ 10.3. የጥብቅና አስተዳደር እና ክትትል ማሳደግ ........ 44
ንዑስ ግብ 10.4. የወንጀል ምስክሮች፣ ጠቋሚዎች፣ ተጎጂዎች አገልግሎት አሰጣጥን ........ 45
ማሳደግ ........ 45
ግብ 11፡ በአገልግሎት አሰጣጥ አካታችነትን ማሳደግ ........ 46
ግብ 12. የትብብርና አጋርነትን ማሳደግ ........ 46
ከመማማርና ዕድገት እይታ አንፃር ........ 47
ግብ 13 የስትራቴጂክ አመራር ብቃት ማሳደግ ........ 47
ንዑስ ግብ 13.1. የስትራቴጂክ ዕቅድ አፈፃፀም ውጤታማነት ማሳደግ፣ ........ 47
ንዑስ ግብ፡- 13.2. የተተኪ አመራር ብቃት ማሳደግ ........ 48
ንዑስ ግብ- 13.3. አሰራርና አደረጃጀትን ማሻሻል ........ 48
ንዑስ ግብ፡- 13.4. የሰው ሃብት የማስፈፀም አቅምን ማሳደግ ........ 49
ግብ 14. የመረጃ አያያዝ፣ አጠቃቀምንና ስርጭትን ማሻሻል ........ 50
ግብ 15. ዘመናዊ አሰራርና የቴክኖልጂ አጠቃቀምን ማሳደግ ........ 51
ግብ 16. የተግባቦትና ገፅታ ግንባታ ስትራቴጂ አፈፃፀም ውጤታማነትን ማሻሻል ........ 51
ክፍል አራት ........ 52
4.1. የተቋሙ የ2014 በጀት ዓመት ፕሮጀክቶች እና ለዓመቱ የተመደበ በጀት ........ 52
ክፍል አምስት ........ 57
5.1. እስትራቴጂያዊ የአፈፃፀም አቅጣጫዎች እና ክትትልና ድጋፍ ስርዓት ........ 57
5.1.1. ስትራቴጂያዊ የአፈፃፀም አቅጣጫዎች ........ 57
ክፍል ስድስት ........ 63
6.1. የ2014 በጀት ዓመት የድርጊት መርሃ ግብር ........ 63

## መግቢያ

ፍትህ ሚኒስቴር የተለያዩ እቅዶችን በማውጣት በፖለቲካ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚ መስኮች የተያዙ ግቦችን ለማሳካት እንዲሁም የፍትህ ዘርፉን የአገልግሎት አሰጣጥ በማሻሻል የብረተሰቡን ፍትህ የማግኘት መብት በማስከበር የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ፣ ህገ-መንግስቱንና ህገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን የማክበርና የማስከበር፣ የዜጎች ሰብአዊ ዴሞክራሲዊ መብቶች ማክበርና ማስከበር፡ የወንጀል ህጎችንና የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ፖሊሲውን የማስፈጸም፣ የፌደራል መንግስት ያወጣቸውን ህጎች ተፈፃሚነት ማረጋገጥ፤ የምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃና ከለላ አዋጅ የማስፈፀም፤ የፌደራል መንግስት የሚያወጣቸውን ህጎች፣ የሚወስነውን ትላልቅ ውሳኔዎችና ብሂራዊ ጥቅምን የሚመለከቱ ግንኙነቶችን የማማከር፤ የፌዴራል መንግስቱንና የሕዝብን ፍትሐብሂራዊ መብትና ጥቅም ማስጠበቅ እንዲሁም በወ/ል የተገኘ ሀብት ማስመለስ ተልዕኮ ተሰጥቶታል፡፡ ተቋሙ ይህንን ተልእኮ ለመወጣት አደረጃጀትና አሰራር በመቅረጽ ሕዝብና መንግሥት ከፍትሕ ዘርፉ የሚጠብቁትን ውጤት ለማሳካት ባለፈው እስትራቴጂክ የዕቅድ ዘመን ዘርፈ ብዙ ተግባራትን በማከናወን ውጤት ማስመዝገብ ችሏል፡፡ ሆኖም የፍትህ ዘርፉ ሕዝብና መንግስት የሚጠብቁትን ውጤት ከማስመዝገብ አንፃር በርካታ ጉድለቶች የሚስተዋሉበት መሆኑን ያለፉት የእቅድ ጊዜያት አፈፃፀም ግምገማ እና በተለያዩ መድረኮች ከሕብረተሰብ ተወካዮችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በተደረገው ውይይት ተመላክቷል፡፡

ስለዚህ በተቋሙ ሃላፊነቶች ዙሪያ የሚታዩ አንኳር ክፍተቶችን ለይቶ ለመቅረፍ እና በተቋሙ ደረጃ በተጀመረው የሕግና ፍትሕ ሪፎርም የተገኙትን ውጤቶች ወደላቀ ደረጃ ለማሸጋገርና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የረጅም ጊዜ ስትራቴጅያዊ ዕቅድ በማውጣትና በመተግበር እስትራቴጅያዊ አመራር መስጠት የሚጠይቅ በመሆኑ ተቋሙ የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ እና የቀጣይ አምስት ዓመታት ዝርዝር እስትራቴጂክ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚህ ከያዝነው እስትራቴጂክ ዕቅድ ተመንዝረው /ውስጥ/ በ2014 በጀት ዓመት የሚተገበሩ ግቦች እና ተግባራትን የሚያመላክት ይህ መሪዕ ቅድ ተዘጋጅታል፡፡

መሪ እቅዱ በስድስት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን በክፍል አንድ የራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች፣ በክፍል ሁለት የእቅዱ መነሻ ሁኔታ፣ ውስጣዊና ውጫዊ የዳሰሳ ትንተና እና የአፈጻጸም ግምገማ፣ በክፍል ሦስት የዝግጅትና ትግበራ ምዕራፍ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት ተመላክቷል፡፡ በክፍል አራት የተቋሙ ፕሮጀክቶችና ለዕቅድ የማስፈጸሚያ የተመደበ በጀት፣ በክፍል አምስት የማስፈፀሚያ እስትራቴጂዎች፣ ከትትልና ድጋፍ ስርአት እና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና የመፍትሔ ሀሳቦች የተመለከተ ሲሆን በመጨረሻም በክፍል ስድስት የድርጊት መርሃ ግብር እንዲካተት ተደርጓል፡፡

## ክፍል አንድ

### 1. የራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች

**ራዕይ**

በ2022 የአፍሪካ የፍትሕ ተቋማት ተምሳሌት ሆኖ ማየት፡፡

**ተልዕኮ**

የህግ የበላይነትንና ሰብዓዊ መብትን በማክበርና በማስከበር፣ ወንጀልን በመከላከል፣ ሰላምና ደህንነት በማረጋገጥና የመንግስትንና የህዝብን ጥቅም በማስጠበቅ፣ የሕዝብ ዓመኔታ ያተረፈ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊና ውጤታማ የፍትህ አገልግሎት መስጠት፡፡

**እሴቶች**

1. ሰብዓዊ ክብር
2. የሕግ የበላይነት
3. ታማኝነት
4. ተጠያቂነትና ግልጽነት
5. ሙያዊ ብቃት/ፕሮፌሽናሊዝም/
6. ትብብርና አጋርነት
7. ፍትሐዊነት

- **መሪ ቃል**

  **ለሕግ፣ ለፍትሕ፣ ለርትዕ!**

# ክፍል ሁለት

## 2. የውጫዊና ውስጣዊ ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ

## 2.1. ውጫዊ ሁኔታ ዳሰሳ

### 2.1.1. ዓለም አቀፋዊ የሁኔታ ዳሰሳ

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሠላምና ዕድገት ፀር የሆኑ የተደራጁና ድንበር ዘለል ወንጀሎች በየጊዜው አድማሳቸውን እያሰፉና አሳሳቢነታቸው እየጨመረ መምጣታቸው በተለይ ሽብርነኝነት፣ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር፣ የጦር መሳሪያ፣ የገንዘብ፣ የመድሃኒትና አደንዛዥ ዕፅ ዝውውርና የሳይበር ወንጀሎች የዓለምአቀፍ ማኅበረሰብ ስጋት በመሆናቸው ይህ ተጨባጭ ጫና በሀገራችንም ፈተና እየሆነ መምጣቱ እየተስተዋለ ነው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ከላይ የተጠቀሱትን በተደራጀ ሁኔታ የሚፈፀሙ ዓለማቀፋዊ የሆኑ ድንበር ዘለል ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እያደረገች ያለችው ህግን የማስከበር እና ወንጀለኞች ለፍርድ የማቅረብ ቁርጠኛ አቋም ተመሳሳይ ፍላጎት ላላቸው የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የምታበረክተው የአጋርነት ሚና ወይም አስተዋፅኦ ስጋቱን ለመቀነስ የራሱ ድርሻ እንዳለው መገንዘብ ይቻላል፡፡ይህም በመሆኑ በተለይ ከተለያዩ ሀገራት ጋር የሚደረጉ የሕግ ጉዳዮች ትብብር እያደገ መምጣቱ፤ ዓለማቀፋዊ የሕግና ፍትሕ ስምምነቶች ተፈጻሚነት ማግኘታቸው፣ የአጋርነት መድረኮችና ዲፕሎማስያዊ ግንኙነቶች መሻሻላቸው ሀገራችን በህግ ማስከበር ዘርፉ ካላት የዓለምዓቀፋዊ አጋርነት የሚያያዝ እንደሆነ አመላካች የሆኑ ውጤቶች ናቸው፡፡

በሌላ መልኩ ሀገራችን የጀመረችው ኢንቨስትመንትን የመሳብ የመሰረተ ልማትና የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በመገንባት ኢንቨስተሮችን በማበረታታት የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም የውጭ ባለሀብቶች ወይም ኢንቨስተሮች በሀገራችን ለሚያደርጉት የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ አድማሱን እያሰፋ በመምጣት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት የሚኖረው ፍትሐብሔራዊ ግንኙነትም በዛው ልክ እያደገ ስለሚመጣ የሀገራችንን ጥቅም ለማስከበርና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴውን በማይጎዳና የሀገራችን ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ ግንኙነቶች ሚዛናዊ/ፍትሃዊ እንዲሆን ሕጋዊ መሠረቶችን መጣልና ማስፋት ይጠይቃል፡፡

ይህ መልካም ጅምር ቢሆንም ዓለም አቀፋዊና ሁኔታው ግን በጀመርነው የሰላም፣ የልማት፣ የዲሞክራሲ፣ የፍትሕና የመልካም አስተዳደር ሥራዎቻችን ላይ የሚያሳርፈው አሉታዊ ገጽታም እንዳለ መገንዘብ ተገቢ ይሆናል፡፡ የዓለም አቀፍ የቴክኖሎጂ እድገት እና የማህበራዊ ሚዲያ መስፋፋት ለሃሰተኛ መረጃዎች እና የጥላቻ ንግግር መስፋፋት ምክንያት በመሆን በሀገራችን ለወንጀሎች መበራከት አስተዋፅኦ እያደረገ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሕገ ወጥ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት፣ የሙስና እንዲሁም የኢኮኖሚ ወንጀሎች እየተስፋፉ በመሄዳቸው ሀገራችንም ለእነዚህ የወንጀል ስጋቶች

ተጋላጭነቷ እየሰፋ መጥቷል፡፡ ከአለፈው ዓመት ጀምሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ 19) ወረርሽኝ ወደ ሀገራችን ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚያችንና ማህበራዊ እንቅስቃሴያችን ላይ ከፍተኛ ጫና ከማሳደሩም በላይ በሀገራችን የመከላከያ ሠራዊት ላይ የተፈፀመውን ጥቃት ተከትሎ መንግስት በወሰደው የህግ ማስከበር ተግባር እና ከህዳሴው ግድብ ድርድር ጋር ተያይዞ በርካታ የዓለም አቀፍ ተቋማት በሚያሳዩ የሚቀያየር አቋም ወይም የኢትዮጵያን ጥቅም የሚፃረር የተለየ ፍላጎትና ጣልቃ ገብነት እየፈጠሩት ባለው ጫና ምክንያት ሀገራችን ኢትዮጵያ (ፍትህ ሚኒስቴር ተቋም) ሕጎችን ከማስፈፀምና በሕግ ጉዳዮች አለም አቀፍ ትብብር የማግኘት ተግባሩን በአግባቡ እንዳይፈፅም እየፈጠረ ያለው ተፅዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡

በመሆኑም የተፈጠሩ መልካም ጅምር ስራዎችን እያበለፀጉ በመሄድ ሀገራት ከራሳቸው የተለያዩ ፍላጎቶቻቸው በመነሳት በውስጥ ጉዳያችን ላይ ጣልቃ ለመግባት የሚደረጉ ሙከራዎችንና ጫናዎችን እንዲሁም በሉዓላዊነታችን ላይ የተደቀኑ ፈተናዎችን በተናጥልም ሆነ በጋራ እየመከቱ መሄድ የግድ ይላል፡፡ ስለሆነም የፍትሕ ዘርፉ በተለየ ሁኔታ ደግሞ የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥና የተጀመረውን የለውጥ ጉዞ የማስቀጠል፣ እያደገ ከሚመጣው የኢንቨስትመንት ፍሰት ጋር የሚጣጣሙ ሕጎችን የመቅረጽና የሚታዩ አለመግባባቶችን ሕጋዊ ዋስትና በሚሰጥ መንገድ መፍታት የሚችል የሕግ ማዕቀፍና የሰው ኃይል ማዘጋጀት እና ወቅቱን የሚመጥን ሃላፊነትንና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ ወጥነት ያለው የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መሥራትና ሀገራችን ከተወሰኑ ሀገራትና ከዓለምአቀፉ ተቋማት ከያዙት የተለየ አቋም በመለስ ባሉ ሊያሰሩና ሊያግዙ የሚችሉ የህግ ጉዳዮች ዓለም ዓቀፍ ትብብርን አጠናክሮ መቀጠል የሚጠበቅና እንደ ዋና ተግባር መፈፀም ያለበት እንደሆነ ይታመናል፡፡

## 2.2. አህጉራዊ የሁኔታ ዳሰሳ

አፍሪካ የዓለም አቀፉ አካል እንደመሆኗ መጠን ከላይ በዓለም አቀፍ ሁኔታዎች ዳሰሳ የተነሱት የድንበር ዘለል የወንጀል ድርጊት ጉዳዮች በጥቅሉ አህጉሩንም ሊመለከተው የሚችል ሲሆን በሌላ በኩል ግን በተለይም ከዲፕሎማሲ ግንኙነቶች አንፃር የተወሰነ የእራሱ የሆኑ ጎልተው የሚስተዋሉ አህጉራዊ ጉዳዮች መኖራቸው አይቀሬ ነው፡፡ እንደሚታወቀው አፍሪካ እስካሁንም ድረስ ያልተቀረፈው የሰው ሰራሽ (የጦርነት፣ የአመፅና የግጭት) እንዲሁም የተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ከልማት እና ዕድገት ይልቅ ድህነት፣ ኋላቀርነት፣ የህዝቦች መፈናቀል፣ መሰደድና መገደል፣ የዲሞክራሲ፣ የፍትህና የመልካም አስተዳደር እጦት በስፋት የሚስተዋልበት አህጉር ሆኖ ቆይቷል፡፡ እንደማሳያም በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ለረጅም ጊዜ ሲካሄድ የቆየውን በሀይል ስልጣን መያዝንና በአምባገነንነት መቀጠልን፣ የእርስ በእርስ ጦርነትን፣ አመፅንና ግጭትን ማንሳት ይቻላል፡፡ ከሰው ሰራሽ ችግሮቹ በተጨማሪም ድርቅ እና የዝናብ እጥረትን የመሳሰሉት የተፈጥሮ አደጋዎች በተደጋጋሚ ሲከሰቱ የቆዩበት አህጉር በመሆኑ የእነዚህ የሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ችግሮች የወለዱትን ኋላቀርነትንና ድህነትን መነሻ በማድረግ አህጉሩ ለድንበር ተሻጋሪ የወንጀል ድርጊቶች በቀላሉ የተጋለጠ ሲሆን ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር በሀገራቱ መካከል ጠንካራ ትብብሮችን ለመፍጠር እየተደረገ ያለውን ጥረትና የትብብር ሂደት እንዳይሳካ ከሚያደርጉት ተግዳሮቶች መካከል ሊጠቀሱ

የሚችሉ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ሕገወጥ የሰዎች፣ የአደንዛዥ ዕፅ እና የጦር መሣሪያ ዝውውር፣ የኮንትሮባንድ እና የሽብርተኝነት ወንጀሎች፣ እንዲሁም የባህር ላይ ውንብድና የመሳሰሉት ወንጀሎች የቀጠናውን ሰላም እና መረጋጋት በከፍተኛ ሁኔታ የሚፈታተኑት አህጉር እንዲሆን አድርገውታል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ቀደም ሲል በአፍሪካዊያን ነፃነት እንዲሁም ለአፍሪካ ህብረት መጠናከር የነበራትን ንቁ ተሳትፎና አቋም፤ በቅርቡ ደግሞ በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የፀጥታ መደፍረስ ሲያጋጥም በሰላም ማስከበሩ ዘርፍ ለአፍሪካ ህብረትና ለአፍርሪካዊያ ስታበረክት የቆየችው አስተዋፅኦ፤ሽብርተኝነትንና የፀትታ መደፍረስን ከመከላከል አኳያ ለአህጉሩ የምታበረክተው አስተዋፅኦና አጋርነት የማይለዋወጥ የጓላ ታሪክ ያላት ከመሆኗ ጋር ተያይዞ ከአፍሪካዊያን ጋር ያላት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትና አጋርነት በመልካም ሁኔታ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያ በአጠቃላይ በአፍሪካ በተለይ በምስራቅ አፍሪካ ቀጠና ሰላምና ትብብር እንዲኖር ተዋናይ በመሆን ላለው አንፃራዊ ሰላምና መረጋጋት፤ በአህጉሪቱ ከሚገኙ የተለያዩ ሃገራት የኢኮኖሚና የመሰረተ ልማት ትስስር እንዲኖር እያሳየች ያለችው ፍላጎትና ጥረት በሃገራቱ ዘንድ በመልካም ጎኑ የሚታይ ሲሆን ኢትዮጵያ ለጎረቤት አገራት ካላት በሰላም የመኖርና የመከባበር ከፖሊሲ የመነጨ ፍላጎት፤ ጎረቤት ሀገራት በወንጀል የተጠረጠሩና የተፈረደባቸውን ሰዎች አሳልፎ ለመስጠት እያሳዩ ያለውን ትብብር፤ ከኤርትራ ጋር የተፈጠረውን ሰላምና አጋርነት፤ በምስራቅ አፍሪካ በይየነ መንግስታት (ኢጋድ) የምትጫወተውን ሚና ድንበር ዘለል ወንጀሎች ከመፈፀማቸው በፊት ለመከላከልና ወንጀል ከተፈፀመም የወንጀል ሃላፊነት ያለባቸውን አካት ለፍርድ ለማቅረብ አቅም የሚፈጥፈር እንደሆነ ይታመናል፡፡ ስለሆነም የሀገራችን የፍትሕ ዘርፍ በተለም የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥና ከሀገራቱ ጋር የተጀመረውን የትብብር መልካም ግንኙነት አጠናክሮ መቀጠል የሚጠበቅና ታቅዶ ሊሰራበት የሚገባ ተግባር ነው፡፡

## 2.3 ውስጣዊ የሁኔታ ዳሰሳ

### 2.3.1. ሀገራዊ የሁኔታ ዳሰሳ

የኢፌዴሪ መንግስት የረጅም ጊዜ ዕቅዶችን በማውጣት በፖለቲካ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚ መስኮች የተያዙ ግቦችን ለማሳካት እንዲሁም በሀገራችን ሰላም፣ ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን መንግስትም ዋነኛ የለውጥ አጀንዳ አድርጎ እየሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም ሕዝቦች በሁሉም መስኮች ንቁ ተሳታፊዎች የሚሆኑበት ሥርዓት ለመገንባት፣ በዲሞክራሲ ግንባታና በመልካም አስተዳደር ተግባሮቻችንም ትርጉም ያላቸው ለውጦች በማምጣት ሕብረተሰቡን በየደረጃው የበለጠ ተጠቃሚ ለማድረግ በአዲስ መንፈስ የለውጥ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው፡፡ በቅርብ አመታት በመጣው ለውጥ መንግስት የህግና የፍትህ ሥርዓቱን ለማሻሻል በሰጠው ትኩረት መሠረት የሰብዓዊ መብት አያያዝ እንዲሻሻል፣ የምህረት አዋጅ በማውጣት ሰላምና ለውጡን እንዲያግዝ ማስቻል፣ የፍርድ ቤቶች፣ የዐቃቤ ህግ፣ ፖሊስና የማረሚያ ቤቶች አደረጃጀት እንዲስተካከል፣ የምርመራ ስራዎች በፖሊስና በዐቃቤ ህግ በቅንጅት እንዲሰራ፣ አደገኛ ቅስቀሳዎችን በማራገብ ግጭትንና ብጥብጥን እንዳይባባስ ክልከላ የሚያደርግና ክልከላውን ለተላፉ አካላትን ተጠያቂ የሚያደርግ የጥላቻ ንግግር አዋጅ መውጣቱና ህገ-ወጦች ለሠላም መደፍረስ የሚያዘዋውሩትንና የሚጠቀሙበትን የጦር

መሳሪያ አጠቃቀምና ዝውወር የሚገድብ አዋጅ መውጣቱ፣ በአጠቃላይ የህግ የበላይነት ለማረጋገጥ ከፍተኛ የሆነ እንቅስቀሴ መጀመሩና ከመንግስት መዋቅር ውጭ የተሻለ የህግ እውቀትና የሥራ ልምድ ያካበቱ የህግ ምሁራን ያሉበት የህግና የፍትህ ጉዳዮች አማካሪ ምክር ቤት በማቋቋም ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የሚያግዙ ህጎች እንዲሻሻሉ እየተሰራ ይገኛል፡፡

ሆኖም ዲሞክራሲንና መልካም አስተዳደር በማስፈን ረገድ ሀገራችን ያልተሻገረቻቸው በርካታ ፈተናዎች እና ችግሮች ከመኖራቸው ጋር ተያይዞ ባለፉት ዓመታት በሕብረተሰቡ በርካታ ጥያቄዎች በየጊዜው ሲያቀርቡ ይስተዋላል፡፡ በተለይ በሀገራችን በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ዉስጥ የሕግ የበላይነት መስፈን ዋነኛ ምሰሶ በመሆኑ ህዝብ ከሚፈልገው አንፃር የፍትሕ ስርዓቱና ሕግ የማስከበር፣ የማስፈጸም ተልዕኮዎችን ከመወጣጥ አንፃር ሰፊ ክፍተት ይታይበታል፡፡ በተጨማሪም የሕግ አስከባሪ ተቋማት ገለልተኛ፣ ለፍትሕና ለሙያቸው ታማኝ፣ ለዜጎች መብት ቀናኢ እንዲሆኑ የሕዝብ ፍላጎት ቢሆንም ተቋማቱ ይህንን ፍላጎት በሚያሳካ ቁመና ላይ አለመሆናቸው፣ ሕግ ሁሉንም በዕኩል በመዳኘትና ዜጎች በተፈጥሮ ያላቸውን ሰብዓዊ ክብር በማስጠበቅ ረገድ ጥያቄ የሚነሳበት በመሆኑ በአገራችን ዲሞክራሲ እንዲያብብ፣ ነጻነትና ፍትሕ እንዲሰፍን፣ የሕግ የበላይነት ዕውን እንዲሆን አስፈላጊውን ማሻሻያ በማድረግ በዘርፉ ያለውን ክፍተት መሙላት ይጠይቃል፡፡

በሌላ መልኩ በሀገራችን በየቦታው አሁንም ግጭቶችና የህዝቦች መፈናቀል አለመቆሙ፣ የህብረተሰቡ የህግ የበላይነት አልተከበረም የሚል ስሜት መፈጠሩ፣ የወንጀል መከላከል ስራ በተፈለገው መልኩ አለመሆኑ፣ የተጠርጣሪዎች ማቆያዎች ደረጃቸውን የጠበቁ አለመሆናቸው አሁንም ያልተፈቱ ጉዳዮች ከመሆናቸው አንጻር የህዝብን ጥያቄ ለመመለስና የህግ የበላይነትን ለማስከበር ከፍተኛ ርብርብን የሚጠይቅበት ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን፡፡

ስለሆነም በመንግስት የተነደፈው የአስር አመት መሪ የልማት ዕቅድ እንደ መነሻ ይዞ የተነሳው ኢትዮጵያን የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት (African beacon of prosperity) የማድረግ ራእይ ለማሳካትና ዜጎች ዘር፣ ሐይማኖት፣ እድሜ፣ ፆታ ሳያግዳቸው በማህበረሰባዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያለምንም ተፅእኖ በእኩልነት እንዲሳተፉ ለማድረግ የተመቻቸ የሕግ ማዕቀፍና አፈፃፀም እንዲኖር የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ ዋነኛው የዕቅዱ ምሰሶ በማድረግ ከላይ የተቀመጡት መልካም አጋጣሚዎች አሟጦ ለመጠቀም እንዲሁም ክፍተቶችና ፈተናዎችን በሚፈታ መልኩ አቅዶ መንቀሳቀስን ይጠይቃል፡፡

በሰኔ ወር 2013 ዓ.ም. የሚካሄደውን 6ኛ አገራዊ የምርጫ ወጤት ተከትሎ በሚቀጥለው የበጀት ዓመት የሀገር ሰላም እንዳይናጋ የቅድመ ዝግጅት በማድረግ በበጀት ዓመቱ ሊከሰት የሚችለውን የህግ ጥሰት ለመከላከልና ጥሰት ፈፃሚዎችን ለፍርድ ለማቅረብ የሚያስችል ከጉዳዩ ጋር የሚጣጣሙ ወይም የማይጣረዙ ህጎችን መቅረፅና የሚታዩ አለመግባባቶችን በህጋዊ መንገድ

ለመፍታት የሚያስችሉ የህግ ማእቀፍ ማዘጋጀት፤ ለህዝብ ህጋዊ ዋስትና ለመስጠት የሚያስችል አደረጃጀትና አቅም በመፍጠር ልዩ ትኩረት ተሰጥቶትና ታቅዶ መስራት ያለበት ተግባር ነው፡፡

## 2.3.2. ተቋማዊ የሁኔታ ዳሰሳ

በሕግ የተሰጠው ተልእኮና ኃላፊነት ተግባራዊ በማድረግ ሕዝብና መንግሥት የሚጠብቁትን ውጤት ለማሳካት የረጅም፤ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ ዕቅዶች በማውጣት በርካታ ተግባራት ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ ሆኖም ባለፉት ዓመታት በሃገራችን ለረጅም ጊዜ ከተጠራቀሙት ውስብስብ ችግሮች አኳያ የህግ የበላይነትን በዘቂ ሁኔታ የማረጋገጥ ወሰንነቶች በመኖራቸው ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ፣ ለሰላምና መረጋጋት እና ለሁለንተናዊ ልማት/ዕድገት/ ዋነኛ ማነቆ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ለዚህም ዋነኛ ምክንያት መንግስትም ሆነ የፍትሕ ስርአቱ የሕግ የበላይነትን ከማረጋገጥ አንፃር በፖለቲካ ወገንተኝነቱና በሙያዊ ነፃነቱ ላይ ጥያቄ የሚነሰባት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ክፍተት መኖሩ፤ በየደረጃው ያሉ ፍትህ አካላት የመፈጸም አቅም ውስንነት የነበረበት መሆኑ፤ ተቋማዊ አደረጃጀቱና የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ ሲስተሙ ወይም የአሰራር ሥርዓቱ እንዲሁም ይሰራባቸው ከነበሩት የተወሰኑ የህግ ድንጋጌዎች ዘመኑን ያዋጁ አለመሆናቸው በምክንያትነት ከሚጠቀሱት መካከል የሚገኙ ሲሆን በዚህም ህብረተሰቡ በመንግስትና በፍትሕ ስርአቱ ላይ አመኔታ አጥቶ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም ይህንን ሁኔታ በመሰረቱ ለመለወጥ መንግስት ቁርጠኛ አቋም መያዙና ለዚህም ስኬት የሕግና ፍትሕ ዘርፉ ሪፎርም ዋነኛ የለውጥ ማዕከል በማድረግ ተግባራዊ እርምጃዎች መውሰድ ጀምሯል፡፡ በዚህ መሰረት የሕግ የበላይነት ለማረጋገጥ የመፈፀም አቅምን የመገንባት፤ የማያሰሩ ህጎች የማሻሻል፣ የፍትሕ የተቋማት አደረጃጀት ማሻሻያ/ሪፈርም ስራዎች ማከናወን የሚጠይቅ እንደሆነ ይታመናል፡፡

ፍትህ ሚኒስቴር የዚህ ለውጥ አካልና ባለቤት በመሆን በዘርፉ በሚደረጉ የሕግና ፍትሕ ማሻሻያ እርምጃዎች ሕብረተሰቡንና የዘርፉ ባለሙያዎች በማሳተፍ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡ በተለይም ተቋሙ የሕግ የበላይነት የማረጋገጥ ቁልፍ ሀላፊነት የተጣለበት መሆኑን በውል በመገንዘብ በዚህ ረገድ መሰረታዊ ተቋማዊና የአሰራር ለውጥ ለማምጣት ዕቅዱን ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በዚህም መሰረት መሰረታዊ የሕግና የፍትሕ ችግሮች በመለየትና በቅደም ተከተል በማስቀመጥ ችግሮቹን ለመቅረፍና ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት አደረጃጀትና አሰራር በመዘርጋት ለተግባራዊነቱ በመንቀሳቀስ ውጤት ማስገኘት ጀምሯል፡፡ ከነዚህም የሕግ የበላይነት ለማረጋገጥ የሕግ ጥሰቶችን የማረምና ተጠያቂነት ለማረጋገጥ እየተሰራ ሲሆን የሰብዐዊ መብት ጥሰት በመፈጸም፣ ሙስናና ሌብነት፣ የሕዝብና የሀገርን ሐብት በመመዝበር፤ በተደራጁ ወንጀሎች፣ በብሄር ተኮር ግጭቶች፣ በሕገወጥ ጦር መሳርያ፣ በሕገወጥ ገንዘብ ዝውውርና ሌሎች የኢኮኖሚ ወንጀሎች የተጠረጠሩ አካላትን ተጠያቂ የማድረግ ጅምርና ተስፋ ሰጪ ተግባራት ማከናወን ጀምሯል፡፡ በተለይ መንግስትን በሃይል ለመለወጥ ወይም ህገ-

መንግስታዊ ስርዓቱን ለማፍረስ ጥቃት የፈፀሙ፤ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ብጥብጥና ሁከትን በማስነሳት ጥቃት ያደረሱ፣ አስገድደው የደፈሩ እና የህዝብ፣ የመንግስት ሀብት እና ንብረት ያወደሙ በአጠቃላይ ህገ-ወጥ ድርጊት ሲፈፅሙ በነበሩ ተጠርጣሪዎች ከፌደራል ፖሊስ ጋር በመቀናጀት ለፍርድ እንዲቀርቡ የማድረግ ምጣኔው ከጊዜ ወደጊዜ መሻሻል የታየበት ነው፡፡

በተጨማሪም በጥናት በመመስረት የተቋምና የህግ ማሻሻያ ስራዎች የተከናወኑና በሂደት ላይ ያሉ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ፣ የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ አዋጅ፣ የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ፣ የሚድያ ህግ፣ የምርጫ ህግ፣ የሀሰት ወሬዎችና የጥላቻ ንግግር አዋጅ፤ የጦር መሳሪያ አጠቃቀምና ዝውወር አዋጅ፤ የወንጀል ስነ ስርዐት ህግ፣ የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አዋጅ፣ የጥብቅና ሙያ አስተዳደር አዋጅ፣ የአስተዳደር ስነ ስርዐት ህግ፣ የንግድ ህግ፣ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች (የግልግል ዳኝነትና ሽምግልና) አዋጅና ሌሎችም ተጠቃሽ ናቸው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ -19) ወረርሽኝ ወደ ሃገራችን ከገባበት ከዓመት በፊት ጀምሮ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚያችንና ማህበራዊ እንቅስቃሴያችን ላይ ከፍተኛ ጫና በማሳደሩ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅና ማስፈፀሚያ ደንብና መመሪያዎች ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን መንግስት ደረጃ በደረጃ የመፍትሔ እርምጃዎችን ሲወስድ ቆይቷል አሁንም በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡ ፍትህ ሚኒስቴር የአዋጁንና የደንቡን ማስፈፀሚያ የሚሆኑ ተከታታይ መመሪያዎችን በማርቀቅ በማስገንዘብና በማስፈፀም ሂደት የመሪነት ሚናው ተጫውቷል፣ እየተወጣም ይገኛል፡፡

ሆኖም ተቋሙ ባካሄዳቸው ማሻሻያ ስራዎች ከላይ የተገለጹ ውጤቶች የተገኙ ቢሆንም ለውጡ በተጠበቀው ደረጃ አለመድረሱና የተልእኮ አፈፃጸማችን ከመንግስት የለውጥ ፍጥነትና ከህዝቡ መሰረታዊ የፍትሕ ፍላጎትና ጥያቄዎች አንፃር ሲመዘኑ ገና ጅምር መሆኑ፣ ዜጎች በመብትና በግዴታ ወይም በነጻነትና በሃላፊነት መካከል ያለውን ሚዛን አለመጠበቅና የመብት ጥያቄን በሃይል ለማስፈፀም የሚደረጉ የተደራጁ ሕገወጥ ተግባራት፣ ሀገር እንዲፈርስ ዓላማ በላቸው ፋይናንስ አድራጊነት የነውጥና የሽብር ተግባራት እንዲፈፀሙ በሚገዙ በክህደት የተደራጁ ቡድኖች የሚፈፀሙ የሽር ተግባራት መበራከታቸው፤ የስርዐት አልበኝነት አዝማሚያዎች መታየታቸው፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተከሰቱ ብሄር ተኮር ግጭቶች/ጥቃቶችና በዚህ ሂደት ወንጀል ፈፀሚዎች በተሟላ መልኩ ለሕግ ለማቅረብ ፈተናዎች እየጎለበቱ መምጣቸው፣ ህገወጥ የጦር መሣሪያና የገንዘብ ዝውውር፣ እንዲሁም የሀሰት ወሬዎችና የጥላቻ ንግግር በመስፋፋቱ፣ በሃገሪቱ ትላልቅ ከተሞች በተለይም በአዲስ አበባ በተደራጀ መልኩ የወንጀል ድርጊቶች መበራከታቸው፣ የህብረተሰቡ ንቃተ ህግና ተሳትፎ ማነስ መብትና ግዴታውን ጠንቅቆ የሚረዳ ሕብረተሰብ ከመፍጠር ረገድ ሰፊ ክፍተት መኖሩ፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ግጭት በማስነሳት እና በግጭቱ ተሳታፊ ሆነው ክስ የተመሰረተባቸው በርካታ ተጣርጣሪዎች ለህግ ያልቀረቡ መሆናቸው፣ የሕግ አስከባሪ ተቋማት ከፖለቲካ፣ ከብሔር ወገንተኝነት ወይም / / መሆናቸው ጥያቄ የሚነሳበት ሆኖ መቆየቱና የሙያ ነፃነት ያልዳበረ መሆኑ፣ የተደራጁና ድንበር ዘለል ወንጀሎች በተለይ ሽብርነኝነት፣ ሕገወጥ

የሰዎች፣ የጦር መሳርያ፣ የገንዘብና የመድሃኒት (አደንዛዥ ዕፅ) ዝውውርና የሳይበር ወንጀሎች መበራከታቸው፣ ወንጀሎችን ለመከላከል እና ወንጀለኞችን ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችል ተቋማዊ አቅም የችግሩን ስፋት በሚመጥን አግባ አለመገንባቱ፣ የወንጀል መከላከል ስራ በተፈለገው መልኩ አለመሆኑ፣ የሰብዐዊ መብት አያያዝና አጠባበቅ ህገመንግስቱና አለምአቀፍ ስምምነቶችን ስታንዳርድ መሰረት አለመሆኑ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ 19) ወረርሽኝ በሀገራችን እየተባባሰ በመምጣቱ ተደራሽና የተፋጠነ ፍትህ ለመስጠት እንቅፋት መሆኑ፣ የቤት ውስጥ የፆታ ጥቃት በተለይም የህፃናት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች መጨመር፣ የዘመነ የአሰራር እና የአደረጃጀት ስርዓት በበቂ ሁኔታ ባለመዘርጋቱ ምክንያት ለተቋሙ የተሰጡ ተግባርና ሃላፊነቶች በተሟላ መልኩ አለመተግበራቸው፣ የመካከለኛ አመራሩና የበታች አመራሩ እንዲሁም የፈፃሚዎች አቅምና የስነ-ምግባር ግንባታና ስርፀት በተሟላ ሁኔታ ባለመከናወኑ ለስራው ያላቸው ትኩረት መሰጠት ላይ አነስተኛ በመሆኑ፣ ከሌሎች ፍትሕ አካላትና ባለድርሻ አካላት ጋር የተጀመረውና የሚሰራበት ቅንጅታዊ አሰራሩ የችግሩን ስፋት የሚመጥን አለመሆኑ፣ በዘርፉ የተለዩ ዋና ዋና ክፍተቶች ናቸው፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት እውነታዎች በመነሳት የሕግ የበላይነትን በሀገራችን ሰላምን ለማስፈን የሚደረገው ጥረት ብዙ ተግዳሮት ያለበት እና እጅግ ፈታኝ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ይህንን ፈተና ለመወጣት እና የሕግ የበላይነት የተከበረባት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ተቋማዊ እና መዋቅራዊ የሆኑ፣ ረጅም ጊዜ እና ብዙ ልፋት የሚጠይቁ ለውጦችን ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል። ዘላቂ እና ጥልቀት ያለው የሕግ የበላይነት ባህል እና ስርዓት ለመዘርጋት የተጀመሩ የለውጥ እንቅስቃሴዎች ይበልጥ ተጠናክረው ሊቀጥሉ፣ በተደራጀ መንገድ ተግባራዊ ሊደረጉ እና ይበልጥ ጥልቀት እና ስፋት እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል። የሕግ የበላይነትን እውን ማድረግ የረጅም ጊዜ ትግል የሚጠይቅ የሩቅ ግብ መሆኑ እውነት ቢሆንም፣ በአጭር እና በመካከለኛ ጊዜ ማዕቀፍ የሚሰሩ ስራዎች አሰትዋየም ቀላል አይደለም። በተለይም ከፊታችን ካለው ሀገራዊ ምርጫ ጋር ተያይዞ ሊኖሩ የሚችሉትን እና ባለፉት ሶስት አመታት የታዩትን ችግሮች ከግምት በማስገባት፣ በአጭር እና በመካከለኛ ጊዜ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ እርምጃዎችን መውሰድ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

6ኛውን ሀገራዊ ምርጫ ተከትሎ ሊፈፀም የሚችል ብጥብጥ/አመፅ/ እና የጎዳና ላይ ነውጥ ቢኖር ወንጀልን ለመከላከልና ወንጀል ፈፃሚዎች ለፍርድ ለማቅረብ ጠቅላይ ዐ//ህግ በቂ ዝግጅት አድርጎና ከሚመለከታቸው የፀጥታ ሃይሎች ጋር ቅንጅት በመፍጠር በዕቅዱ አካቶ መንቀሳቀስን ይጠይቃል፡፡

## 2.3. የ2013 በጀት ዓመት የእቅድ አፈፃጸም የሁኔታ ግምገማ

### 2.3.1. የቁልፍ ተግባር አፈፃጸምና አመራር የሁኔታ ግምገማ

**የበላይ አመራሩ ሁኔታ**

የበላይ አመራሩ በ2013 በጀት አመት የተቋሙን መሪ እቅድ በማቀድ እንዲሁም የታቀዱ ተግባራትን በመምራትና ተቋማዊ ለውጡ እንዲጠናከር ስትራቴጂያዊ አመራር በመስጠት ከፍተኛ ሃላፊነት

ሲወጣ ቆይቷል፡፡ በ2012 በጀት አመት የተቋሙ የበላይ አመራር ላይ በመንግስት ለውጥ የተደረገ ቢሆንም ተጀምረው የነበሩ የለውጥ እንቅስቃሴዎች ላይ ምንም አይነት አሉታዊ ተጽዕኖ ሳይኖረው በ2013 በጀት ዓመት የበለጠ በመጠናከር በተቋሙ ላይ የተጣለውን ኃላፊነት ለመወጣት ተችሏል፡፡ የበላይ አመራሩ በተልዕኮ አፈጻጸም በሂደት ላይ የሚስተዋሉ የመካከለኛ አመራሩና ፈፃሚው የአመለካከት፣ ክህሎትና ግብአት ማነቆች በተግባራዊ የዕለተ ተዕለት ግንባታ በመፍታት፣ የተዘረጉ አሰራሮችና አደረጃጀቶች ውጤታማነታቸውን በማረጋገጥ በተደራጀ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅዱን ለማሳካት መምራት እንዳለበት አቅጣጫ አስቀምጦ እየመራ ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት በ2013 በጀት አመት መጀመሪያ ላይ በየደረጃው ያለውን መካከለኛ አመራር ፣ የህዝብ ክንፍና ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ የ2012 ዓ.ም በጀት ዓመት የእቅድ አፈጻጸም በመገምገም የ2013 ተቋማዊ መሪ እቅድ ላይ ኦረንቴሽን እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

ተቋማዊ የአሰራር ሥርዓቶች እንዲቀረፁ እና የነበሩ አሠራሮችን በመከለስ እንዲፀድቁ በማድረግ በአሠራሮቹ ዙሪያ የመካከለኛ አመራሩን፣ ሠራተኛውና ባለድርሻ አካላትን ዓቅም ለመገንባትና ግልጽነት እንዲፈጠር ተደርጓል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ተቋሙ በህግ የተጣለበትን ኃላፊነት በውጤታማነት ለመወጣት ይችል ዘንድ በተቋማዊ አደረጃጀት ላይ የነበሩ ክፍተቶችን በየደረጃው የሚገኙ የተቋሙን አመራሮች እና ፈጻሚዎች ባሳተፈ ሁኔታ የአደረጃጀት ጥናት እና ማሻሻያ ስራ ለመስራት ተችሏል፡፡

የበላይ አመራሩ በተለይ በ2012 በጀት አመት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ተፈጥረው የነበሩ ግጭቶችን የሚያጣራ እና ተገቢውን ህጋዊ ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ የምርመራ እና የዐቃቤ ሕግ በማዋቀር፣ ስምሪት በመስጠት እና አፈጻጸሙን በየጊዜው በመገምገም ቀጣይ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ስራው ውጤታማ እንዲሆን የነበው አስተዋጽዖ በማድረግ በዚህም በጀት አመት ቀጥሏል፡፡

የግብዓት ማነቆንም ለመፍታት ችግሮቹ እንዲለዩ ያደረገና የግዢ እቅድ በማውጣት ግዢ እንዲፈጸም የተሞከረ ቢሆንም ግብዓትን ለሟሟላት የተሄደበት ርቀት ውጤታማ ነው ባያስብልም ከፍተኛ ርብርብ ሲያደርግ ተስተውሏል፡፡ ይሁን እንጂ ከሰው ኃይልና የግብዓት አቅርቦት አንጻር የሚቀርቡ ተደጋጋሚ ጥያቄዎችን ከመፍታት አንፃር ውስንነቶች ታይተዋል፡፡ ከ2012 በጀት አመት አጋማሽ በኋላ በአለም ላይ ስጋት ሆኖ የመጣው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በሀገራችንም መገኘቱ የታወቀ ሲሆን በዚህም ምክንያት በተቋሙ የአገልግሎት አሰጣጥ እና የተለመደ የተልዕኮ አፈጻጸም ሂደት ላይ የራሱን ጫና የፈጠረ መሆኑ የሚታወስ ነው፡፡ ይህ ወረርሽኝ በተቋሙ የተልዕኮ አፈጻጸም፣ የፈጻሚዎች ስምሪት፣ የአገልግሎት አሰጣጥ እና የክትትል እና ድጋፍ አፈጻጸም ላይ የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳደረ ቢሆንም የተቋሙ የበላይ አመራር የፈጻሚው ጤንነት አደጋ ላይ እንዳይወድቅ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት እና በመተግበር፣ የስራ አካባቢ ደህንነት እንዲረጋገጥ የሚያስችል ተግባራትን በመፈጸም፣ አስፈላጊውን ግብዓት በማሟላት እና የፈጻሚ ስምሪትን ከወረርሽኙ አንጻር በመቃኘት ማስተካከያ በማድረግ በተጨማሪም ፈፃሚው እራሱን እንዲያውቅ ለማድረግ በዋናው መስሪያቤት እና በልደታ ዳይሬክቶሬት የኮቪድ 19 ምርመራ እንዲያደርጉ በማድረግ ረገድ የበላይ አመራሩ የመሪነት ሚናውን ተወጥቷል፡፡

በአጠቃላይ የለውጥ ሰራዊት ግንባታው በተደጋጋሚ ቢገመገምም የሚፈለገውን ያህል ለውጥ አለመምጣቱና አደረጃጀቶቹ ወደ እርስ በእርስ መማማር መድረክ ቀይረው ወደ ውጤት ለመቀየር ጥረት ቢደረግም አደረጃጀቱን ከአንድ አንድ ፈፃሚዎች በኩል አደረጃጀቱ ውጤት የመጣል በሚል

በአስተሳሰብ ያለመቀበል፣ የህዝብ ክንፉን በእቅድና አፈጻጸም ውይይትና በሌሎች ጉዳዮች በተሟላ ሁኔታ አለማሳተፍና ተልዕኮ ሰጥቶ አለማሰማራት፣ እንዲሁም ቅልጥፍናን፣ ውጤታማነትን፣ ፍትሀዊነት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የተቀረፁ የለውጥ መሣሪያዎች አጠቃቀም በተሟላ ሁኔታ በጥብቅ አለመተግበርና የክትትልና ድጋፍ አካሄዱም ወጥነት የሚጎድለው በመሆኑ በቀጣይ ሊስተካከሉ የሚገባቸው የአመራር ውስንነቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም አመራሩ ከዕለት ከዕለት ሥራ መጠመድ ወጥቶ ስትራቴጂካዊ የሆነ አመራር ያለመስጠት ችግሩን ለመቅረፍ ልዩ ልዩ የአሰራና አደረጃጀት በመዘርጋት ክፍተቱን ለመፍታት የላቀ ትኩረት መስጠት ይኖርበታል፡፡

### የመካከለኛ አመራሩ ሁኔታ

የመካከለኛ አመራሩ ሚና ለተቋሙ የተሰጡት ተልዕኮዎች እና ኃላፊነቶች የእለት ተእለት አፈጻጸም መከታተል እና መምራት ሲሆን በፈጻሚው እና በበላይ አመራሩ መካከል አገናኝ ድልድይ ሆኖ ማገልገል ሲሆን በዚህ ረገድ በበጀት አመቱ ዕቅድ አፈፃፀም ውጤታማነት የራሱን አስተዋጽዖ አድርጋል፡፡የመካከለኛ አመራሩ ሥራዎች በወጡ አሠራሮች፣ መመሪያዎችና የአገልግሎት አሰጣጥ መስፈርቶች (ስታንዳርዶች) መሠረት መከናወናቸውን፣ ዐቃብያነ ህግና የአስተዳደር ሠራተኞች ሥራቸውን በአገልጋይነት መንፈስ ማከናወናቸውን የድጋፍና ክትትል ሥራ በመሥራት በተቋሙ ተልዕኮ አፈፃጸም አመራር በመስጠት የበኩላቸውን ሚና ለመወጣት ጥረት ተደርጓል፡፡

መካከለኛ አመራሩ ፈፃሚዎች ባወጡት እቅድ የሚመሩ፡ ሣምንታዊ የእቅድ አፈፃፀማቸው የሚገመግሙ፣ ሪፖርት የሚያቀርቡ፣ የእርስ በእርስ ውይይት መድረክ ውጤታማና ችግር ፈቺ መሆናቸውን፣ የተገኙ ለውጦችን በመገምገም ያጋጠሙ ችግሮችን በጋራና በተናጠል እንዲፈቱ አቅጣጫ በመስጠት የክትትልና ድጋፍ ስራ ተሰርቷል፡፡

ይሁን እንጂ የለውጥ መሣሪያዎች አጠቃቀም በተሟላ ሁኔታ በጥብቅ አለመተግበር፣ ከፍትሕ አካላት ጋር በቅንጅት መሰራት ያለባቸውን ጉዳዮች ወጥነት ባለው መልኩና በአሰራር ደረጃ እየፈፀመ አለመሄድ የታዩ ክፍተቶች ሲሆን ፈፃሚዎችን የሚስተዋሉ የአመለካከትና የክህሎት ማነቆዎች ለዋጭ በሆነ መልኩ አለመፍታት፣ የክትትልን ድጋፍ ሥርዓቱ መቀዛቀዝና መቆራረጥ የሚታይበትና የመረጃ አያያዝ ክፍተት በመኖሩ በቀጣይ መሙላት የሚጠይቁ ስራዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በቀጣይ የክትትልና ድጋፍ ስራው መረጃን በማደራጀት መምራት፣ የለውጥ ሰራዊት ከመግንባት ረገድ የታችኛውን አመራር የለውጡ አጋዥ ለማድረግ ማበረታቻ ስርዓት በመዘርጋትና እያበቁ ከመሄድ አንፃር ትኩረት ተሰጥቶበት የሚከናወን ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ መካከለኛ አመራሩ ሥራዎችን በቅርበት በመከታተል ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ከማድረግ፣ ኪራይ ሰብሳቢነትን እቅድ አውጥቶ ከመታገል አንፃር እንዲሁም የለውጥ ቡድኖችን ለመምራት የተደረገው ጥረት የታዩ ጥንካሬዎች ሲሆኑ፣ መካከለኛ አመራሩ በፈፃሚው ላይ የሚስተዋሉ የስነምግባር ችገሮች ከመፍታት፣ ፈፃሚውን የስራ ትጋቱ እንዲጨምርና የአገልጋይነት ስሜት እንዲያዳብር የአመለካከትና የክህት ግንባታ ያለማድረግና ያለማብቃት፣ የተቀረፁ የለውጥ መሣሪያዎች አጠቃቀም በተሟላ ሁኔታ በጥብቅ አለመተግበር፣ ሀሰተኛ ሪፖርቶችን የማቅረብ ችግር መኖሩ፣ የተጠርጣሪ እስረኞችን ጉብኝት ወጥነትና ተከታታይነት ያለመኖርና ጉብኝቱም መፍትሄ ሰጪ እንዲሆን አቅጣጫ ያለመስጠት፣ ከፍትሕ አካላት ጋር የተፈጠረውን ቅንጅታዊ አሰራር ክፍተቶች አለመሙላት፣ መረጃን መሰረት በማድረግ የተሟላ አመራር አለመስጠትና የክትትልና ድጋፍ አካሄዱም ወጥነት የሚጎድለው በመሆኑ በቀጣይ ሊስተካከሉ የሚገባቸው የአመራር ውስንነቶች

ናቸው፡፡

## የፈፃሚው ሁኔታ ዳሰሳ

በዐቃቤ ህግና በአስተዳደር ዘርፉ ያሉ ፈፃሚዎችን በቡድን በመደራጀት ለሥራቸውውጤታማነትና መድረኩን የልምድ መለዋወጫና መማማሪያ ለማድረግ፣ የጋራና የግለሰብ ዕቅድ በማውጣት ሥራን ቆጥሮ ከመረከብና ከመተግበር በየዕለቱ የሚሰሩትን የስራ አፈፃፀሞቻቸውን እየገመገሙ ጠንካራ አፈፃፀሞች እንዲስፋፉ፣ ክፍተቶች እንዲቀረፉና የተሻለ የአፈፃጸም ውጤቶች እንዲመዘገቡ በጎ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ ፈፃሚዎች ስራቸውን በየጊዜው እየገመገሙ መሄዳቸው፣ የእርስ በእርስ መማማር መድረክ በመፍጠር ችግር ፈቺና አቅም ገንቢ የውይይት መድረኮች ማድረጋቸው፣ የቡድን ስሜት በመፍጠርና ሥራዎችን በግለሰብም ደረጃ ቢሆን ውጤታማ ለማድረግ ጥረት ማድረጋቸው በበጎ ጎን የተገመገመ ነው፡፡ በተለይ የከባድና ውስብስብ ጉዳዮች ምርመራዎችን ውጤታማ ለማድረግና በዓቃቤ ሕግ በመዛግብት ለመወሰን በግል ውሣኔ ከመስጠት ይልቅ ዐቃብያን ህግ በቡድን ውይይት በማድረግ ከኃላፊዎች ጋር በመመካከር መወሰን እንዳለባቸው ስርዓት ተዘርግቶ በዚህም የተሻለ ውጤት ታይቷል፡፡ እንዲሁም በሃገሪቱ እዚህም እዛም በሚከሰቱ የዜጎች መፈናቀሎችና ግጭቶችን ለመመርመር ዐቃብያነ ሕግ የሚገጥሟቸውን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ተቋቁሞ በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች በመንቀሳቀስ የዜጎችን መብት ለማስከበር አጥፊዎችን ተጠያቂ ለማድረግ በርካታ ስራዎችን መስራታቸው ይበል የሚያሰኝ ተግባር ነው፡፡

በአጠቃላይ ፈፃሚው በስራው ላይ ፈጣን ምላሽ ሰጪነት ያለማዳበር፣ ራሱን በማብቃት የችግሩም ሆነ የመፍትሄውም አካል እየሆኑ ያለመሄድ፣ የምርመራና ክርክር ክህሎት ማነስ፣ እያንዳንዱን ስራ ሲያከናውን መረጃ መያዝና ማደራጀት ላይ መንጠባጠብ መኖሩና የለውጥ መሳሪያዎችን በመጠቀም ስራዎችን አለማከናወን ክፍተቶች መኖራቸው ታይተዋል፡፡ በተጨማሪም ሁሉም ፈፃሚ በየደረጃው ጠንካራ ቁመና ያለው የለውጥ ሠራዊት አካል ሆኖ ተልዕኮን በተደራጀ መልኩ አለመወጣት፣ የህዝብ አገልጋይነት ስሜት ተላብሶ ሥራን በተነሳሽነትና በባለቤትነት አለመስራት፣ በስራ ቦታዎች አርፍዶ መገኘት ቀድሞ መውጣት፣ የተሰጠውን ስራ በቅልጥፍና እና በጥራት አለመከወን የመሳሰሉት ፈፃሚው ያልተሻገራቸው ችግሮች በመሆናቸው የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ ጠንካራ በክትትልና ድጋፍ፣ በሥልጠናና ልምድ ልውውጥ እንዲሁም ተጠያቂነት የማረጋገጥ ስራን በመስራት ልዩ ትኩረት በመስጠት የሚከናወን ይሆናል፡፡

## የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ (BPR) ሁኔታ

በተጠናው በተቋሙ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ሠነድ መሠረት በተቀመጡ የአሰራር ሂደቶች፣ ተደራሽ ግቦች ለማሳካት ጥረት ተደርጎ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ በቅልጥፍናና ውጤታማነት ላይ መሻሻል እንዲመጣ አስችሏል፡፡ ሆኖም በወጡት አሰራሮች በጥብቅ በመመራት አለመተግበርና የተዘረጉ አሰራሮችን በመዘንጋት ወደ ተለመደው አሰራር በመመለስ በዘፈቀደ የመስራት፣ የሚከናወኑ ተግባራትን በጥናት ሠነዱ መሠረት መረጃ እየያዙ ከመሄድ አንፃር ክፍተቶች መኖራቸው ታይቷል፡፡ ከዚህም በላይ የተጠናው የወንጀል ፍትህ አስተዳደር የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ሠነድ አለመከለሱ፣ በወንጀል ፍትህ ሂደት ቅልጥፍና፣ ውጤታማነት ፍትሐዊነትና ተደራሽነት የራሱ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳርፏል፡፡ በተጨማሪም በተቋማት መካከልም የተናበበና የተቀናጀ አሠራር እንዳይኖር ክፍተት ፈጥሯል፡፡ ስለዚህ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር የመሠረታዊ

የሥራ ሂደት ለውጥ ሠነድ የክለሳ ሥራው በጊዜ አጠናቆ ወደ ስራ ማስገባት መሰራት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ በሌለ። በኩል ተቋሙ አዲስ የአደረጃጀት ጥናት በማድረግ በስራ ክፍሎች ተጠሪነት፣ የስራ ኃላፊነት እና አወቃቀር ላይ የተለያዩ ለውጦች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑ አንጻር የስራ ክፍሎች መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት መደረጉ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## የውጤት ተኮር ሥርዓት አፈፃፀም (BSC) ሁኔታ

የተቋሙን እቅድ በሚዛናዊ የውጤት ተኮር ምዘና ሥርዓት አግባብ በማዘጋጀት ስራ ላይ እንዲውል መደረጉ፣ ዕቅድን በመመዘን የላቀ አፈፃፀም ውጤት ያስመዘገቡ አካላትና ለሠራተኞች እውቅና የመስጠትና የማበረታታት ተግባር መፈፀሙ፣ ዝቅተኛ አፈፃጸም ያላቸው የመደገፍና የማብቃት ጅምር ስራዎች መሰራታቸው በአወንታዊ መልኩ የሚታይ ሲሆን፡፡ ሆኖም የእቅድ አፈፃፀም ከዒላማና ከመለኪያ ጋር በማስተሳሰርና መረጃን በጊዜ በማደራጀት ምዘናውን መረጃን መሰረት አድርጎ አለመፈፀም፣ የተቋሙና ሥራ ክፍሎች የአፈጻፀም ደረጃ ከግለሰብ ፈፃሚዎች ውጤት አለመጣጣምና ግሽበት የሚታየበት መሆኑ በክፍተት ታይቷል፡፡

ስለዚህ የተቋሙን ስራዎች መረጃን መሰረት በማድረግ ለማቀድ፣ ለመገምገምና ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ሁሉንም ስራዎች ከመመዘንና ከመረጃ አያያዝ አንጻር ያለው ክፍተት በዚህ የዕቅድ ዘመን ትረጉም ባለው መልኩ መስተካከል አለበት፡፡ የዓቃቤ ህግ ሥራ አፈፃፀም መለኪያ ወጥነት ማረጋገጥ ጥናት በወቅቱ ማጠቃለልና ስራ ላይ ማዋል በእቅድ ዘመኑ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

## የዜጎች ቻርተር የሁኔታ

የዜጎች ቻርተር ሠነድ በሁሉም ደረጃ የሚሰጡ ዋና ዋና ተግባራትን በመለየት ቀደም ሲል ታትሞ የተሰራጨ ሲሆን የአገልግሎት አሠጣጡ እንዲሁም የሚቀርቡ ቅሬታዎች በቻርተሩ መሠረት ምላሽ ለመስጠት ጥረቶች ተደርጓል፡፡ ሆኖም የተገልጋዩን የእርካታ ደረጃ ለማወቅ ብሎም አገልግሎቱን ለማሻሻል በቻርተሩ በተቀመጡ ጊዜና የአገልግሎት ጥራት ደረጃ መሠጠታቸውን ለማረጋገጥ መረጃዎች በመያዝና ከተገልጋዩ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች በቻርተሩ ጊዜ መሰረት ምላሽ ለመስጠት ላይ ወጥነት መጉደልና ምላሽ አለመስጠት ታይቷል፡፡ ስለዚህ በቻርተሩ በተቀመጡ የጥራትና የጊዜ ደረጃዎች አገልግሎት መሰጠቱ፣ በአገልጋይነት ስሜት ምላሽ ሰጪነት በማረጋገጥ የዜጋውና የተገልጋዩ እርካት እያረጋገጡ መሄድ ቀጣይ ክትትል፣ የአመለካከት ትግልና ለውጥ የሚጠይቅ ነው፡፡

## የቅንጅታዊ አሠራር ሁኔታ ዳሰሳ

ተቋሙ የተጣለበትን ሃላፊነት ለመወጣት ከውስጥና ከውጭ ካሉ የፍትህ አካላት እንዲሁም ባለድርሻዎች ጋር በቅንጅት ስራዎችን መስራት በዕቅድ ይዞ እየሰራ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በተቋሙ ውስጥ ቅንጅታዊ አሠራርን ለማጠናከር በዳይሬክቶሬቶች፣ የሥራ ሂደቶችና በየሥራ ሂደቱ ውስጥ የተደራጁ የለውጥ ቡድኖች እንዲሁም በየቡድኑ ውስጥ የተደራጁ ፈፃሚዎች ሥራዎችን በዕቅድ አቀናጅቶ ለመምራት ጥረት የተደረገ ቢሆንም ከተመደቡበት የሥራ ክፍል አጥር ወጥቶ ለተቋሙ ጋራ ተልእኮና ስትራተጅያዊ ግቦች ስኬት የዓላማ አንድነት በመያዝ ተናብቦና ተደጋግፎ ያለመስራት ችግር በቀጣይነት ሊፈታ ይገባል፡፡ ከክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ተቋማት ጋር የጋራ የምክክር መድረክ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በታገዘ መልኩ ጭምር የተለያዩ የምክክር መድረኮች ተዘጋጅተዋል፡፡ በሃገራችን በተከተሰው የኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት የተለያዩ ስብሰባዎችን እንደቀድሞ ለማድረግ

የማያስችልበት ሁኔታ ላይ ስላለን ለዚህም እንደ አማራጭ የZoom ቪዲዮ ኮንፈራንስ ቴክኖሎጂን ተግባራዊ በማድረግ ከክልል የፍትሕ አካላት ጋር የህግ የበላይነትን ከማረጋገጥ አንጻር እንዲሁም ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አንጻር ያሉ የአፈጻጸም አቅጣጫዎች ላይ ውይይት ተደርጓል፡፡ ከፌዴራል ፍትህ አካላት በተለይም ከፖሊስ፣ መርማሪና ህግ አስከባሪ አካላት ጋር በየደረጃው ካለው አመራር ጋር በአሠራር ሥርዓት መሠረት በቅንጅት ለመሥራት ጥረት የተደረገ ቢሆንም በየደረጃው የተቋቋሙ የጋራ አደረጃጀቶች በተዘረጋው አሰራር መሰረት በጥብቅ በመመራት የጋራ ቅንጅቱ ዉጤታማና መሰረታዊ ለውጥ በሚያመጣ አጀንዳዎች እንዲሆን የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በየደረጃው ያለው አመራር የመሪነት ሚናው ሊወጣ ይገባል፡፡ በሌላ በኩል ከፍትህ አካላት ጋር የሚነሳው የጥምር ኮሚቴ (የፍርድ ቤት፣ ዐቃቤ ህግና ፖሊስ) በሁሉም ደረጃ ከላይ እስከታች በሚባል ሁኔታ ከፍተኛ መቀዛቀዝ ታይቶበታል፡፡ ከፖሊስም ጋር ያለው ሠፊ የቅንጅትና ያለመናበብ ችግሮቹ ምንጭ በማጥናት መሠረታዊ መፍትሔ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

ከሌሎች ሕግ አስከባሪ ተቋማት ጋር ከተቋሙ የስራ ባህሪው አንፃር ቅንጅታዊ አሰራርን ዘርግቶ ስራዎችን ከባለድርሻ አካላትና ተቋማት (ከገቢዎችና ጉምሩክ፣ ንግድ፣ ገንዘብና ኢኮኖሚ ...) ጋር ተቀናጅቶና ተባብሮ የመስራት ሂደትም ጎልቶ የሚታይ አሰራር ባለመዘርጋቱ በቀጣይ ተጠናክሮ የሚሰራበትን ምቹ ሁኔታ መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑ ሊወሰድ ይገባል፡፡

### የድጋፍና ክትትል ሥርዓት የሁኔታ ዳሰሳ

የተጠናከረ የክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ሥርዓት ተግባራዊነትን በማረጋገጥ፣ የአመራሩን፣ የፈፃሚውን በአጠቃላይ የተቋሙን የማስፈፀም አቅም ብቃት ለማሳደግና የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከሌሎች ፍትህ አካላት የሚካሄዱ የግንኙነት መድረኮች ችግር ፈቺ እንዲሆኑ የክትትልና ድጋፍ ሥራ ተሠርቷል፡፡ ከተለያዩ የሥራ ሂደቶች በተውጣጡ ኮሚቴዎች ከወንጀል መዛግብት እና ጉዳዮች አያያዝ አንዲሁም የውሳኔዎች አግባብነት ላይ በወንጀል ዳይሬክቶሬቶች የሚስተዋሉ ችግሮችን በተመለከተ የመዛግብት ኦዲት በማድረግ ጥንካሬዎችና ውስንነቶን በመለየት ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡ሆኖም ክትትልና ድጋፉን ጥራት ባለው መረጃ ላይ ተመስርቶ ከመከወን አንፃር በተቋም ደረጃ የመረጃ አያያዝና አጠባበቅ ትኩረት ያልተሰጠበት በመሆኑ የመረጃዎች ቅብብሎሽም ሆነ አያያዝና አጠባበቅ ስርዓት በአጠቃላይ በዘመናዊ መሳሪያዎች ያልታገዘ ደካማ ሊሆን ችሏል፡፡

በዚህም መረጃዎችን አደራጅቶ በተቋም ደረጃ የመያዝ ረገድ ሂደቱ ባለቤት ያጣ ይመስል እስከ ታች ጣቢያ ድረስ መንጠባጠብ የታየበት መሆኑ ተገምግሟል፡፡ ከዚህ በዘለለም የውሸት ሪፖርቶች መብዛት ማለትም ታማኝና ትክክለኛነታቸው ያልተረጋገጠ ሪፖርት ማቅረብ ተስተውለዋል፡፡ ለዚህም አንድ ማሳያ መዝገቦች የማጥራት አፈፃፀም እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው እየተባለ በስራ ክፍሎች ያለው ተጨባጭ ነገር ግን መዛግብት በመርማሪ ፖሊስና በራሱ ዐቃቤ ህግ እጅ ተከማችተውና ተበራክተው መገኘታቸው ታይቷል፡፡ በመሆኑም የስራ ክፍሎች ለሪፖርት ቁጥር ሳይሆን ለዜጎች ፍትህ የመስጠት ጉዳይ አድርጎ በፖሊስም ሆነ በዐቃቤ ህግ እጅ የሚገኙትን ውዝፍ መዝገቦችን ለመጨረሻ ጊዜ በማጥራት የክትትልና ድጋፍ ዋና አጀንዳ አድርጎ የሚሰራ ይሆናል፡፡

ሌላው ተቋሙ ከላይ እስከታች በቴክኖሎጂ አጠቃቀምና አተገባበር ላይ ኋላ ቀር በመሆኑ ዘመኑ ከሚመጥነው የፍትህ ስርዓትን ማዘመን ጋር አብሮ የማይራመድ ስለሆነ የተቋሙን አሰራር ሲደግፍና ሲያግዝ አይሰተዋልም፡፡ በመሆኑ የወንጀል ስታቲክሶችን መቀባበያ ስርዓት በቴክኖሎጂ ያለመዘርጋት፣ አዳዲስ የተቋሙን አሰራር ሊያግዙ፣ አገልግሎቱን ሊያፋጥኑና ሊያቀላጥፉ የሚችሉ

መተግበሪያዎችን (ሶፍት ዌሮችን) ያለማሳልበትና የመተግበር ሂደት ላይ ደካማ የነበረ መሆኑ ታይቷል፡፡ ስለዚህ የመዛግብት አደረጃጀትና አያያዝ ለቀልጣፋ አገልግሎትና ውሳኔ አሠጣጥ በሚያመች መልኩ በዘመናዊ የአሠራር ሥርዓት በመተግበር ችግሩን መቃለል ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ያለቁና ጊዜ ያለፈባቸው ወይም ሊወገዱ የሚገባቸው በአንድ ማዕከል የመሰባሰብ ሥራ መሰራትና ጥብቅ ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡ በተጨማሪም የተጀመረው መዝገቦችን ወደ ሶፍት ኮፒ መገልበጥና የወንጀል ህጎችን በሶፍት ኮፒ የማጠቃለል ሂደትም አዛጋሚ እንደነበረ የተስተዋለ ሲሆን የቴክኖሎጂ አሰራርን በመዘርጋት ተቋሙን በቴክኖሎጂ ሪፎርም ማድረግን ማዕከል አድርጎ በጠንካራ ክትትልና ድጋፍ መምራት ያስፈልጋል፡፡

ለተቋሙ ተጠሪ የሆኑ ተቋማትን ክትትልና ድጋፍ ከማድረግ አንፃር የተቋማቱን አመራር የማደራጀት፤ አፈፃፀማቸውን እየገመገሙና እየደገፉ ለመሄድ ጥረት የተደረገ ቢሆንም የተሟላ ድጋፍ በማድረግ ረገድ የሚቀሩ ስራዎች ያሉና መቆራረጥ ከመኖሩም በላይ አቅዶ ችግሮቻቸውን በሚፈታ መልኩ የተሄደበት ርቀት አነስተኛ በሚባል ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ የክትትልና ድጋፍ ሥራው ከመተግብር ረገድ የተሰሩ ስራዎች ቢኖሩም በተሟላመረጃ ያልተመሰረተ፣ ተከታታይነት የሌለው፣ ችግር ፈቺና ውጤታማ ባለመሆኑ በተለይም ክልሎችንና ተጠሪ ተቋማትን ከመደገፍ አኳያ አጥጋቢ ባለመሆኑ በቀጣይ ተጠናክሮ ሊተገበር ይገባል፡፡ ስለሆነም በመረጃ ላይ የተመሰረተ አመራር ድጋፍና ክትትል ለመስጠት መረጃ መሰረታዊ ግብአት መሆኑን በማመነን በመረጃ ላይ የተመሰረተ የአመራር ጥበብ ልንከተል ይገባል፡፡

### 2.3.2 የ2013 በጀት ዓመት የአብይ ተግባር እቅድ አፈፃጸም የሁኔታ ግምገማ

**የዕቅድ እና የቅደመ ዝግጅት ተግባራት አፈፃፀም**

- የ10 አመት፣ የ5 አመት እና የ2013 በጀት አመት ፍትህ ሚኒስቴር ዕቅድ በማዘጋጀት ከተቋሙ አመራሮች እና ሰራተኞች እንዲሁም ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት በማደርግ የጋራ መግባባት ላይ ተደርሶ ወደ ትግበራ ተገብቷል፤
- የተቋም አደረጃጀት ተጠንቶ ክለሳ በማድረግ ተግባር ላይ ውሏል፤
- የተቋሙ የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፣
- ከተቋሙ የበላይ አመራሮች እና 98 በመቶ የሚሆኑ የተቋሙ ሰራተኞች ሀብታቸዉን በማስመዝገብ ሰርተፊኬት እንዲሰጣቸዉ ለማደረግ ተችሏል፤
- በነጥብ ሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ዘዴ በተዘጋጀው አደረጃጀት መሰረት ሥራቸው የተመዘኑ የሥራ መደቦች ዝርዝር መረጃ ተደራጅቶ የአስተዳደር ሰራተኛ ምደባ ተከናውኗል፤

**የበጀት አጠቃቀማችንን ከግብ ስኬት አንጻር መለካት፤**

- የመደበኛ በጀትን በተመለከተ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. በ2013 የበጀት ዓመት የታቀዱትን ስትራቴጂያዊ ግቦችና ተግባራትን ለማከናወን ብር 701,085,162.00 የተፈቀደ በጅት ሲሆን፤ በአጠቃለይ የመደበኛ በጀትን በተመለከተ በ2013 በጀት ዓመት ለደመወዝና አበል ለሥራ ማስኬጃና ካፒታል በሰራ ላይ የዋለው በጀት ከጸደቀውና ከታቀደው ብር 701,085,162.00 ጋር ሲነጻጸር በሥራ ላይ የዋለው 691,064564.55 ብር ሲሆን፣ አፈፃፀሙም 99 % ነው፡፡

- ለካፒታል በጅት ለዓመቱ ከተፈቀደዉ ከብር 280,867,598 ላይ ብር 191,709,813.40 ወጪ ሆኖ በሥራ ላይ የዋለ ሲሆን አፈጻጸሙም 68% ሲሆን ይህም የሚያመለክተዉ የካፒታል በጅት በዚህ በጅት ዓመት ዉስጥም በቂ ያአልሆነ አፈጻጸም ያላሣየ በመሆኑ በቀጣዩ በጅት ዓመትም የበላይ አመራር ትኩረት የሚያስፈልገዉ ነው፡

**የግንባታ ፕሮጅክቶች ¨ የፊዚካል ስራዎችና የፋይናንሻል አፈጻጸም**

- **አራዳ ፍትህ አካላት ህንጻ ግንባታ-** ግንባታው ያለበት የአፈፃጸም ደረጃ **(99%)** የደረሰ ሲሆን ለፕሮጀክት ሥራ ለበጀት ዓመቱ ጠቅላላ ከታቀደው ብር (20,000,000) ጋር ሲነጻጸር ብር **26,436,010.75** ሲሆን አፈጻጸሙ **132%** ነው፤
- **የአዲስ ከተማ ፍትህ አካላት ግንባታ -** የግንባታ ሥራው አፈጻጸም ደረጃ (99%) የደረሰ ሲሆን ለፕሮጀክት ሥራ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለበጀት ዓመቱ ከታቀደው ብር **(20, 000,000)** ውሰጥ ብር ብር **12,602,373.58 (63.01%)** ክፍያ ተፈጽሚል፡፡
- **የንፋስ ስልክ ላፍቶ የፍትህ አካላት ህንጻ የግንባታ** - የሥራው አፈጻጸም ደረጃ (94.2%) የደረሰ ሲሆን ለፕሮጀክቱ ሥራ በበጀት ዓመቱ **ከታቀደው** ብር (80,819,716.85) ላይ ብር **69,549,192.31 (86.05%)** ክፍያ ተፈጽሚል፡፡
- **የኮልፌ ቀራኒዮ የፍትህ አካላት ህንጻ ግንባታ** -የህንጻ ግንባታው ስራ ያለበት ደረጃ (15.2%) ይገኛል፡፡ በበጀት ዓመቱ **ከታቀደው** ብር **80,819,716.00 ጋር** ሲነጻጻር ብር **24,768,778.25 (35.94%)** ክፍያ ተፈጽሚል፡፡
- **የዋናው መስሪያ ቤት የህንጻ እድሳት-** (60%) ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በበጀት ዓመቱ **ከታቀደው** ብር (57,000,000) ውስጥ ብር 20,192,057.09 **(35%)** ክፍያ ተፈጽሚል፡፡
- ለብሔራዊ የተቀናጀ ፍትሕ መረጃ ሥርዓት -ለአመቱ ብር 22,584,166.00 የተመደበለት ሲሆን በወጪ የተያዘ ብር የሌለ ስለሆነ በመቶኛ አፈጻጸሙ (0%) ነው፡፡

**የወንጀል ህግን በማስከበር እና የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ ረገድ የተያዙ ግቦች አፈጻጸምን አስመልክቶ ያለው አፈጻጸም ሲታይ፡-**

- በ2013 በጀት አመት ዓመታዊ የምርመራ መዛግብት አፈጻጸም በድምሩ 48,614 መዛግብት በሁሉም የወንጀል አይነቶች እና ደረጃ በፖሊስ ምርመራቸው ተጣርተው የቀረቡ ሲሆን ከእነኚህ መዛግብት ውስጥ በ 47,255 መዛግብት ላይ የተለያዩ ውሳኔዎች በዐቃብያነ ሕግ ተሠጥቶባቸዋል፡፡ የዚህ የማጥራት ምጣኔ አፈጻጸም በመቶኛ ሲታይ 97.2% ይሆናል፡፡ይህ የእቅድ አፈጻጸም ከእቅዱ አንጻር ሲታይ ተቀራራቢ ዉጤት ያለው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡
- አጠቃላይ የክርክር መዛግብት 48,381 ሲሆኑ ከእነኚህ መዛግብት ውስጥ በ 15,596 መዛግብት ላይ በፍርድ ቤት ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ውሳኔ ካገኙት መዛግብት ውስጥ 14924 በሚሆኑት መዛግብት ላይ ዐቃቤ ሕግ ያሸነፈ ሲሆን (ተከሳሾ ጥፋተኛ እንዲባሉ ያስደረገ ሲሆን) በተቀሩት 672 መዛግብት ላይ ደግሞ ተከሳሾች በነጻ እንዲሰናበቱ የተደረገባቸው ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት የዐቃቤ ሕግ የመርታት ምጣኔን ከመዛግብት አንጻር ስንመለከተው 95.7% ነው ፡፡ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ የነበረው አፈጻጸም 95 % የነበረ ከመሆኑ አንጻር የዚህ በጀት አመት አፈጻጸም በ 0.7 % የተሻለ አፈጻጸም የተመዘገበ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡

☞ በበወንጀል ክርክር ሂደት ተከሳሾች ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ለማድረግ እና ተከሳሾች ባለመቅረብ የሚቋረጡ መዛግብት ከ (10%) እንዳይበልጥ ለማድረግ ታቅዶ በዓመቱ ክርክር ከተደረገባቸው 48,381 መዛግብት ውስጥ (9227) መዛግብት የተቋረጡ ሲሆን አፈፃፀሙ (19%) ይሆናል፡፡ አፈፃፀሙ ካስቀመጥነው ግብ አንፃር በ (9%) የቀነሰ መሆኑ ታይቷል፡፡

☞ በወንጀል ክርክር ሂደት ምስክር ባለመቅረብ የሚቋረጡ መዛግብት ከ (5%) እንዳይበልጥ ለማድረግ ታቅዶ በዓመቱ በአራቱም የወንጀል ዓይነቶች ክርክር ከተደረገባቸው (48,381) መዛግብት ውስጥ (2645) መዛግብት የተቋረጡ ሲሆን አፈፃፀሙ (5.4%) ይሆናል፡፡

☞ በሴቶችና ህፃናት የሚፈጸሙ ልዩ ልዩ ወንጀሎች አፈጻጸም ውጤታማነት ከማሳደግ አንፃር በዓመቱ ዉስጥ በአጠቃላይ ምርመራቸው የተጠናቀቀው (1363) መዛግብት ቀርበው ሁሉም መዛግብት ላይ ዐቃቤ ሕግ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ተደርጓል፡፡ ክርክር ላይ ከነበሩ 1028 በሴቶችና ህፃናት ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች መዛግብት ውስጥ በምስክሮች ባለመቅረባቸው 48 መዛግብት የተቋረጡ ሲሆን አፈፃፀሙ 4.6% በመሆኑ በተያዘው ከ5 % በታች የማድረግ ግብ ከዕቅድ በላይ ተከናውኗል፡፡ በሌላ በኩል ተከሳሾች ባለመቅረባቸው 84 መዛግብት የተቋረጡ ሲሆን አፈፃፀሙ አፈፃፀሙ 8% በመሆኑ በተያዘው ግብ ከ10 % በታች የማድረግ በመሆኑ አፈፃፀሙን ማሳካት ተችሏል፡፡ በሴቶችና ህፃናት የወንጀል ቀጥታ ክርክር የማስቀጣት ምጣኔን (96%) ለማድረስ ታቅዶ በዚህ በዓመቱ ውስጥ ክርክር ላይ ከነበሩ መዛግብት ውስጥ 1028 መዛግብት ውስጥ በ(406) መዛግብት ላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡ ውሳኔ ከተሰጠባቸው ውስጥ (378) መዛግብት ላይ የቅጣት ውሳኔ ሲሰጥባቸው (28) መዛግብት ደግሞ በነፃ ተሰናብተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት የማስቀጣት ምጣኔ አፈፃፀማችን በአማካኝ (93.1%) ሊደርስ ችሏል፡፡

☞ **የዓቃቤ ህግ የይግባኝና ሰበር ክርክር መርታት ወደ 65% ማድረስን በተመለከተ፡-** የዓቃቤ ህግ ይግባኝ በጠየቀባቸው መዝገቦች ላይ ተከራክሮ የመርታት ምጣኔን (65%) ለማድረስ ታቅድ በበጀት ዓመቱ ውስጥ 1204 መዛግብት ላይ ክርክር ተደርጎ በ(609) መዛግብት ላይ በፍ/ቤት ውሳኔ ተሠጥቶባቸዋል፡፡ ውሳኔ ከተሰጠባቸው የዓቃቤ ህግ ይግባኝ ውስጥ በ(350) መዝገብ በማሸነፍ የመርታት ምጣኔያችን (57.5%) ሊደርስ ችሏል፡፡የዓቃቤ ይግባኝ ካባለፈት ዓመታት አንፃር የተሻለ አፈፃፀም ተመዝግቧል፡፡

☞ **በተከሳሽ ይግባኝ የተጠየቀባቸው መዝገቦች ላይ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔዎች እንድፀኑ የማድረግ አቅም (97%) ማሳደግን በተመለከተ፡-** በጥቅሉ በበጀት ዓመቱ ውስጥ (1322) መዛግብት ላይ ክርክር ተደርጎ በ(998) መዛግብት ላይ በፍ/ቤት ውሳኔ ተሠጥቶባቸዋል፡፡ ውሳኔ ከተሰጠባቸው የተከሳሽ ይግባኝ ውስጥ (65) መዛግብት የተቋረጡ ሲሆን በ (864) መዝገብ በማሸነፍ የመርታት ምጣኔያችን በአማካኝ (92.6%) ሆኗል፡፡

☞ **በፍርድ ቤት ከሚሰጡ የገንዘብና የእስራት ቅጣት ዉስጥ 80% የሚሆኑትን ማስፈፀምን በተመለከተ፡-** በበጀት ዓመቱ በሁሉም የወንጀል ጉዳዮች በፍርድ ቤት በቀረቡ ክሶች እና በተደረጉ ክርክሮች ዐቃቤ ሕግ በረታባቸው መዛግብት ላይ በገንዘብ እንዲቀጡ ፍርድ ቤት ውሳኔ ካስተላለፈባቸው መዛግብት ውስጥ በድምሩ 20,005,808 (ሃያ ሚሊየን አምስት ሺህ ስምንት መቶ ስምንት ብር) በዚህ ዓመት ዉስጥ ቅጣት የተጣለ ሲሆን ከዚህ ውስጥም

አብላጫውን ድርሻ የሚይዘው የገንዘብ መጠን ለመንግስት ገቢ ተደርጓል፡፡ የተቀሩት ደግሞ የአፈጻጸም ክትትል እየተደረገባቸው ይገኛል።

**ልዩ ትኩረት ከሚደረግባቸው የወንጀል መዛግብት አንጻር ሲታይ፡-**

- ☞ ሰኔ 15/2011 ዓ.ም በመከላከያ ከፍተኛ አመራር ላይ ከተፈጸመው የግድያ ወንጀል ጋር በተያያዘ ወንጀሉን የፈጸመው በእድሜ ልክ እንዲቀጣ ለማድረግ ተችሏል፤
- ☞ አርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳ ላይ ግድያ የፈጸሙ ግለሰቦች አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች ለፍርድ ቤት ቀርቦ ጥፋተኛ ተብለዋል፤
- ☞ ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም የአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ዞኖችና በአዲስ አበባ ላይ ከተፈጸመው ወንጀል ምርመራውን በማከናወን በኦሮሚያ ክልል አምስት ዞኖች በ114 የክስ መዛግብት 2883 ከሚሆኑ ተከሳሾች ጋር ክርክር ተደርጎ፤ 2495 ምስክሮች ተሰምተው እስካሁን 581 ተከሳሾች ጥፋተኛ የተባሉ ሲሆን ቀሪዎቹ በሂደት ላይ ይገኛሉ፤
- ☞ ጅግጅጋ ላይ በተፈጸመው ወንጀል በእነ አብዲ መሀመድ ኡመር (አብዲ ኢሌ) መዝገብ ላይ ከ20 በላይ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የተሰሙ ሲሆን ቀሪ ምስክሮችን በመስማት ሂደት ላይ ይገኛል፣
- ☞ ከሰብአዊ መብት ጥሰት ጋር ተገናኝቶ በቀድሞው የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አመራሮች እነ ጌታቸው አሰፋ (26 ሰዎች) እንዲሁም የፌዴራል ፖሊስ አባላትና የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባላት ላይ ምስክር የማሰማት ሂደት ላይ ይገኛል።
- ☞ የአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳ ግድያን አጋጣሚ በመጠቀም የተለያዩ የወንጀል ተግባራትን በፈጸሙ በእነ ጀዋር መሀመድ (23 ሰዎች) ላይ በቀረበው ክስ ላይ ያቀረቡትን መቃወሚያ ተመልክቶ ብይን ለመስጠት እንዲሁም በእነ እስክንድር ነጋ (7 ሰዎች) ላይ በቀረበው ክስ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን ለመስማት ተቀጥሯል
- ☞ የህዋሃት ቡድን በመከላከያ ሰራዊት እና በሀገር ላይ በፈጸመው ጥቃት እንዲሁም በማይካድራ በንጹሐን ዜጎች ላይ በተፈጸመው ጥቃት መነሻነት ባለሙያዎችን ወደ መቀሌ፤ ማይካድራ እና ራያ አከባቢ በማንቀሳቀስ እንዲሁም በአዲስ አበባ ቡድን በማቋቋም ምርመራው እየተከናወነ ይገኛል።
- ☞ ሰኔ 16 በመስቀል አደባባይ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ በተፈጸመው የግድያ ሙከራ ክስ ቀርቦባቸው ከነበሩ ተከሳሾች ውስጥ 4 ተከሳሾች በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብለው ከ5 አመት እስከ እድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ለማስወሰን ተችሏል።
- ☞ ከሙስና ወንጀሎች ጋር ተያይዞ በርካታ ከባድ፤ ውስብስብ የሆኑና ልዩ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ክትትል እየተደረገባቸው የሚገኙ ሲሆን የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን አመራሮች በነበሩ ግለሰቦች ላይ የሙስና ወንጀል ክስ ቀርቦ ማስረጃ የመስማት ሂደት ላይ ናቸው።

**በወንጀል የተገኘ ሀብትን ከማስመለስ፣ ከማሳገድ እና ከማስወረስ አንጻር ሲታይ፡-**

- ☞ ***የተመለሰና ገቢ የሆነ*** ፡- በበጀት ዓመቱ በአይነት ገቢ የተደረጉ ንብረቶችን ጨምሮ በሙስና እና በሌሎች የተደራጁ የኢኮኖሚ ወንጀሎች የተመዘበረ ሃብት በድምሩ ብር **ብር 162,715,071.00** በሃብት ማስመለስ ዳይክቶሬት ጄነራል አማካኝነት ወደ ሕዝብና መንግስት እንዲመለስ ተደርጓል፡፡ ከተመለሰዉ ገንዘብ ዉስጥ ብር **68,949,567.52** (ስድሳ ስምንት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ስድሳ ሰባት ብር) ሕወሃት በተባለዉ አሸባሪ ድርጅት ስም የተገኘ እና በሕግ አግባብ ወደ ምርጫ ቦርድ ገቢ ማድረግ ተችሏል።

- ☞ በተጨማሪም ግምታቸዉ **2 ቢሊየን** ብር የሆነ የትራንስ ኢትዮጵያ 179 የደረቅና ፈሳሽ ጭነት ከባድ ተሽከርካሪዎችን በፍ/ቤት የሕግ ትብብር ጥያቄ ለጅቡቲ መንግስት በማቅረብ ማስመለስ ተችሏል።

- ☞ ***ሃብት ገቢ ለማድረግ በአፈጻጸም ሂደት ላይ ያሉ ጉዳዮች***፡-በፍ/ቤት ጥፋተኛ የተባሉ እና ንብረታዉም እንዲወረስ ዉሳኔ በተሰጠባዉ 23 ጉዳዮች ላይ ብር**638,450,099/ስድስት ሚሊዮን ሰላሳ ስምንት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ብር ከዘጠና ዘጠኝ ሳንቲም** እና **48** ተሸከርካሪና 3 የመኖሪያ ቤቶች እና 2 ማሽነሪዎች ላይ ለሕዝብና መንግስት ገቢ ለማድረግ የአፈጻጸም ክትትል እየተደረገ ነዉ፡፡

- ☞ ***የዉርስ አቤቱታ እና የፍታብሔር ክስ የቀረበባቸዉ ጉዳዮች***፡-በተከሳሾች ላይ በፍ/ቤት የጥተኝነት ዉሳኔ በተሰጠባቸዉ **14** ጉዳዮች ላይ ብር 165,609,149 ብር / አንድ መቶ ስድሳ አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶአርባ ዘጠኝ ብር/፣ 1,999.68 ካሬ ሜትር መሬት እና 190,661.83 የአክሲዮን ሼር ይዞታ ለማስመለስ የውርስ አቤቱታ ያቀረብን ሲሆን በተለያዩ ምክንያት የወንጀል ጉዳያቸዉ በተቋረጠ 7 ማዛግብት ላይ ብር 564,935,775.63/አምስት መቶ ስድሳ አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰላሳ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ አምስት ብር ከስድሳ ሶስት ሳንቲ. / የፍትሀ ብሄር ክስ መስርተኛል፡፡

- ☞ ***የሀብት ምርመራ በሚደረግባቸው መዛግብት የታገዱ/የተያዙ ንብረቶች/ገንዘብ***፡-በበጀት አመቱ ምርመራ በተጀመረባቸው ሁሉም መዛግብት ላይ የሀብት ጥናትና ምርመራ በማከናወን የወንጀል ፍሬ ወይም ወንጀል መፈጸሚያ የሆኑ እንዲሁም በወንጀል ለደረሰ ጉዳት ማካካሻ የሚሆኑ የተጠርጣሪ/ተከሳሽ ንብረቶች ንብረቶች ሆነዉ ዕግድ ሊወጣባቸው በሚገባ በሁሉም ጉዳዮች ላይ የፍ/ቤት የእግድ ትዕዛዝ እንዲወጣ የተደረገ ሲሆን በዚህም ጥሬ ገንዘብ ብር 5,300,578,447.98 ፣ ተሸከርካሪ 805 ፣ ቤት ፣ 140፣ ድርጅት 15፣ አክሲዮን ብር 462,737,999.62፣ ማሽነሪ 496 ፣ ቦንድ፡- 235,521.74፣ መሬት፡-328,296 ካሬ መሬት ፣ ብረት፡ 601,069 ኪሎ ግራም እንዲታገድ ተደርጓል፡፡

- ☞ ከዚህ ዉስጥ ብር 5,222,264,185.00፣ አክሲዮን ድርሻ ብር 450,440,736.62/አራት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን አራት መቶ አርባ ሺህ ሰባት መቶ ሰላሳ ስድስት ብር ከስድሳ ሁለት ሳነቲም) ፣ 42 ቤቶች፣ 711 ተሽከርካሪዎች፣484 ማሽነሪዎች እና 15 ድርጅቶች እንዲሁም 235,521.74 ቦንድ ላይ የተሰጠዉ የገንዘብና ንብረት ዕግድ በሕወሃት የሽብር ቡድን ፣በሽብር ቡድኑ ጋር ግንኙነት ባላቸዉ ግለሰቦች፣ የንግድ ድርጅቶችና ሲቪል ማህበራት አመራሮች ሀብትና ገንዘብ ላይ የተሰጠ ዕግድ ነዉ፡፡

- ☞ ***የታገዱና የተያዙ ንብረቶች ለሌላ የወንጀል ዓላማ እንዳዉሉና በአግባቡ ተጠብቀው እንዲያዙ ለማድረግ የተሰሩ ሥራዎች***፡-በበጀት አመቱ የኤፈርት ድርጅቶች፣ የትግራይ ልማት ማበር

እና ማህበረ ረድኤት ትግራይን ጨምሮ በ7 የተለያዩ ጉዳዮች ላይ በተያዙ ሀብቶች ላይ አስተዳዳሪ በማሾም ንብረቶቹ ለሌላ የወንጀል ዓላማ እንዳይሉና እንዳይባክኑ ለማድረግ ተችሏል፡፡

- በህውሃት የሽብር ቡድን አመራሮች ስም በአዲስ አበባ በሚገኙ 12 ተጠርጣሪዎች ስም ተመዝግቦ የሚገኙ 10 የመኖሪያ ቤቶችና 2 ንግድ ማዕከላት ላይ ፌዴራል ቤቶች አስተዳደር በአስተዳዳሪነት ተሹሞ ሥራውን የጀመረ ሲሆን በተመሳሳይ በመቀሌ በሚገኙ 19 ተጠርጣሪዎች እጅ በተገኙ 24 ቤቶችና ድርጅቶች ላይ ኮሚርሻል ኖሚኒስ እንዲያስተዳድራቸው በፍርድ ቤት ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ ይህ ሥራ በአሁኑ ሰዓትም ይህ ሥራ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

***የመንግስትና የህዝብን ፍትሐብሔራዊ ጥቅም ከማስጠበቅ አንጻር፡-*** ተገቢውን የሕግ ምክር ከመስጠት፣ ረቂቅ ውል ምርመራ እና ዝግጅት ከማካሄድ፣ በሐገር ውስጥና ከሐገር ውጭ ባሉ በዳኝነት እና ከፊል ዳኝነት ስልጣን ባላቸው አካላት ዘንድ ቀርቦ ከመከራከር፣ በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ክርክሮች እንዲቋጩ ከማድረግ፣ የፍትሐብሄር ውሳኔዎችን ከማስፈፀም እና ለመንግስት ተቋማት ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ከማድረግ አንፃር በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በዚህ መሰረት፡-

- ለሚቀርቡ የሕግ ምክር በተቀመጠው አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ መሰረት 100% ለመስጠት ተቃዶ ለቀረቡ ለ3,364 የፍትሐብሔር የህግ ምክር ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ምላሽ በመስጠት አፈጻጸሙ 100% የደረሰ ሲሆን እቅዱን ማሳካትና ባለፈው ዓመት በተመሳሳይ ወቅት በቀረበው ሪፖርት ጋር ተመሳሳይ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል፤

- ለሚቀርቡ የረቂቅ ውል ምርመራና ዝግጅት በተቀመጠው አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ መሰረት 100% ለማከናወን ተቃዶ የግዙፍ የመንግስት ፕሮጀክቶች ውሎችን ጨምሮ ለቀረቡ 37 የረቂቅ ውልና ሰነዶች ምርመራ ጥያቄ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት 100% ምላሽ የተሰጠ በመሆኑ እቅዱን ማሳካት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ የረቂቅ ምርመራ የተደረገባቸው ውሎች የያዙት የገንዘብ መጠን 25,716,641,834 የአሜሪካን ዶላር፣ 3,550,177.98 ዩሮ እና 85,288,190.47 ብር ነው፤

- በመንግስት ተቋማት መካከል የመፈጠሩ አለመግባባቶችን ግራ ቀኙን በማነጋገር በድርድር የመቋጨት አቅምን 79% ለማድረስ ተቃዶ በበጀት ዓመቱ ውስጥ 76 መዛግብት ለድርድር ቀርበው 44 መዛግብት በስኬት አንድ መዝገብ ደግሞ በስኬት ማጠናቀቅ አልተቻለም፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዮችን በድርድር የመቋጨት ምጣኔ 95.67% ማድረስ የተቻለ ሲሆን ይህ አፈፃፀም የመንግስት ተቋማትን ጉዳይ በድርድር መፍታትን ብቻ ያማከለ ከሆነ ውሳኔ ካገኙት ውስጥ ሁለት የመንግስት ተቋማት የተደራደሩበት በስኬት በመጠናቀቁ አፈጻጸሙ 100% ነው ማለት ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ በድርድር የታዩት ጉዳዮች የያዙት የገንዘብ መጠን ድምር 425,444,745.95 ብር እና 24,314,405.17 የአሜሪካን ዶላር ነው፤

- በዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት የሚታዩ ጉዳዮችን በመከታተል የመንግስትን እና የህዝብን ጥቅም ከማስጠበቅ አንፃር በበጀት ዓመቱ ውስጥ በ15 ጉዳዮች ጉዳዮቹ ከተነሱባቸው ተቋማት ጋር በመሆን ተሳትፎና ክትትል እያደረግን የሚገኝ ሲሆን በአጠቃላይ በቀጥታ/በተዘዋዋሪ ተሳትፎ ያደረግንባቸው የግልግል ዳኝነት ጉዳዮች የያዙት የገንዘብ መጠን 1, 17,867,705.76

ዩሮ፣ 359,854.80 የእንግሊዝ ፓውንድ፣ 178,384,482 ብር እንዲሁም 808,976,181.2 የአሜሪካን ዶላር ነው፤

- በፍርድ ቤት የሚቀርቡ የፍትሐብሄር ክርክሮች ላይ ብቃት ያለው ክርክር በማድረግ የመርታታ ዓቅምን ወደ 95% ለማድረስ ተቃዶ በቀጥታ ክስ ክርክር የተደረገባቸው መዛግብት ብዛት 480 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ በ288 መዛግብት ላይ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ ውሳኔ ከተሰጠባቸው መዛግብት ውስጥ በ282 ስናሸንፍ በ6 መዛግብት ላይ ዐቃቤ ህግ ተረትቷል፡፡ በዚህ መሰረት የበጀት ዓመቱ አፈጻጸም አማካይ ውጤት 97.91% ማድረስ የተቻለ ሲሆን ይህ ውጤት በእቅድ ከተያዘው 95% ሆነ ከባለፈው በጀት ዓመት አፈጻጸም ውጤት አንጻር ሲታይ ብልጫ ያለውና ከፍተኛ መሻሻል የታየበት ነው።

**ሕግ ማርቀቅን በተመለከተ፡-** በ2013 ዓ.ም በጀት ዓመት ውስጥ አስራ ስድስት ሕጎችን ለማርቀቅ እቅድ ተይዞ የነበረ ሲሆን በዚሁ መሰረት አስራ ስምንት ሕጎችን፣ ሁለት ጋይድላይኖችን እና አንድ ሀተታ (commentary) በአጠቃላይ 21 ረቂቅ ሰነዶችን የማርቀቅ ስራ ተሰርቷል፡፡

**የህግ ማጠቃለል ስራን** በተመለከተ ቀሪ ያልተጠቃለሉ ህጎችን ለማጠቃለል እና አሳትሞ ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ እቅድ ተይዞ ነበር፡፡ በዚሁ መሰረት ቀሪ ያልተጠቃለሉ እና እስከ ሚያዚያ 2013 ዓ.ም (አዋጅ ቁጥር 1234/2013) ድረስ የወጡ አዋጆችንና ደንቦችን የመሰብሰብ፣ ያልተጠቃለሉ የፌዴራል ህጎችን የማጠቃለል ስራን ያጠናቀቅን ሲሆን እስካሁን የተጠቃለሉትን ህጎች አሳትሞ ለማሰራጨት በተያዘው እቅድ መሰረት የማሳተሙ ስራ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

**የህግ ማረም ስራን** በተመለከተ ከልዩ ልዩ ተቋማት የሚቀርቡ ረቂቅ ህጎች ላይ 100% ከህገ-መንግስቱ፣ ከፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ ሀገሪቱ ከምትገደድባቸው አለማቀፍ ስምምነቶች፣ ከሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች እንዲሁም ባለብዙ ዘርፍ ተግባራትና መሰል ጉዳዮች አንፃር ተገቢዉን እርማት በማድረግ ምላሽ መስጠት፣ እንዲሁም ተቋሙ በሚያዘጋጇቸው መመሪያዎችና የአሰራር ስርዓቶች ወይም ሌሎች ህጎች ላይ 100% የእርማት ስራ መስራት፣ የሚል እቅድ የተያዘ ሲሆን፣ በዚሁ መሰረት 124 ጉዳዮች ቀርበው በሁሉም ጉዳዮች ላይ ተገቢው እርማት ተደርጓል፡፡ አፈፃፀሙን በተመለከተ 100% መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

**የሕግ ምክርን በተመለከተ** በዓመቱ ውስጥ በ59 ጉዳዮች ላይ ምክር እንድንሰጥ በተለያዩ አካላት የተጠየቅን ሲሆን በሁሉም ጉዳዮች ላይ በፅሁፍ፣ በመድረክ በመገኘት፣ ፊትለፊት በመገናኘትና በመሳሰሉት ዘዴዎች በሁሉም ጉዳዮች ላይ ምክር የተሰጠ ሲሆን፤ የሕግ ረቂቅ እርማትን በተመለከተ 124 ጉዳዮች ቀርበው በሁሉም ጉዳዮች ላይ ተገቢው እርማት ተደርጓል፡፡

መመሪያዎችን ወጥ የሆነ ቁጥር በመስጠት ከመመዝገብና ለህዝብ ተደራሽ ከማድረግ አንፃር ከተለያዩ የአስተዳደር ተቋማት የተላኩ ስምንት መቶ አርባ ስድስት (846) የሚሆኑ መመሪያዎችን ወጥ ቁጥር በመስጠት የመመዝገብና በተቋማችን ድረ-ገፅ ላይ የመጫን ስራ ተሰርቷል፡፡የተመዘገቡ መመሪያዎችን ለየተቋማቱ ለማሳወቅና በየተቋማቱ ድረ-ገፅ ላይ እንዲጭኑ ለማድረግ፣ ያላስመዘገቡ ተቋማትም ልከው እንዲያስመዘግቡ በማሳሰብ የተመዘገቡ መመሪያዎችን አባሪ በማድረግ ለፌዴራልና ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስተዳደር ተቋማት በሁለት ዙር በደብዳቤ የማሳወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡

የዓመቱን የጥናት እቅድ መሰረት በማድረግም በበጀት ዓመቱ ውስጥ አምስት ጥናቶች ተሰርተው የተጠናቀቁ ሲሆን አንዱ በመጠናት ላይ ይገኛል፡፡ አንድ ተጨማሪ ጥናት በመሰራት ላይ በመሆኑ አፈጻፀሙ ከእቅድ በላይ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በሂደት ላይ የሚገኘውን የወንጀል ሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ የማፀደቅና ተያያዥ ተግባራትን ለማከናወን በበጀት ዓመቱ በአዲስ መልክ በተቋቋመው የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ፅ/ቤት በኩል የተከናወኑ ተግባራትብ በተመለከተ ረቂቅ የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት እና ማስረጃ ሕግ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ለተነሱ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ በመሰጠቱ እና የሕጉን አስፈላጊነት በማስረዳት በመቻለሉ በምክር ቤቱ አባላት የተሰጡ አስተያየቶች ተካተው ረቂቁ ፀድቋል፡፡

**በሕግ ጉዳዮች ከሚከናወኑ የዓለም አፍ ትብብር ተግባራት ረገድ** የአሳልፎ መስጠት እና የወንጀል ጉዳዮች የፍትሕ ትብብር ስምምነቶችን ማድረግ በተመለከተ በኢትዮጵያና ኡጋንዳ መካከል የተፈረሙት የአሳልፎ መስጠትና በወንጀል ጉዳይ የፍትሕ ትብብር ስምምነቶች በሚኒስትሮች ም/ቤት ተቀባይነት አግኝተው ወደሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ተልከው እንዲፀድቁ ለማድረግ መግለጫ፣ የስምምነቶች ድንጋጌዎች ማብራሪያ እና የማፅደቂያ ረቂቅ አዋጆች ተዘጋጅተዋል፤ ስምምነቶቹ በሚኒስትሮች ም/ቤት ተቀባይነት አግኝተዋል፤ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ተዋካዮች ም/ቤት የሕግ፣ ፍትሕና ዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ባዘጋጀው መድረክ ላይ በአስረጅነት በመገኘት በስምምነቶቹ ዙሪያ ለቀረቡ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቶ እንዲፅድቁ ሆነዋል፡፡ በተጨማሪም ከኬንያ መንግሥትና ከአልጄሪያ መንግስት ጋር ስምምነቶችን ለመፈራረም በሂደት ላይ ይገናል፡፡

በአሳልፎ መስጠት እና በወንጀል ጉዳዮች የፍትሕ ትብብር ጥያቄዎችን ለሌሎች የማቅረብ እና ከሌሎች ሀገራት ተቀብሎ ምላሽ መስጠትን በተመለከተ በጂቡቲ መንግስት በወንጀል የሚፈለጉ ሶስት ግለሰቦች ተላልፈው እንዲሰጡ ተደርጓል፤ በትግራይ ክልል ካለው ሕግ የማስከበር ተግባር ጋር በተያያዘ በወንጀል የሚፈለጉ ሶስት ግለሰቦቹ ከጂቡቲ መንግስት ተላልፈው እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ተጠርጥሮ በታንዛኒያ በቁጥጥር ስር የዋለ አንድ ኢትዮጵያዊ ተላልፎ እንዲሰጥ ለታንዛኒያ መንግስት ጥያቄ አቅርበናል፡፡ ሕገወጥ ሰዎችን በማዘዋወር ኔትወርክ ውስጥ ተሳታፊ ግለሰቦች/ድርጅቶችን ለመለየትና ተጠያቂዎችን ለፍትሕ ለማቅረብ በውጭ ጉዳይ ሚ/ር በቀረበው ጥያቄ መነሻ የጋራ የወንጀል ምርመራ (joint Investigation) ለማድረግ እንዲቻል ለጂቡቲ፣ ለኬንያ፣ ታንዛኒያ እና ደቡብ አፍሪካ የፍትሕ ትብብር ጥያቄዎችን አቅርበናል፡፡ ተላልፈው እንዲሰጡ በሚፈለጉ እና የሚገኙበት ሀገር ባልታወቁ 6 ግለሰቦች ላይ የሚገኙበትን አገር (አድራሻ) ለማወቅ እንዲቻል ዓለም አቀፍ ማፈላለጊያ ቀይ ማስታወቂያ (Red Notice) እንዲወጣባቸው እንዲደረግ አስፈላጊ መረጃዎችን በማሰበሰብ ለብሔራዊ ኢንተርፖል እንዲላክ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች የትብብር ጥያቄዎች ለአውስትራሊያ እና አሜሪካ መንግስታት የተላከ ሲሆን ከሩማንያ እና ኔዘርላንድ መንግሥት ለቀረቡ ደግሞ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

በተጨማሪም በፍትሐብሔር ጉዳዮች የጋራ የፍትሕ ትብብር ዙሪያ በተላኩ ረቂቅ ስምምነቶች ላይ አስተያየት መስጠት፣ በፍትሐብሔር ጉዳዮች የፍትሕ ትብብር ጥያቄዎችን ለሌሎች ማቅረብ እና ከሌሎች ሀገራት ተቀብሎ ምላሽ መስጠትን፣ ፍርደኞችን ማስተላለፍ በተመለከተ በተላኩ ረቂቅ ስምምነቶች ላይ አስተያየት መስጠት፣ ፍርደኞችን የማስተላለፍ ጥያቄዎችን ማቅረብ ከሌሎች ሀገሮች የሚቀርቡትን ተቀብሎ ምላሽ መስጠትን፣ የበይነ መንግስታት ድርጅቶች ስምምነቶች በሚፀድቁበት ሂደት ላይ ተሳትፎ ማድረግን፣ በኢትዮጵያ ላይ ለሚቀርቡ ሕግ ነክ ጥያቄዎች፣ ክሶችና አቤቱታዎች

ምላሽ መስጠት፣ አስፈላጊውን ክርክር እና ክትትል ማድረግን፣ ዓለም አቀፍ ሕግን በሚመለከት ከሀገር ውስጥ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠትን፣ በዓለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶች ላይ ወቅታዊ ሀገራዊ ሪፖርቶችን ማዘጋጀትን እንዲሁም ሌሎች ዓለም አቀፍ ትብብርን የሚመለከቱ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

**ከፌዴራል ሕጎች ተፈፃሚነት ክትትል ረገድ** የፌዴራል ሕጎች ተፈጻሚነት ክትትልና የተጠያቂነት ሥርዓት ተቀርጿል። ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የሚታዩና ክትትል የሚደረግባቸው የፌዴራል ሕጎች የትንበያ ዳሰሳ ጥናት ተከናውኖ በቀጣይ አምስት አመታት ክትትል የሚደረግባቸው የትኩረት መስክ ሕጎች እና ተቋማት ተለይተዋል፡፡ የሽያጭ ምግቦች ደህንነትና ጥራት ቁጥጥር አፈጻጸምና የሕግ ማዕቀፍ ዳሰሳ ጥናት እንዲሁም በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የግዢ፣ ንብረት አስተዳደር እና ፋይናንስ ሕጎች አፈጻጸም ዳሰሳ ጥናት ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ በጥናቶቹ የመጀመሪያ ረቂቅ ሪፖርት ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የማጽደቂያ ውይይት ተደርጓል፡፡

**ከጸረ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር አንጻር :-**

- የተለያዩ የመንግስት ተቋማትን ማለትም ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የዳያስፖራ ኤጀንሲ፣ የማዕከላዊ እስታስቲክስ ኤጀንሲ፣ ከፕላን ኮሚሽን፣ ከከተሞች ስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ፣ ከሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሚኒስቴር እንዲሁም ከዓለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት ተወካዮች በማካተት ኮሚቴ በማዋቀር ኮሚቴውም የ5ዓመት የፍልሰት አስተዳደር ስትራቴጂክ ዕቅድ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ የስትራቴጂ እቅዱ የትግበራ እቅድም ከዓለማቀፉ የፍልሰት ደርጅት ጋር በመተባበር ተዘጋጅቶ ለብሔራዊ ትብብር ጥምረቱ አባላት ውይይት ተደርጎበት ግብአት ከተሰበሰበ በኃላ ተስተካክሎ ተዘጋጅቷል። ይህ ሰነድም ለሚመለከታቸው የክልል እና የፌዴራል ተቋማት ለማሰራጨት ህትመቱ ስራ ተጀምሯል፡፡ በተመሳሳይ መል ዕቅዱ በእንግሊዘኛ ቋንቋም እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡
- አዋጅ ቁጥር 1178/2012ን ተፈጻሚ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አጋር ደርጅቶችና ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ሶስት መመሪያዎችና አንድ ዝርዝር ማስፈጸሚያ ደንብ የተዘጋጀ ሲሆን መመሪያዎቹ ላይም አራት የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ከሚመለከታቸው አካላት ግብዓት የመሰብሰብና የማዳበር ስራ ከተሰራ በኃላ ሁለቱ በብሔራዊ ምክር ቤቱ እንዲጸድቁ ከተደረገ በኃላ ቁጥር በተቋማችን የተሰጠው ሲሆን ቁጥሮቹም መመሪያ ቁ. 562/2013 እና 563/2013 ተብሎ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡
- የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር የተጀመረውን ሁሉን አቀፍ የፍልሰት ፖሊሲ ቀረፃ ዝግጅት በ11 ወራት ውስጥም ዝግጅቱ ቀጥሏል ለዚህ ስራም ከተለያዩ ተቋማት ተውጣጥቶ የተዋቀረው የባለሙያዎች ቡድንም ተገናኝቶ ስራዎች የደረሱበትን ሁኔታ የመገምገምና የመከታተል ስራ ተከናውኗል፡፡ በሪፖርት ዘመኑም ከዚህ ቀደም በሀገራችን ያሉ ከፍልሰት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ፖሊሲዎችና የህግ ማዕቀፎች በዝርዝር የመፈተሽ ስራ የክፍተት ትንተና በዓለማቀፉ የፍልሰት አማካሪ የተካሔደ ሲሆን የኢትዮጵያን የፍልሰት ፕሮፋይልን የማሻሻል ስራ ደግሞ በሀገር ውስጥ አማካሪ በኩል በመሻሻል ላይ ሲሆን ለሚዘጋጀው የፍልሰት ፖሊሲ እንደ ግብዓት እንዲሆን ሰነዱ ተዘጋጅቷል፡፡ በሌላ በኩል እስካሁን የተዘጋጁትን ሰነዶች ላይ የሚኒስትሮች ስብስብ የሆነው አብይ ኮሚቴ ጋር ቀርቦ ውይይት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ከተለያዩ አካላት በለተውጣጡ ባለ ድርሻ አካላትና

የከፍተኛ ተቋማት የዘርፉ ምሁራን በተገኙበት ውይይት ተካሂዷል፡፡ በአጠቃላይ በአሁኑ ሰዓት የፍልሰት ፖሊሲው የመጀመሪያ ቅጅ ተዘጋጅቶ ተጠናቋል፡፡ ወደ ውይይት መድረክ ከመሄዳችን በፊት መስተካከል ያለባቸውን ጉዳዮች የማስተካከል ስራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

**ከሰብዓዊ መብት ድርጊት መርሀ-ግብር አፈጻጸም አንጻር፡-**

- የተጠርጣሪዎችና ታራሚዎች የሰብዓዊ መብት አያያዝ ክትትል አስመልክቶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በሚገኙ አስሩም ክፍለ ከተሞች ያሉ የተጠርጣሪዎች ማቆያ ስፍራዎችን በመጎብኘት የተጠርጣሪዎች አያያዝ ያለበት ሁኔታ ክትትል ተደርጓል። በተጨማሪም ከሰላም ሚኒስቴር እና ከክልሎቹ ከተውጣጡ ባለሙያዎች ጋር በመሆን በተሰራ መጠነ ሰፊ ስራ በአፋር ክልል ሶስት የዞን ማረሚያ ቤቶችና ስድስት ፖሊስ ጣቢያዎች፣ በጋምቤላ ክልል ሶስት ማረሚያ ቤቶችና ሶስት ፖሊስ ጣቢያዎች፣ በአማራ ክልል ሶስት ማረሚያ ቤቶችና ስድስት ፖሊስ ጣቢያዎች፣ በሶማሌ ክልል አምስት ማረሚያ ቤቶችና አስር ፖሊስ ጣቢያዎች፣ በሀረሪ ክልል አንድ ማረሚያ ቤትና ሁለት ፖሊስ ጣቢያዎች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሁለት ማረሚያ ቤቶችና አራት ፖሊስ ጣቢያዎች፣ በሲዳማ ክልል ሁለት ማረሚያ ቤቶችና ሁለት ፖሊስ ጣቢያዎች፣ በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር 5 ፖሊስ ጣቢያዎች፣ በኦሮሚያ ክልል የምስራቅ ሀረርጌ ዞን ማረሚያ ቤትና በፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የዝዋይና ድሬደዋ ማረሚያ ቤቶች ጉብኝት ተደርጓል። በድምሩ በ21 ማረሚያ ቤቶችና 39 ፖሊስ ጣቢያዎች ጉብኝት የተደረገ ሲሆን የጉብኝቱ ግኝቶችም ለሚመለከታቸው የክልል ፖሊስና አቃቤ ህግ የስራ ኃላፊዎች በማሳወቅ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ አቅጣጫ ተሰጥቷል።

- ከዚሁ ከተጠርጣሪዎች እና ታራሚዎች አያያዝ ጋር በተገናኘ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ያለውን የሰብአዊ መብት አያያዝ ሁኔታ ለመከታተል በተለይ ደግሞ ከአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ህልፈት ጋር ተያይዞና በእስር ላይ የነበሩ ተጠርጣሪዎችን የአያያዝ ሁኔታ ለመከታተል እንዲያስችል ከክልሉ ጋር በመሆን በምስራቅና ምዕራብ ሸዋ፣ በምስራቅና ምእራብ ሐረርጌ፣ በአርሲና ምእራብ አርሲ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ በጅማ፣ ቡኖ በደሌና ባሌ ዞኖች ውስጥ በሚገኙ 28 ወረዳዎችና 10 ዞኖች ውስጥ ያሉ 44 ፖሊስ ጣቢያዎች እና 14 ማረሚያ ቤቶች ጉብኝት ተደርጓል። በጉብኝቱ ወቅት የነበረውን ግኝት ለጣቢያዎቹ የፖሊስ አመራሮች፣ በወረዳና ዞኖች ላሉ የአቃቤ ሕግ ኃላፊዎች ግብአት ተሰጥቷል እንዲሁም የጉብኝቱን መረጃው የማሰባሰብ ስራ ተሰርቷል። እንዲሁም በከፋ ዞን የቦንጋ ከተማ ማረሚያ ቤት በታራሚዎች ላይ በተፈጸመ የሰብአዊ መብት ጥሰት የታራሚዎች ህይወት አልፏል እንዲሁም የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል በሚል በቀረበ ጥቆማ መሰረት ከተደራጁ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ጋር በመሆን ወደ ስፍራው የባለሙያዎች ቡድን ተልኮ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን በማናገር፣ ሰነዶችን በመመርመር እና በማረሚያ ቤቱ ጉብኝት በማድረግ የተገኘው ግኝት ሪፖርት ተዘጋጅቷል።

- ከሰብዓዊ መብት ድርጊት መርሐ ግብር በተገኛኘ የሁለተኛው ብሔራዊ የሰብአዊ መብት ድርጊት መርሐ ግብር ትግበራ ጥቅል ሪፖርት ለማዘጋጀት እንዲያስችል የ5 አመት መርሐ ግብር አፈጻጸም ሪፖርት ከክልል እና ፌዴራል ፈጻሚ ተቋማት እንዲልኩ በደብዳቤና በስልክ ክትትል የተደረገ ሲሆን በሂደቱም ከሶማሌ ክልል በስተቀር ከአማራ፣ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ከኦሮሚያ፣ ከአፋር፣ ከጋምቤላ ከሀረሪ እና

ትግራይ ክልሎች፣ ከአዲስ አበባ እና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ከ37 የፌደራል ፈጻሚ ተቋማት የተሰበሰበውን ጨምሮ በአጠቃላይ ከ167 ተቋማት የአምስት አመት የድርጊት መርሃ ግብሩን ሪፖርቶች ለማሰባሰብ ተችሏል፡፡ ከተቋማት የተሰበሰቡትን ሪፖርቶች ወደ አንድ ቋት የማሰባሰብ እና ይህንኑ የተሰባሰበ መረጃ በማጠናቀር የተጠቃለለ አገር አቀፍ ሪፖርት ለማዘጋጀት ተችሏል። በተጨማሪም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተወጣጡ ባለሙያዎች አማካይነት የሦስተኛው ብሔራዊ የድርጊት መርሐ-ግብር ዝግጅት እንዲከናወን ተደርጎ፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በመጡ ከፍተኛ ባለሙያዎች እንዲተች እና የሰብዓዊ መብት ትምህርትን የሚመለከት አዲስ ተግባራትን የያዘ ክፍል በረቂቅ ሰነዱ በማካተት እንዲዳብር የማደረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ በረቂቅ ሰነዱ ላይም ከሲቪል ማህበራት፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ከዘጠኝ ክልሎች (ትግራይ ክልልን ሳይጨምር) እና ሁለት ከተማ መስተዳድሮች እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌደራል መንግስት ተቋማት የተውጣጡ የስራ ኃላፊዎች፣ ተወካዮች ሰነዱ ላይ አስተያየት እነዲሰጡበት ከተደረገ በኋላ የተጠቃለለው ረቂቅ ሰነድ ለብሄራዊ አስተባባሪ ቦርድ ቀርቦ እንዲተች ተደርጓል።

- ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን ዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች መከታተልን በተመለከተ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2019 ዓ.ም ሀገራችን በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ባቀረበችው ሶስተኛ የሁሉአቀፍ አገራዊ ወቅታዊ የሰብአዊ መብት አፈጻጸም ግምገማን(Universal Periodic Review) ሪፖርት ላይ የተሰጡ ምክረ ሀሳቦች አፈጻጸም ያለበትን ደረጃ መለየት አንዱ የተከናወነ ተግባር ሲሆን፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሀገራችን ተቀብላ ያጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብት ስምምነቶችንና በእነዚሁ ዙሪያ ባቀረበቻቸው ወቅታዊ ሪፖርቶች ላይ የተሰጡ ምክረ ሀሳቦችን አፈጻጸም ብሎም አጠቃላይ አገራዊ የሰብአዊ መብት አያያዝ መረጃን ለመከታተል እንዲያስችል ያለውን የሰብዓዊ መብቶች ብሄራዊ የክትትል እና የሪፖርት ስርዓትን (National Mechanism for Implementation, Reporting and Follow-up) ለማጠናከር እንዲያስችል ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች የመረጃ ቋት (National Recommendations Tracking Database) ለመገንባት በማለም ብሔራዊ የክትትል እና የሪፖርት ስርዓት ምንነት፣ አስፈላጊነት እና ይዘት ላይ የመነሻ ጽሁፍ ተዘጋጅቷል፡፡ በጠቅላይ አቃቤ ሕግ ያለውን የሰብዓዊ መብቶች ብሔራዊ ክትትል እና ሪፖርት ሥርዓት በመደገፍ እና በማጠናከር ረገድ የተ.መ.ድ የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ፅ/ቤት (OHCHR) በሚኖረው ድጋፍ ዙሪያ ምክክር ተደርጓል፡፡

## የይቅርታ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት እና የይቅርታ ውሳኔዎችን ማፀደቅ አፈጻጸም አንጻር፡-

- በበጀት ዓመቱ በይቅርታ አሰጣጥና አፈፃፀም ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 840/2006 በተደነገገው መሰረት በግልና በመንግስት አቅራቢነት በድምሩ የ1,307 ታራሚዎች የይቅርታ ጥያቄ ቀርቦ ተመርምሮ አስፈላጊው መረጃና ማስረጃ መሟላቱን በማረጋገጥ ለቦርድ እንዲቀርብ ተደርጎ ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም የቀረቡ የይቅርታ ጥያቄዎች በሙሉ ምላሽ ያገኙ ስለሆነ አፈፃፀሙ 100% ሆኗል፡፡ ይህም ከተያዘው ግብ አንፃር የተሻለ አፈፃፀም መሆኑ ታይቷል፡፡

- በሌላ በኩል ከቀረቡ 1,307 ታራሚዎች የይቅርታ ጥያቄ ውስጥ በአዋጁ የተቋቋመው ቦርድ ከህዝብ፣ ከመንግስትና ከታራሚው ጥቅም አንፃር መርምሮ በድምሩ ለ692 ታራሚዎች ይቅርታ እንዲደረግላቸው የውሳኔ ሀሳብ ለኢፌዴሪ ፕሮዝዳንት በመላክ ታራሚዎቹ የይቅርታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሲያደርግ የ615 ታራሚዎች የይቅርታ ጥያቄን የህዝብን፣ የመንግስትንና

የታራሚዎቹን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል ቦርዱ የይቅርታ ጥያቄያቸዉን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህም መሰረት ይቅርታ እንዲደረግላቸው የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ሙሉ በሙሉ በክብርት ፕሬዝዳንቷ ፀድቆ ታራሚዎቹ የይቅርታ ተጠቃሚ የሆኑ በመሆኑ አፈፃፀሙ 100% ሆኗል፡፡

- ይህ በእንዲህ እንዳለ በበጀት ዓመቱ የይቅርታ ውሳኔ ከተሰጠባቸው ታራሚዎች መካከል የ4 ታራሚዎች ይቅርታ በተሳሳተ መረጃ ላይ መሰረት ተደርጎ የተሰጣቸው መሆኑ በመረጋገጡ የ4ቱም ታራሚዎች ይቅርታ ተሰርዞ ወደ ማረሚያ እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡

## ከጥብቅና አስተዳደርና ነፃ የሕግ ድጋፍ አንጻር

- በበጀት ዓመቱ መስፈርቱን አሟልተው ለቀረቡ 264 አመልካቾች የፌዴራል የጥብቅና ፈቃድ ለመስጠት የተቻለ ሲሆን፤ ለ3255 የፌደራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች የፈቃድ እድሳት አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡
- ጠበቆች ስለሚሰጡት አገልግሎት ክትትል ከማድረግ ረገድ በተዘጋጁት ቼክ ሊስቶች መሰረት በአጠቃላይ በችሎትና በቢሮ 323 ጠበቆች ክትትል ተደርጎባቸዋል፡፡ ከተጠያቂነት አንፃር ደግሞ በጠበቆች ላይ ቀርበው ከነበሩት የዲስፕሊኒን ክሦች መካከል በ408 መዝገቦች ላይ ውሣኔ የተሰጠ ሲሆን፤ ከዚህም ውስጥ ጥፋተኛ የተባሉት 336 ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ 135 ፈቃድ በወቅቱ ባለማሳደስ በገንዝብ የተቀጡ፣ 185 ፍቃድ ባለማሳደስ ለጊዜው የታገዱ፣ በስነ ምግባር ችግር ጥፋተኛ ተብለው በገንዘብ የተቀጡ 06፣ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው 10 ሲሆኑ ክሱ አያስቀርብም የተባለባቸው 07 እና በነፃ የተሰናበቱ ደግሞ 65 ናቸው፡፡
- ጠበቆች ገንዘብ የመክፈል ዓቅም ለሌላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ነፃ የህግ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግን በተመለከተ 719 ባለጉዳዮች ከሚኖሩበት ቀበሌ የድህነት ማረጋገጫ ማስረጃ ካመጡ በኋላ ከጠበቃ ጋር እንዲገናኙ እና ጉዳያቸውን ጠበቃው እንዲይዘላቸው ተደርጓል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ሴት 458 እና ወንድ 261 ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ አገልግሎቱን ያገኙት አዛውንቶች 143 (ሴት 74፣ ወንድ 69)፣ አካል ጉዳተኞች 36 (ወ.21፣ ሴ.15)፣ ወጣቶች 160 (ወ.56፣ሴ.104) ናቸው፡፡ በአገልግሎቱ ከቀረቡት ሪፖርቶች አንፃር በፍ/ቤት ክርክር ተደርጎ በገንዘብ ደረጃ በአጠቃላይ ብር 4,879,095.00/አራት ሚሊዮን ስምስት መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺህ ዘጠና አምስት ብር እንዲያገኙ እንዲሁም በገንዘብ ያልተተመኑ በመወሰኑ የነፃ አገልግሎቱ ተጠቃሚ ተደርገዋል፡፡

## የንቃተ ሕግ፣ ትምሕርትና ሥልጠና ተግባራትን በተመለከተ

- ለንቃተ ህግ ማሳደጊያነት የሚውል በ79 ርዕሶች ላይ አጫጭር ጽሑፎችን የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፣ አብዛኞቹ ለህብረተሰቡ ንቃተ ህግ በተቋሙ ማህበራዊ ድረ ገፅ ላይ በመለጠፍ ለህብረተሰቡ ንቃተ ህግ እንዲውል ተደርጓል፡፡
- በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ተቋማት አማካኝነት በተለያዩ 45 ርዕስ ጉዳዮች ዙሪያ ለህብረተሰቡ የንቃተ ህግ ገለፃ/ትምህርት ተሰጥቷል፡፡
- በገፅ ለገፅ (ፊት ለፊት) ትምህርት ለ2000 ሰዎች ለመስጠት በእቅድ ከተያዘው ከብዙ እጥፍ በላይ ለ47196 ሰዎች በ13 ርዕሰጉዳዮች ላይ ትምህርት መስጠት ተችሏል፡፡

- ለህብረተሰቡ የንቃተ ህግ ትምህርት በብሮሸር ለመስጠት እንዲቻል በተለያዩ 4 (አራት) ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ፅሁፍ የማዘጋጀት እና በብሮሸር መልክ የማሳተም ስራ ተከናውኗል፣ ለህብረተሰቡ የማሰራጨት ስራ ተሰርቷል፡፡

- በአጠቃላይ ጽሑፎችን በማዘጋጀትና በማህበራዊ ሚዲያ አማካኝነት፣ በፊት ለፊት ስልጠና፣ በመገናኛ ብዙሃን እና በብሮሸር አማካኝነት በ113 ርዕሰ ጉዳዮች (በተለያየ ትምህርት መስጫ መንገድ የተደጋገሙ ተመሳሳይ ርዕሶችን ሳይጨምር) ላይ ለበርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች የንቃተ ህገ ትምህርት መስጠት ተችሏል፡፡

- በተጨማሪም በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ለ303 የተቋሙ መካከለኛ አመራሮች፣ 755 ዐቃብያነ ሕግ፣ እንዲሁም 1220 የአስተዳደር ሠራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ለሌሎች ተቋማት የተሰጠ ስልጠናን በተመለከተ 815 ለሚሆኑ ከፍትህ አካላት እና ሌሎች የመንግስት ተቋማት ለተወጣጡ ባለሞያዎችና አመራሮች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

**የሴቶች፣ ህጻናት እና ባለብዙ ዘርፍ ተግባራትን በተመለከተ**

- በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ለመከላከል እና ተፈፅሞ ሲገኝ ምላሽ ለመስጠት ተዘጋጅቶ የነበረውና የመፈፀሚያ ጊዜው የተጠናቀቀውን የብሄራዊ አስተባባሪ አካል ስትራቴጂክ እቅድና ድርጊት መርሃ ግብር ክለሳ በዩኒሴፍ እና በዩኤንውመን በኩል ሁለት አማካሪዎችን በመቅጠር "**በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚፈፀምን ጥቃት ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የአምስት አመት**(2014 - 2018) **ብሄራዊ ስትራቴጂክ እቅድና ድርጊት መርሃ ግብር**" ተዘጋጅቷል፡፡በየደረጃው በሚመለከታቸው አካላት ውይይት እየተደረገበት የተዘጋጀ ሲሆን ከቀጣይ አመት ጀምሮ በብሄራዊ አስተባባሪ አካል አባል ተቋማት ሀላፊዎች በይፋ ወደ ስራ በማስገባት የትግበራ ጊዜው ይጀምራል፡፡

- በሃገር አቀፍ ደረጃ ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶችና ህጻናት የተቀናጀ የፍትህና እንክብካቤ አገልግሎት የሚሰጡ ማእከላትን ወጥ አሰራርና አደረጃጀት እንዲኖራቸው ለማስቻልና አስፈላጊውን የአሰራር መመሪያ ሰነዶች ለማዘጋጀት የኢ.ፌ.ድ.ሪ ጤና ሚኒስቴር እና የሴቶች፣ ህጻናት ወጣቶች ሚኒስቴር፣ አዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን፣ ፌደራል ፖሊስ፣ አዲስ አበባ ጤና ቢሮ፣ ዩኒሴፍ ተቋማትን ባሳተፈ መልኩ ሃገር አቀፍ ጥናት ተደርጓል፡፡ በጥናቱም በሃገር አቀፍ ደረጃ የተቀናጀ የፍትህና እንክብካቤ አገልግሎት የሚሰጡ ማእከላትን ለመለየትና አጠቃላይ በማዕከላቱ ከአሰራርና አደረጃጀት እንዲሁም ከአገልግሎት አሰጣጥ አንጻር የሚታዩ ችግሮችን የለየና የመፍትሄ ሀሳቦችን አስቀምጧል፡፡የጥናቱ ውጤት ከክልልና ከፌደራል የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ግብዓት እንዲሰጡበት የማድረግና ሰነዱን የማጠናቀቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ የተጠናቀቀው ሰነድ ቅጂም በፌደራል ሆነ በክልል በሚገኙ የፍትህ እና እንክብካቤ ማዕከላት ዙሪያ የሚሰሩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡

- የኮቪድ ወረርሽን በሴቶችና ህጻናት ጥቃትን በመከላከልና ተፈጽሞ ሲገኝ ምላሽ በመስጠት ስራው ላይ የሚኖረውን ተጽእኖ ለመቀነስና የፖሊስና አቃቤ ህግና የሴቶችና ህጻናት አደረጃጀቶች እንዲሁም የፍትህና እንክብካቤ ማእከላት ራሳቸውን ከበሽታው በጠበቀ መልኩ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት የሚችሉበት አሰራር በተመለከተ የመተግበሪያ ማንዋል

በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አገልግሎቱን ለሚሰጡ ባለሞያዎች ተልኮ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

- በዩኒሴፍ በጀት ሊከናወኑ የታቀዱ የ2012 በጀት አመት ተግባራት በግዢ ሂደት መጓተት ምክንያት የበጀት መጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈ ተግባራት በዚህ አመት ማገባደጃ ላይ የተለያዩ ንጽህና በመጠበቂያ ቁሳቁሶች ግዢ ተከናውኖ ቁሳቁሶቹ በሴቶች እና ህጻናት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች የምርመራ ቡድን ፣ ለፍትህ እና እንክብካቤ ማዕከላት እና ለተቋሙ የስራ ክፍሎች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡
- በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ለሚገኙ የፍትህና እንክብካቤ ማዕከላት አገልግሎት አሰጣጥ ወጥ የአሰራር ስርዓት የሚዘረጋ ፤ የተቋማትን እና ባለሙያዎችን ሀላፊነት በግልጽ የሚደነግግ፤ መረጃ አያያዝ እና ስርጭትን በተመለከተ የሚያስቀምጥ የአሰራር ስርአት ማኑዋል ዳይሬክቶሬቱ ከጤና ሚኒስቴር፤ የሴቶች ህጻናት ወጣቶች ሚኒስቴር፣ ከአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን፣ ከፌደራል ፖሊስ፣ ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮና ከዩኒሴፍ ጋር በጋራ በመሆን ማዘጋጀት ተችሏል፡፡
- የኮቪድ ወረርሽኝ በሴቶችና ህጻናት ጥቃትን በመከላከልና ተፈጽሞ ሲገኝ ምላሽ በመስጠት ስራ ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ ለመቀነስና ባለሞያዎች ራሳቸውን በጠበቀ መልኩ አገልግሎቱን እንዲሰጡ ለማስቻል ከUNWOMEN በተገኘ ድጋፍ 1.1 ሚሊየን ብር በላይ የሚገመት የተለያዩ ንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችና በአዲስ አበባና በድሬደዋ ለሚገኙ ለሁሉም የአቃቤ ህግ፣ የፖሊስ ተቋማትና ለ4 የፍትህና እንክብካቤ ማዕከላት ድጋፍ ተደርጓል፡፡በተጨማሪም ለክልሎች ድጋፍ ለማድረግ ዳይሬክቶሬቱ ለUNWOMEN ኮቪድ ስርጭት ለመከላከል የሚውሉ የማቴሪያል ድጋፍ ጥያቄ መሰረት የተገዙትን የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች(2 ሚሊየን ብር) በክልል የቢሮዎች አማካኝነት በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ ቤኒሻንጉል፣ ጋምቤላ፣ አማራ ፣ በሚገኙ ክልልሎች እና ድሬደዋ መስተዳደር ለሚገኙ የፍትህ እና እንክብካቤ ማዕከላት ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- በሁለት ዙር 70 ለሚሆኑ በፍትህና እንክብካቤ ማዕከላት እና በፖሊስ መመሪያ የሚሰሩ የስነልቦና ባለሞያዎች፣ አቃቢያነ ህጎች እና ኬዝ ማኔጀሮች፣ የህክምና ባለሞያዎች እና መርማሪ ፖሊሶች burnout and stress management፣ team bulding እና medcolegal (የህክምና ምስክር አጻጻፍ ይዘት) ላይ የሶስት ቀናት ስልጠና እንዲያገኙ ተድርጓል፡፡
- የፌደራል አገልግሎትን ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ከማድረግ በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አንጻር ያለበት ሀላፊነት መሰረት በማደረግ ዳይሬክቶሬቱ በ2012 መጨረሻ የተሰራ ጥናት መሰረት የታዩ ክፍተቶች መሻሻል እንዲችሉ አቅጣጫ እንዲሰጥበት ለሚመለከታቸው አመራሮች የትኩረት ነጥቦቹ ተለይተው በድጋሚ እንዲያውቁት የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

**የሕግ ኦዲት እና ኢንስፔክሽን በተመለከተ፡-** በጀት ዓመቱ ጠቅላላ 8423 የውሳኔ ግልባጭ የቀረቡ ሲሆን 6721 (79.7%) የተመረመረ ሆኖ 1704 (20.2%) ለቀጣይ በጀት አመት ዞሯል፡፡ ከተመረመሩት 6721 የውሳኔ ግልባጮች ውስጥ 6647 (98.8%) ውሳኔዎች መጽናታቸው በየደረጃው የሚሰጡ የዐቃብያነ ሕግ ውሳኔዎች የተሻላ ጥራት ያላቸው መሆኑን አንዱ አማላካች ነው፡፡

**የሰው ሀይል አስተዳደርን በተመለከተ፡-**

**በአስተዳደር ዘርፍ ያለው የሰው ኃይል ብዛት** ወንድ 290 ሴት 509 በድምሩ 799 ሠራተኞች ሲሆኑ ይህም በቀድሞ አደረጃጀት 69.53% ማድረስ ተችሏል፡፡ የኮንትራት ሰራተኞች 4 ሴት እና 2 ወንድ በድምሩ 6 ሰራተኞች በተቋሙ በስራ ላይ ይገኛሉ።

**ዐቃቤ ህግ ያለው የሰው ኃይል ብዛት፡-** በጠቅላላው 745 ዐቃቤ ህግ በስራ ላይ ያለ ሲሆን የፆታ ስብጥሩም ሲታይ 30% ሴት እና 70% ወንድ ናቸው፡፡ በበጀት አመቱ በስራ ክፍሎች ይታይ የነበረውን ኢፍታዊ የባለሙያ ስርጭት ለማስተካከል የባለሙያ ማመጣጠን ስራ የተሰራ ሲሆን በዚህም በስራ ክፍሎች ከ57% እስከ 140% ድረስ ያነበረውን ልዩነት በማጥበብ ወደ ተቋማዊው አማካኝ ማለትም ከሚያስፍልገው ባለሙያ አንፃር 88.58% አካባቢ በየስራ ክፍሉ ባለሙያ እንዲሟላ የማድረግ ስራ ተሰርቷል።

በስራ ላይ ያሉ ዐቀብያነ ሕግ ለፈጸሙት የስነ-ምግባር ጥሰት በጉባኤው ክስ ቀርቦባቸው ተጠያቂነትን ለማስፍን እየተሰራ ሲሆን በበጀት አመቱ 6 ዐቃብያነ ሕግ ላይ የዲስፕሊን ክስ ቀርቦባቸው 2ቱ ባለሙያዎች ከፈፀሙት የዲስፕሊን ጥፋት ክብደት አንፃር ከስራ እንዲሰናበቱ በዐቃብያነ ህግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሲሆን ባለሙያዎቹ በጉባኤው ውሳኔ ላይ በመደኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ጠይቀውበት ፍርድ ቤቱ የጉባኤውን ውሳኔ አፅንቶታል።

**ዘመናዊ አሰራር እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ**

- ☞ የወንጀል ምዝገባ አስተዳደር ሥርዓት የመረጃ ቋት(CRMS) የወንጀል ሪከርዶችን ከፖሊስ እስከ ዐቃቤ ሕግ እንዲሁም እስከ ፍርድ አሰጣጥ ድረስ ያለውን መዝግቦ የሚይዝና ውጤታማ እና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ ልውውጥ በፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግና በፌደራል ፖሊስ እንዲሁም አዲስ አበባ ፖሊስ መካከል እንዲኖር የሚያስችለውን የመረጃ ቋት ግንባታ በማጠናቀቅ የሙከራ ትግበራ ሂደት ላይ ይገኛል።

- ☞ በፌደራል በአዲስ አበባ እና በድሬደዋ የመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ ሥራላይ የሚውሉ መመሪያዎችን ለኅ/ሰቡ በቴክኖሎጂ በመታገዝ ተደራሽ የሚደረግበትን የመረጃ ቋት ግንባታ ተከናውኖ መመሪያዎቹን ለኅ/ሰቡ ተደራሽ ማድረግ ተችሏል።

- ☞ የወንጀል መዛግብት ወደ ሶፍትኮፒ በመቀየር ሂደት ውስጥ በ2013 በጀት ዓመት ከተከፈቱ መዝገቦች ውስጥ 15405 ያህል መዝገቦችን ወደ ሶፍት ኮፒ መቀየር ተችሏል።
- ☞ የውጤት ተኮር ምዝገባ አስተዳደር ሥርዓትን ከኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር ጋር በመተባበር የመረጃ ሥርዓቱ ግንባታ ተጠናቋል።

- ☞ የመዝገብ አኖኖዝ ሥርዓት በተመለከተ በቴክኖሎጂ ለማዘመን የሚረዳ የመረጃ አኖኖዝ ሥርዓት ማልማት ሥራ ተጠናቋል።

- ☞ በተቋሙ ውስጥ የሚኖረውን የመረጃ ልውውጥ በአውትሉክ የማከናወን ሥራ ተከናውነዋል።

# የተግባቦትና ገፅታ ግንባታን ማሻሻል

**የተከናወኑ ተግባራት፡-**

**ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ከማሰራጨት አንጻር፡-**

- መንግስት እና ለግል ሚዲያዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በበጀት ዓመቱ ውስጥ 40 ጋዜጣዊ መግለጫ እና ዜና መግለጫዎች ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም ከ150 በላይ የአካል እና የሥልክ ቃለ ምልልሶችን /INTERVIEWS/ በመሥራት በዜናዎቻችን አካተን ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ተችሏል፡፡
- ሕብረተሰቡን ስለወንጀል አስከፊነት ሊያስተምሩ የሚችሉ 323 የተቋም እና የችሎት ዜናዎች በማዘጋጀት ለሚዲያ ግብዓት እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ የተቋሙን የተለያዩ ተከታታይ መረጃዎች በመዘገብ ለሕብረተሰቡ ተደራሽ የሚያደርግ የሚዲያ ቲም (COROSPONDENTS) ከ13 የተለያዩ የሚዲያ አካላት የተውጣጡ ባለሙያዎች በማዘጋጀት አብሮ በመስራት የተሻለ የሚዲያ ግንኙነት ለመፍጠር ተችሏል፡፡ 55 በጽሁፍ እና በተንቀሳቃሽ ምስል የታገዙ የንቃተ ህግ ትምህርቶችን በማህበራዊ ገጾች ተጋርቷል፡፡
- ለሕብረተሰቡ የተቋሙን ተልዕኮ የሚያስገነዝቡ እና የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መመሪያና ደንብ አስመልክቶም 17 መልዕክቶች ተቀርጸው ተደራሽ ተደርገዋል፡፡
- ኮቪድን ለመከላከል የወጣውን መመሪያ ቁጥር 30/2013ን በተመለከተ ከ5 ሚዲያዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ተሰጥቧል፡፡
- በ2013 በጀት አመት እቅድ አፈጻጸም በተለያዩ ተቋማዊ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ የተደረጉ የ76 ውይይት መድረኮችና በተለያዩ ተቋማዊና አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የተሰጡ መግለጫዎች የቪዲዮ ቀረጻ እና ፎቶ ማንሳትሥራ ተከናውኗል፤ ሁሉም ዘርፎች በምክትል እና በዘርፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች አማካኝነት የየሩብ ዓመቱን አፈጻጸም አስመልክተው ማብራሪያ እንዲሰጡ በማድረግ የማጋራት ስራ ተሰርቷል፡፡ የፍትሃ ብሄር እና ልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዘርፍ እና የህግ ጉዳዮች ዘርፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የስድስት ወር የዘርፉን ዕቅድ አፈጻጸም በተመለከተ ማብራሪያ እንዲሰጡ ተደርጎ በማህበራዊ ድረ-ገጽ ላይ ተጭኗል፡፡
- በቼክ እና አራጣ ዙሪያ፣ በክርክር ማቋረጥ የህግ ማዕቀፍ እናዲሁም የዐቃቤ ህግ የወንጀል ምርመራ እና ማስቀጣት ፍሰት እንዲሁም በጥብቅና እና ነጻ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ዙሪያ ዶኩሜንታሪ ቪዲዮዎችን በራስ አቅም ማዘጋጀት ተችሏል፡፡
- በጽሁፍ ከሚጋሩ ዜናዎች በተጨማሪ በድምጽ እና ምስል ሽፋን ቅንብር የሚሰራጩ ሳምንታዊ ዜናዎችን የማጋራት ስራዎች ተሰርቷል፡፡ የተቋሙን ዓመታዊ መጽሄት ጽሁፍ በማጠናቀቅ ለግዢ ስራ ክፍል የማስረከብ ስራ ተሰርቷል፡፡
- የተግባቦትና የግልፀኝነት አሰራርን ውጤታማ ለማድረግ በሀብት ማስመለስ ዳይሬክቶሬት ነጻ የጥቆማ መቀበያ 6044 መንገዶችን በመክፈት ጠቆሚዎችች ጥቆማ የሚሰጡበትን ስልክ መስመሮች ተዘጋጅተው ስራ ላይ ውለዋል፤

- ☞ **የማህበራዊ ሚዲያ ተከታዮችን በተመለከተ፦** በ4ኛ ሩብ ዓመት ብቻ ፔጁን LIKE ያደረጉትን 5977 ሰዎች ጨምሮ በአጠቃላይ በአመቱ መጨረሻ የፌስቡክ ገጻችን ወዳጆች 164,323 ደርሰዋል፡፡ እንዲሁም 168,744 ተከታዮች ፔጃችንን ተቀላቀለዋል፡፡
- ☞ በተቋሙ በዌብ ሳይት እና የትዊተር ገጽም መረጃዎች እና ዜናዎች የተጋሩ ሲሆን 55 የተመረጡ የተቋሙ ዜናዎች በትዊተር ገጹ እንዲጋራ ተደርጓል፡፡ የትዊተር ተከታዮችም 12,800 መድረስ ችሏል፡፡

## 3. የኢፌዴሪ የ2014 በጀት ዓመት እቅድ

### 3.1. የእቅዱ ዋና ዓላማ

ፍትህ ሚኒስቴር በህግ የተሠጠውን ሕገ መንግስቱንና ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በማክበርና በማስከበር የሕግ የበላይነትን የማረጋገጥ ሐላፊነቱን በብቃት እንዲወጣ ማስቻል፡፡

### 3.2. የእቅዱ ዝርዝር ዓላማዎች

1) ህገ መንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ማስከበር፣
2) የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣
3) የወንጀል ህግን ማስከበር፣
4) የፌዴራል መንግስቱንና የህዝብን ፍትሐብሔር ጥቅም ማስጠበቅ

### 3.3. በዝግጅት ምዕራፍ የሚከናነወኑ ዋና ዋና ተግባራት

በዝግጅት ምዕራፍ ያለፈውን በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ከሁሉም የውስጥና ከሚመለከታቸው የውጭ ባለድርሻ አካላት ጋር በመገምገም በቀጣይ በጀት ዓመት በተቋሙ መሪ ዕቅድ ላይ መግባባት ለመድረስ የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

**ከእቅድ ዝግጅት አንፃር፡-**

- ❖ የ2013 እቅድ አፈጻፀም ከተቋሙ መላው ሠራተኞችና የህዝብ ክንፍ ተወካዮች ጋር ከባለድርሻ አካለት ጋር መገምገም፣
- ❖ ከተቋሙ 2014 መሪ እቅድ በመነሳት ሁሉም የስራ ክፍሎች የየሥራ ክፍላቸውን በወቅቱ እንዲያወጡ ማድረግ፣
- ❖ እስካሁን የተሰጡ የተለያዩ አቅም ግንባታ ስልጠናዎች ካመጡት ውጤት በመነሳት የአመራሩንና የፈፃሚውን አቅም (ስነ-ምግባር፣ ክህሎት፣ ዕውቀት) ለመገንባት የሚያስችል የሥልጠና ዕቅድ ማዘጋጀት ተግባራዊ በማድረግ፣
- ❖ እቅዱን ለማስፈፀም የሚያስፈልግ ግብዓትን ለማሟላት የግዥ ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ተግባር መግባት፣

**ፈፃሚን ከማዘጋጀት እና የእቅድ ኦረንቴሽን ከመስጠት አንፃር፡-**

በበጀት ዓመቱ ተቋማዊ መሪ እቅድ ላይ በየደረጃው ለሚገኝ መካከለኛ አመራሩ፣ የፈፃሚውንና እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ኦረንቴሽን በመስጠት ለዕቅዱ ስኬት ሁሉም የራሱን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ግንዛቤ መፍጠር፣

## 3.4. በትግበራ ምዕራፍ የሚከናወኑ ተግባራት

### 3.4.1. ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች (Strategic Themes)

ፍትህ ሚኒስቴርበ2014 በጀት ዓመት ውስጥ የሚተገበሩ ግቦችና የሚከናወኑ ተግባራት በተቋሙ አምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ (2013-2017) የተለዩ ሶስት ተቋማዊ ስትራቴጂካዊ መስኮች እና ውጤቶች መሰረት አድርጎ ሲሆን እነዚህም ፡-

| ተ.ቁ. | ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ /Strategic Themes/ | ስትራቴጂያዊ ውጤት /Strategic Result/ |
|---|---|---|
| 1 | የላቀ የህግ ተፈፃሚነት | በተረጋገጠ የሕግ የበላይነት ያደገ ተቋማዊ የህዝብ ዓመኔታ |
| 2 | የላቀ የፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ | በአገልግሎቱ የተገልጋይ እርካታ |
| 3 | የተቋም ግንባታ | የማስፈፀም አቅሙ የተገነባ የዓቃቤ ህግ ተቋም |

**የትኩረት መስኮች መግለጫ**

**የላቀ የሕጎች ተፈፃሚነትን በተመለከተ፡-** ከተቋቋመበት አላማዎች መካከል የህጎችን ተፈጻሚነት በማረጋገጥ የህግ የበላይነትን ማስፈን አንዱ እና ዋነኛው ነው። የሕግ የበላይነት ማለት ማናቸውም የመንግሥት አካል፣ ባለሥልጣን፣ የግልም ሆነ የመንግሥት ድርጅት እንዲሁም ማናቸውም ግለሰብ የአገሪቱን ሕግ ማክበር እንዳለበትና የትኛውም ወገን ከሕግ በታች እንጅ በላይ እንዳልሆነ የሚያመለክት ሲሆን ከዚህም በመነሳት የላቀ የህጎች የተቋሙ የትኩረት መስክ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

**የላቀ የፍትህ አገልግሎት ከመስጠት ረገድ፡-** የኢ.ፌዴሪ በሕግ ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች አንጻር በርካታ አገልግሎት የሚሰጣቸው ተገልጋዮች አሉ፡፡

እነዚህ ተገልጋዮች እንደየአገልግሎቱ ዓይነት እና ባህሪ የተለያዩ ፍላጎቶች ያሏቸው ቢሆንም በጥቅል ሲታይ ግን ተቋሙ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ፍትሐዊና ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ፣ ጥራት ባለው፣ በአነስተኛ ወጪ (ያለውጣ ውረድ) እንዲሁም በቅርበት እንዲሰጣቸው ይፈልጋሉ፡፡በመሆኑም በአጠቃላይ ተገልጋዮች ከተቋሙ ተግባርና ኃላፊነት ጋር በተገናኘ አገልግሎት በሚጠይቁበት ወቅት አላስፈላጊ የሆኑ የቅብብሎሽና የምልልስ አሠራሮችን በመቀነስ፣ ለተገልጋዮች እሴት የማይጨምሩ ሥራዎችን በማስወገድ፣ ሥራዎቹ እሴት የሚጨምሩ ቢሆን እንኳን በተፋጠነ እና በጥራት እዲሠሩ በማድረግ፣ ለፈጻሚዎች ተጨማሪ ኃላፊነቶችን ተጠያቂነት ጋር በመስጠት፣ በአነስተኛ ወጪና በተፋጠነ መልኩ ያለ እንግልት ተገልጋዮች

የፍትሕ አገልግሎቱን እንዲያገኙ ማስቻል አስፈላጊ በመሆኑ የላቀ የፍትህ አገልግሎት መስጠት የተቋሙ የትኩረት መስክ ይሆናል፡፡ በዚህ መስክ ላይ አተኩሮ መሥራቱ ተቋሙ የሚሰጣቸው የፍትህ አገልግሎቶች ጥራት ያላቸው፣ ተደራሽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆኑ በማድረግ ተቋሙ ራዕዩንና ተልዕኮውን እንዲወጣ ከማስቻሉም በላይ የተገልጋዩን እርካታ ያረጋግጣል።

ሶስተኛው የትኩረት መስክ የተቋም ግንባታ ሲሆን የስትራቴጂክ አመራርና የማስፈፀም አቅም ማሳደግ ተቋሙን ብቃት ባለው በሰው ኃይል በማጠናከር፣ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን በማሟላት፣ ውስጣዊ አሰራርና አደረጃጀቶችን በማሻሻል የሕግ የበላይነትን የሚያከብርና የሚያስከብር፣ ቀልጣፋና ፍትሐዊ የፍትህ አገልግሎቶችን የሚሰጥ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅሙ የተገነባ የዐቃቤ ሕግ ተቋም መገንባት አስፈላጊ በመሆኑ የተቋም ግንባታ በስትራቴጂክ ትኩረት ዘመኑ እንደ አንድ የትኩረት መስክ ተይዟል፡፡ ከላይ የተመላከቱ ስትራቴጂክ መስኮችን እናከታች የተቀመጡ ስትራቴጂክ ግቦች መነሻ በማድረግ በበጀት ዓመቱ የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካት ርብርብ ይደረጋል፡፡

ስትራቴጂያዊ ግቦች/strategic Objectives/

ለሁሉም የተቋሙ የትኩረት መስኮች የተጠቃለሉ ስትራጂያዊ ግቦች በእያንዳንዱ እይታ ውስጥ ስትራቴጂክ ግቦችን እንደሚከተለው ተካተዋል፡፡

| ዕይታ | ስትራቴጂክግብ |
|---|---|
| ተገልጋይ | 1) የተገልጋዩን እርካታ ማሳደግ |
| | 2) የህብረተሰብ/ ሲቪል ማህበረሰብ/ ተሳትፎ ማሳደግ |
| ፋይናንስ | 3) የሃብት አጠቃቀም ውጤታማነት ማሻሻል |
| የውስጥ አሰራር | 4) የወንጀልና የወንጀል ስጋትን መቀነስ |
| | 5) የመንግስትና የህዝብ ጥቅምን የማስጠበቅ ውጤታማነትን ማሻሻል |
| | 6) የሰብዓዊ መብት ማክበርና ማስከበር አፈፃፀምን ማሻሻል |
| | 7) የህግ ተገዥነትን ማሳደግ |
| | 8) የአገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽነትን ማሳደግ |
| | 9) የፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማሳደግ |
| | 10) የህግና ፍትህ ማሻሻያ ስራዎችን ውጤታማነት ማሻሻል |
| | 11) በአገልግሎት አሰጣጥ አካታችነትን ማሳደግ |
| | 12) የትብብርና አጋርነትን ማሳደግ |
| መማማርና እድገት | 13) የስትራቴጂክ አመራር ብቃት ማሳደግ |
| | 14) የመረጃ አያያዝ፣ አጠቃቀምንና ስርጭትን ማሻሻል |
| | 15) ዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ |
| | 16) የተግባቦትና ገፅታ ግንባታን ማሻሻል |

ስለዚህ ከላይ የተገለፁ ስትራቴጂያዊ ግቦችን መሰረት በማድረግ በ2014 በጀት ዓመት የሚተገበሩ ዋና ዋና ግቦችና ስትራቴጂክ ተግባራት በአራቱ እይታ አንጻር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## ከተገልጋይ እይታ አንፃር

### ግብ 1 የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ፣

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- የተገልጋዩንና የህብረተሰብ የእርካታ ደረጃ ለማወቅ የሚያስችል የመለኪያ ስርዓት መቅረፅ፣
- ተቋማዊ የአገልግሎት አሰጣጥ መለኪያ ስታንዳርድ (ጥራት፣ ቅልጥፍና፣ ተደራሽነትና ወጪ) ማሻሻልና መተግበር፣
- ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት በመስጠት የተገልጋዩና የህብረተሰቡን እርካታ ወደ 80% ማሳደግ፣
- በስታንደርድ መሰረት የሚሰጡ አገልግሎቶች ምጣኔን 96.5% ማድረስ፣
- የቅሬታና አቤቱታ መስተንግዶን ማሻሻልና ለቅሬታ ምላሽ የመስጠት ምጣኔን 77% ማድረስ፣
- በዓመት አራት ጊዜ ከተገልጋይ አስተያየት መሙያ ቅፅ ላይ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ የተገልጋዩን የእርካታ ደጃ መመዘን፣

**የሚጠበቅ ውጤት- ያደገ የህብረተሰብና የተገልጋይ እርካታ፣**

### ግብ 2 የህብረተሰብ/ የሲቪል ማህበረሰብ/ ተሳትፎን ማሳደግ

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- የሲቪል/ሙያ/ ማህበራት ተሳትፎ ማበልጸግያ ፕሮግራም መንደፍና መተግበር መጀመር፣
- የግሉ ዘርፍ በፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ ስለሚሰሳተፍበት መስክ ማጥናት፣
- ለተቋሙ ዕቅድ መሳካት ቁልፍ ድርሻ ያላቸው የህዝብ አደረጃጀቶች መለየትና ከሲቪል ማህበረሰቡ ጋር አራት(4) መድረኮች ማዘጋጀት፣
- ከሲቪል ማህበረሰቡ ጋር በጋራ የተሚሰሩ ስራዎች መለየትና የጋራ ዕቅድ በማውጣት መተግበር፣
- 2 ስራዎች ጋር በጋራ ማከናወን፣ ለፍትሕ ስርዓቱና ለተቋሙ ስትራቴጅያዊ ዕቅድ መሳካት ቁልፍ ድርሻ ያላቸው የህዝብ አደረጃጀቶች መለየትና ተሳትፎ ማጠናከር፣
- ከሲቪል ማህበረሰቡ ጋር አራት(4) የውይይትና የምክክር መድረኮችን ማካሄድ፣
- የሚጠበቅ ውጤት፡- ያደገ የህብረተሰብ/ የሲቪል ማህበረሰብ/ ተሳትፎ፣

## ከፋይናንስ እይታ አንፃር

### ግብ 3 የሐብት አጠቃቀም ውጤታማነት ማሻሻል

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- የበጀትና የፋይናንስ አስተዳደር አሰራር ሕግ የተከተለና የዋና ኦዲተር ግኝት ከአጥጋቢ በላይ

(ከነቀፌታ የፀዳ) እንዲሆን መስራት፣

- ☞ የፕሮግራም በጀቲንግ፣ ያልተማከለ የፋይናንስ አስተዳደር ስርአትና የአቅርቦት ሁኔታ ጥናት መተግበር፣
- ☞ የሐብት የማፈላለግና የማስተዳደር የስራ ክፍል መዋቅርና የሰው ሐይሉን መልሶ ማደራጀት፣
- ☞ የሐብት ምንጮችን ማስፋት፣
- ☞ የፕሮጀክቶች አፈፃፀም ውጤታማነት ክትትልና ድጋፍ ስርአት መዘርጋት፣
- ☞ ውስጥ ኦዲትና ቁጥጥር ስርዓቱ ማጠናከር፣
- ☞ ጊዜ የውስጥ ኦዲትን ማካሄድ
- ☞ የተሸከርካሪና የነዳጅ አጠቃቀም ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፣
- ☞ በተቋሙ ዉስጥ መለስተኛ የተሸከርካሪና የአይቲ መገልገያ መሳሪያዎች የጥገና ስርዓት ማደራጀትና መተግበር፣
- ☞ የተማከለ የህትመትና የፎቶ ኮፒ አገልግሎት ማደራጀትና መተግበር፣
- ☞ የፕሮግራም በጀትን በወቅቱና በጥራት የማዘጋጀት ስራን 100% መፈጸም፣
- ☞ ከመንግስት የሚመደበዉን በጀት በ10 % እንዲያሳድግ መስራት፣
- ☞ የተቋሙን አላማ በማስፈፀም ሊያግዙ ከሚችሉ አለም አቀፍ ተቋማት 15 ሚሊዮን ብር የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ማሰባሰብና መጠቀም፣
- ☞ ከመንግስት ለተቋሙ የተመደበዉን በጀት አጠቃቀም ውጤታማነት ወደ 95% ማሳደግ፣
- ☞ የፕሮጀክት አፈጻጸም ምጣኔን ወደ 82% ማድረስ፣
- ☞ የኦዲት ግኝቶች ላይ ማስተካከያ ማድርግና ምክረ ሃሳቦች በተሟላ መተግበር፣ 100% ተጠያቂነትን ማረጋገጥ

**የሚጠበቅ ዉጤት፡ ዉጤታማ የበጀትና የፕሮጀክት አፈፃፀም፡፡**

## ከዉስጥ አሰራር እይታ አንፃር

**ግብ 4 የወንጀልና የወንጀል ስጋትን መቀነስ**

**ንዑስ ግብ 4.1. የወንጀል መከላከል አቅምን ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- ☞ የወንጀል መከላከል ስትራቴጂ ፈፃሚ አካላት ጋራ የትብብር መድረክ መፍጠርና ቀጣይ የግንኙነት ስርዐት መቅረፅ፣

- የወንጀል መከላከል ስትራቴጂውን አፈፃፀም የሚከታተልና ሴክተር ፈፃሚዎችን የሚያስተባብር አደረጃጀት መፍጠር፣
- ወንጀልና የወንጀል ስጋት አካባቢዎችን፣ የወንጀል አይነትና ወንጀል ፈፃሚዎችን መለየት የሚያስችል ስርዓት መርዘጋትና መተግበር፣
- የወንጀል መከላከል የሚረዱ 2 ፕሮግራሞች መንደፍና ማስተግበር፣
- በወንጀል መከላከል ለሚሳተፉ 2000 ፈፃሚ አካላት ስልጠና መስጠት፣
- ወንጀልና የወንጀል ስጋት ስለመቀነሱ አንድ ጥናት ማካሄድ፣
- ከህብረተሰቡ ለተዉጣጡ 2 ሚሊዮን ሰዎች በተለያዩ መድረኮች የወንጀል መከላከል ንቃተ ህግ ትምህርት መስጠት፣
- በወንጀል መከላከል ዙሪያ 2 የጥናትና የምርምር ስራ መስራትና ማሰራጨት፣
- በወንጀል መከላከል አስፈፃሚ አካላት ጋር 2 መድረክ በመፍጠር ምክክር ማድረግ፣
- በአመት ሁለት ጊዜ የወንጀል መከላከል መረጃ በማሰባሰብ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ፣

**የሚጠበቅ ዉጤት፡- ያደገ የወንጀል መከላከል አቅም፡፡**

**ንዑስ ግብ 4.2. የህገወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከል አቅምን ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- የህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከልና ቁጥጥር ሀገራዊ አደረጃጀት ማጠናከር፣
- ሀገራዊ የፍልሰት ፖሊሲ ማስተግበር የሚያስችል ህግ መቅረፅና አተገባበሩን መከታተል፣
- የህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የተጋላጭነት ሁኔታ ከቦታ፣ ከተጎጂዎችና ከአዘዋዋሪዎች አንጻር ጥናት ማካሄድ፣ የተጋላጭነት ካርታ ማዘጋጀትና ለተጠቃሚዎች ማዳረስ፣
- የተሻሻለው አዋጅ የአፈፃፀም ደንቦችና መመርያዎች ማውጣትና መተግበር፣
- የአዋጁ ሃገራዊ ተፈፀሚነት ለማሳደግ በአዋጁና አፈፃፀሙ ዙርያ ሃገራዊ ንቅናቄ መፍጠር
- ህጋዊ የሰዎች ዝዉዉር ለማበረታትና ስራ ስምሪትን ለማሻሻል የወጡ የህግ ማዕቀፎች አተገባበር መከታተል፣
- የህገወጥ የሰዎች ዝዉዉር ለመከላከልና ለመቆጣጠር አለምአቀፍ ትብብርን ማጠናከር፣

**የሚጠበቅ ዉጤት፡- ያደገ የህገወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከል አቅም፡፡**

**ንዑስ ግብ 4.3፡- የወንጀል ህግ አፈፃፀም ውጤታማነት ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- ልዩ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች [1] መለያ ስርአት መቅረፅና ቅድሚ በመስጠት

መፈፀም፣

- ለትርጉም የተጋለጡ ህጎችን በጥናት መለየትና ተገማች ዉሳኔ ለመስጠት የሚረዳ ጋይድ ላይን መቅረፅና መተግበር (ጉቦ መስጠት ስለማስረዳት፣ በእምነት ማጉደል ንብረት መመለስ…)
- ወንጀል መዛግብት ምርመራና ክስ ዉጤታማነት የሚያሳድጉ (የሚወዘፉ፣ የሚመለሱና የሚንጠባጠቡ የወ/ክሶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ) አሰራርና አደረጃጀቶች መቀርፅና መተግበር፣
- ተጠርጣሪን፣ ተከሳሽና ምስክርን ፍርድ ቤት ለማቅረብ የሚያስችል ግንዛቤ፣ አሰራርና አደረጃጀት መቅረፅና መተግበር፣
- ቀላልና ዘመናዊ የወንጀል የጥቆማ፣ ክስና አቤቱታ አቀባበል ስርዓት መዘርጋት፣
- ለፖሊስ ሪፖርት ከተደረጉት የወንጀል አቤቱታና ክሶች ዉስጥ 85% ወደ ምርመራ እንዲገቡ ማድረግ፣
- የወንጀል ምርመራ መዛግብት ዉሳኔ የመስጠት (ማጥራት) ምጣኔ 82% ማድረስ፣
- በምስክርና ተከሳሽ አለመገኘት ምክንያት የሚቋረጡ የክስ መዛግብት መንጠባጠብ ምጣኔ 1.5% እንዳይበልጥ ማድረግ፣
- የወንጀል ክሶችን የመርታት ምጣኔን አፈጻጸምን ወደ 94% ማሳደግ፣
- የጥፋተኝነት የድርድር ስኬት ምጣኔን 93% ማድረስ፣
- በዐቃቤ ህግ የይግባኝና ሰበር ክርክር መርታት ወደ 65% ማሳደግ፣
- በተከሳሽ የሚቀርቡ የይግባኝና ሰበር ክርክር መርታት ምጣኔ 97% ማሳደግ፣
- የህብረተሰብ ግዴታና ከእስር ዉጪ አማራጭ የቅጣት አፈፃፀም መተግበር የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ፣ አሰራርና አደረጃጀት መቅረፅና መተግበር፣
- በፍርድ ቤት ከሚሰጡ የገንዘብና የእስራት ቅጣት ዉስጥ 82% የሚሆኑትን ማስፈፀም፣
- የወንጀል ህግ አፈፃጸም ዉጤታማነት በወንጀልና ወንጀል ስጋት በመቀነስ ያመጣዉን አንድ ፋይዳ ጥናት ማካሄድና የማሻሻያ እርምጃ መዉሰድ፣

**የሚጠበቅ ዉጤት፡- ያደገ የወንጀል ህግ አፈፃፀም፡፡**

**ንዑስ ግብ 4.4. በወንጀል የተገኘ ሃብት የማስመለስ ውጤታማነት ማሳደግ የሚከናወኑ ተግባራት**

- በወንጀል ተግባር በሀገር ዉስጥና ከሀገር ዉጪ የተደበቀ ሀብት
- ለማሳገድና ለማስመለስ የሚያስችል አሰራርና አደረጃጀት መፍጠርና
- መተግበር፣

- ☞ የሐብት ምርመራ መዛግብት መርምሮ የማጠናቀቅ ምጣኔ 90% ማድረስ፣
- ☞ የሐብት ምርመራ መዛግብት ላይ ውሳኔ የመስጠት አፈፃፀም 95% ማድረስ፣
- ☞ በወንጀል የተገኘ በውጪ የታገደ ሐብት 51% ማስመለስ፣
- ☞ የሐብት ማስመለስ ክስ የተመሰረተባቸው መዛግብት የመርታት/ሀብት የማስመለስ ምጣኔ 95% ማድረስ

**የሚጠበቅ ዉጤት፡- ለመንግስት ገቢ የተደረገ በወንጀል የተገኘ ሀብት፣**

**ንዑስ ግብ 4.5. የይቅርታ አመክሮ አፈፃፀም ክትትልና ውጤታማነት ማሻሻል፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- ☞ የይቅርታ፣ አመክሮ፣ ገደብና ከእስር ዉጪ አማራጭ ቅጣቶች አፈፃፀም ክትትል ማድረግ የሚያስችል አሰራርና አደረጃጀት መቅረፅና መተግበር፣
- ☞ የይቅርታ ጥያቄ ላቀረቡ ታራሚዎች በተቀመጠው የጊዜ ስታንዳርድ መሰረት 100% ምላሽ መስጠት፣
- ☞ የይቅርታ ውሳኔ ሃሳብ
- ☞ የማፀደቅ ምጣኔን 90% ማድረስ፣
- ☞ የወንጀል ቅጣት አፈፃፀምን /በተለይም የሞት ቅጣት/ ክትትል አሰራር መቅረፅና መተግበር፣

**የሚጠበቅ ዉጤት፡- ያደገ ታረመዉ ይቅርታ የተደረገላቸዉ ታራሚዎች፣**

**ግብ 5. የመንግስትና የህዝብ ጥቅምን የማስጠበቅ ውጤታማነትን ማሻሻል**

**ንዑስ ግብ 5.1. የመንግስትና የህዝብ ፍትሐብሔራዊ ጥቅም ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- ☞ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የውል ምርመራ በማድረግ ምላሽ የመስጠት ሽፋኑን 90% ማድረስ፣
- ☞ ለቀረቡ የህግ ምክር ጥያቄዎች 100% ምላሽ መስጠት፣
- ☞ በፍትሀብሔር ጉዳዮች የመርታት ምጣኔን አሁን ካለበት 95.5% ማሳደግ፣
- ☞ በፍትሀብሔር ጉዳዮች የሚሰጥ ፍርድ የማስፈፀም ምጣኔን 54 % ማሳደግ፣
- ☞ በመንግስት ተቋማት መካከል የሚነሱ የፍታብሄር አለመግባባቶችን በድርድር የመፍታት አፈፃፀም ምጣኔን 9% ማድረስ፣
- ☞ የመንግስትና የህዝብ ፍትሐብሔራዊ ጥቅም ከማሳደግ በግልግል ጉዳዮች የመወሰን ምጣኔ 80%
- ☞ የመንግስትግዙፍ ፕሮጀክቶች የዉል አሰተዳደርና አፈፃጸም ስርዓት መመርመር የማማከርና የመከታተል ስርዐት መቅረፅና መተግበር፣
- ☞ የመንግስት ተቋማት የክርክር ተጋላጭነት ለመቀነስ የሚያስችል አሰራር መቅረፅ መተግበር፣

- የፍ/ብሄር ጉዳዮች የዉል ዝግጅት ምርመራ፣ ድርድርና ክርክር ጉዳዮች በመንግስት ተቋማትና በስለሚኖረዉ የስልጣን ክፍፍል መለያ መስፈርት ማዉጣትና መተግበር፣
- የመንግስት ተቋማት የህግ አማካሪዎች ሞያ ብቃት ማረጋገጫና ሰርቲፊኬሽን ስርአት መቅረፅና መተግበር
- በአለምአቀፍ የግልግል፣ ድርድርና ክርክር የሚደረግባቸዉ ጉዳዮች ክትትልና ዉክልና የሚሰጥበት ስርዐት መቅረፅ መተግበር፣
- አለም አቀፍ የግልግል ተቋማት በአገር ዉስጥ ማቋቋም የሚያስችል ስርዐት ማጥናት፣ አሰራርና አደረጃጀት ስርዐት መቅረፅ መተግበር፣
- የመክስር፣ የዉክልና ጋብቻ እና የጋብቻ ተቃዉሞ፣ ከጋብቻ እድሜ በፊት
- ለጋብቻ ፍቃድ የመስጠት ስርዐትና አደረጃጀት መቅረፅ መተግበር፣
- የወንጀል መቀጮና በዋስትና የተያዘ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ስለመደረጉ ክትትል የሚደረግበት ስርዐት መቅረፅ መተግበር፣
- የኦዲት ግኝቶችና መሰረት በማድረግ የመንግስት የሀብት ማስመለስ፣ ለግድፈቶቹ የግለሰብ ፍታብሄራዊ ተጠያቂነት ማረጋገጥ፣

**የሚጠበቅ ዉጤት፡- የመንግስትና የህዝብ ፍታብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቅ**

**ንዑስ ግብ 5.2. በህግ እና ፍትህ ጉዳዮች አለም አቀፍ ትብብርን ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ተግባራት፦**

- ከበይነ መንግስታት ድርጅቶች ጋር ሁለት የሕግ እና ፍትህ የትብብር ስምምነቶች መፈፀም፣
- ሁለት የሁለትዮሽና ባለብዙ ሀገራት ስምምነቶች መፈጸም፣ በአገር ዉስጥና በዉጪ ሀገር የሚገኝ ተጠርጣሪ/ተከሳሽ ተላልፎ የማስመጣትና አሳልፎ የመስጠት ምጣኔ 81 በመቶ ማድረስ፣
- በአገር ዉስጥና በዉጪ ሀገር የተሰጠ የፍርድ የማስፈፀም ምጣኔን 51 በመቶ ማድረስ፣
- በህግናፍትህ ጉዳዮችትኩረት የሚደረግባቸዉመስኮች፣ትብብር የሚደረግባቸዉ ሀገራትና አለምአቀፍ ተቋማት መለየት የሚያስችል ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀትና መተግበር፣
- በህግና ፍትህ ጉዳዮች አለም አቀፍ ትብብር ማስፈፀሚያ ስልትና ስርዐት መቅረፅና መተግበር፣
- በህግና ፍትህ ጉዳዮች አለም አቀፍ ትብብር እስካሁን የተደረጉት ስምምነቶች ያመጡት ፋይዳ ማጥናትና የማሻሻያ እርምጃ መዉሰድ፣
- በህግና ፍትህ ጉዳዮች አለም አቀፍ ትብብር የማዕከላዊ ባለስልጣንነትን አቋም ማጠናከርና የሁለትዮሽና አለምአቀፍ ስምምነቶች የግንኙነት መስመሩ በየሚያልፉበት ስርዐት መንደፍና መተግበር፣
- በህግና ፍትህ ጉዳዮች አለም አቀፍ ትብብር የመረጃ ማዕከል መቋቋምና የመረጃ ልዉዉጥ ስርዐቱን መዘርጋት፣

**የሚጠበቅ ዉጤት፡- ያደገ የአገሪቱን ጥቅም ያስጠበቀ በሕግ እና ፍትህ ጉዳዮች አለም አቀፍ ትብብር፣**

**ግብ 6. የሰብዓዊ መብት ማክበርና ማስከበር አፈፃፀምን ማሻሻል**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- ሶስተኛውን የሰብዓዊ መብት ድርጊት መርሐ-ግብር ማፅደቅና ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣
- በድርጊት መርሃ ግብሩ ይዘትና አፈፃጸም ሃገራዊ የግንዛቤ ንቅናቄ መፍጠር፣
- የሰብአዊ መብት ድርጊት መርሃ ግብር አፈፃፀም ክትትል አሰራር ስርዓትና አደረጃጀት ውጤታማነቱን ማረጋገጥ፣
- የሰብዓዊ መብት ድርጊት መርሃ-ግብር አፈፃፀም ሪፖርት ያቀረቡ አካላት ሽፋን ምጣኔን 90 በመቶ ማድረስ፣
- የተያዙና የተከሰሱ ሰዎች አያያዝና አጠባበቅ 100% ህግን የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- ለ20000 የተያዙና የተከሰሱ ሰዎች የሰብአዊ መብት አያያዝ ላይ ክትትል ማድረግ፣
- በተያዙና በተከሰሱ ሰዎች ላይ የሰብዓዊ መብት ጥሰት የፈፀሙ 100% ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን ወይም የተቀበለቻቸውን ዓለምአቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች አፈፃፀማቸውን መከታተል፣ ሪፖርትና ምላሽ መስጠት የሚያስችል ሀገራዊ ቋሚ ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፣
- የወንጀል ምርመራ ከሃይል ድርጊት በፀዳ መልኩ ስለሚከናወንበትና በቴክኖሎጂ ስለሚደገፍበት ስርአት መቅረፅና መተግበር፣

**የሚጠበቅ ዉጤት፡- ያደገ የሰብዐዊ መብት አጠባበቅ፡፡**

**ግብ 7. የህግ ተገዥነትን ማሳደግ**

**ንዑስ ግብ 7.1. የዜጎችን ንቃተ ህግ ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- ለዜጎች/ለሕብረተሰቡ/ ሊሰጡ የሚችሉ የንቃት ሕግ ትምህርቶችና የአሰጣጥ ዘዴዎች አመላካች የትንበያ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፣
- ቋሚ የገፅ ለገፅ ንቃተ ሕግ ማሳደግያ አደረጃጀቶች (የትምህርት ቤት ክለብ፣ ሲቪል ማህበራት፣ የሀይማኖት ተቋማት፣ አገልግሎት መስጫ ተቋማት፣ ችሎት፣ ዕድር፣ የኮሙኒቲ ፖሊሲንግ ማዕከላት ወዘተ) መለየትና ቋሚ የንቃተ ሕግ ትምህርት የሚሰጥበት ስርአት መቅረፅና መተግበር፣
- ቋሚ የኤሌክትሮኒክስና ህትመት ሚዲያ (የቴሌቪዥን፣ ሬድዮ፣ ጋዜጣ፣

መፅሄትና ማህበራዊ ሚድያ) የንቃተ ሕግ ማበልፀያ ዘዴዎች ማጥናትና መተግበር፣

- ☞ የተሰጡ የህግ ትምህርቶች ተደራሽነትና ያመጡት ፋይዳ ማጥናትና የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ፣
- ☞ በተለያዩ አስራ ሁለት (12) ርዕሶች የንቃተ ህግ ማስገንዘቢያ ሰነድ ማዘጋጀት፣
- ☞ ንቃተ ህግ ለመስጠት የሚችሉ 12 አደረጃጀቶችን መለየትና የንቃተ ሕግ እንዲሰጡ ማድረግ፣
- ☞ 10 የንቃተ ህግ ማስገንዘቢያ መድረኮች መፍጠርና ትምህርት መስጠት፣
- ☞ ለ2 ሚሊዮን ዜጎች የንቃተ ሕግ ትምህርት መስጠት፣
- ☞ የዜጎች ንቃተ ህግን ማሳደግያ ማስተማሪያ 2 ሞጁሎች መቅረፅና መተግበር፣
- ☞ በንቃተ ሕግ ትምህርት አሰጣጥና ውጤታማነት የህብረተሰቡን እርካታ 62% ማድረስ፣

**የሚጠበቅ ዉጤት፡- ያደገ የዜጎች ንቃተ ህግ፣**

**ንዑስ ግብ፡- 7.2. የፌዴራል ህጎች ተፈፃሚነት ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- ☞ የፌዴራል ህጎች ተፈፃሚነት ክትትል የተጠያቂነት ስርዐት መቅረፅና መትግበር፣
- ☞ ቅድሚያ ተሰጥቷቸዉ የሚታዩና ክትትል የሚደረግባቸው የፌዴራል ሕጎች የትንበያ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድና ትኩረት ሰጥቶ መተግበር፣
- ☞ የፌዴራል ህጎች ተፈፃሚነት ለማረጋጥ በ24 ሕጎች ላይ የአፈፃፀም ክትትል ማድረግ
- ☞ የምክረ ሃሳቦችን የአተገባበር ምጣኔን 90% ማድረስ፣
- ☞ ለ3 የአስተዳደር ፍትህ የሚሰጡ ተቋማት ያለባቸዉን ክፍተት በጥናት በመለየት ድጋፍ መስጠት
- ☞ ነባር የወጡና አዲስ የሚወጡ የአስተዳደር ሕጎችና የተቋማት ማቋቋሚ አዋጆች የዜጎች በመደበኛ ፍርድ ቤት ፍትሕ የመጠየቅና የመዳኘት መብት የማይጋፉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ጥናት ማካሄድና የማሻሻያ ምክረ ሃሳብ ማቅረብ፣
- ☞ የአስተዳደር ስነስርአት ህግ አተገባበር ክትትል ማድረግና በመንግስት ተቋማት የሚወጡ መመርያዎች መመርመር፣ መመዝገብና ታትመው ስለመውጣታቸው መከታተያ ስርአት መዘርጋትና መተግበር፣
- ☞ በአስተዳደር ተቋማት የተዘጋጁ መመሪያዎች 100% ማሰባሰብና ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፣

**የሚጠበቅ ዉጤት፡- ያደገ የፌዴራል ሕጎች አፈፃፀም፣**

## ግብ 8. የሕግ ጥናትና ማርቀቅ አፈፃፀም ማሻሻል

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- በበጀት ዓመቱ 12 አዲስ ሕግ የሚወጣላቸውና የሚሻሻሉ ህጎች የትንበያ ጥናት ማካሄድ፣
- 16 ረቂቅ ሕጎችን በማዘጋጀት ወይም ነባር ሕጎችን በማሻሻል ለሚመለከተው አካል ማቅረብ፣ ለእርማት የሚቀርቡ ሁሉንም ሕጎች በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ማረም፣
- ለሚቀርቡ የህግ ምክር ጥያቄዎች 100 ምላሽ መስጠት፣
- በኮድ ደረጃ መጠቃለል ያለባቸው ሕጎች መለየትና ሁለት ሕጎችን በኮድ መልክ ማዘጋጀትና ተደራሽ ማድረግ፣
- አስፈፃሚ የመንግስት አካላትና የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን ሕግ የማመንጨት፣ የማጥናትና የማርቀቅ የቅንጅታዊ አሰራር መቅረፅና መተግበር፣
- በሀገር ደረጃ እስከ 2012 ዓ.ም የወጡ ህጎች በማሰባሰብና 100% በማጠቃለል ለተጠቃሚዎች በቀላሉና በዘመናዊ መልክ ተደራሽ ማድረግ፣
- አንድ በተመረጠ ሕግ ላይ ፋይዳ ጥናት ማካሄድና የማሻሻያ ምክረ ኃሳብ ማቅረብ፣
- በክልሎች የሚቀርቡ የሕግ ረቂቅ ድጋፍ ጥያቄ ምላሽ መስጠት የሚያስችል አሰራር መቅረፅና መተግበር፤

**የሚጠበቅ ዉጤት፡- ያደገ የሕግ ጥናትና ማርቀቅ አፈፃፀም፣**

### ግብ 9፡ የአገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽነትን ማሳደግ

ንዑስ ግብ 9.1.በክልሎች ፍትህ ሚኒስቴርአገልግሎት ተደራሽነትን ማስፋት

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- ለክልሎች በዉክልና የተሰጡ ጉዳዮችን የሚመራበት አንድ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት መቅረፅና መተግበር፣
- በክልሎች የተልዕኮና አደረጃጀት ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል አንድ ጥናት ማካሄድና ጥናቱን መተግበር፣
- በዓመት አራት ጊዜ በሁሉም ክልሎች በውክልና የተሰጡ ጉዳዮች የክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**የሚጠበቅ ውጤት- ተደራሽ የሆነ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አገልግሎት፡፡**

**ንዑስ ግብ 9.2. የነፃ ህግ ድጋፍ አገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽነት ማሻሻል**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- የነፃ የህግድጋፍ አገልግሎት ስትራቴጂ በማፀደቅ የህግ ድጋፍመስጫ ስርዐት መዘርጋትና መተግበር፣
- የነፃ የህግ ድጋፍ የሚሰጡ አካላት ለማስተባበር የሚያስችል አሰራርና አደረጃጀት መቅረፅ፣
- የነፃ የህግ ድጋፍ ተጠቃሚ እርካታ ደረጃ መለኪያና አሰራር መቅረፅ በመተግበር፣ እርካታቸውን 85% ማድረስ፣
- 2000 የገንዘብ አቅም ለሌላቸው ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አረጋውያን እና ሌሎች ግለሰቦች የነጻ
- የህግ ድጋፍ አገልግሎት መስጠት፣
- አቅም ለሌላቸው ዜጎች (100%) ነፃ የሕግ አገልግሎት መስጠት
- ለ12 ለነጻ የህግ ድጋፍ መስጫ ማዕከላት ድጋፍ ማድረግ፣

**የሚጠበቅ ውጤት- አቅም ለሌለቸው ዜጎች የተሰጠ ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት፡፡**

**ግብ 10፡ የፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማሳደግ**

ንዑስ ግብ 10.1. የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀምን ማሳደግ

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- በተለዩ የትኩረት መስኮች አገልግሎትን በቴክኖሎጂ ተደራሽ ለማድረግ ጥናት ማካሄድና መተግበር (የጥብቅና አገልግሎትና ክፍያ፣ ቅሬታ አቀራረብና ምላሽ መስጠት፣ ወዘተ.)
- የተቋሙን አራት አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ (ኦንላይን) መስጠት መጀመር፣
- ለ2000 ተገልጋዮች ዘመናዊ ቴክኖሎጂ አገልግሎት በመጠቀም የኦንላይን አገልግሎት መስጠት፣
- የዜጎች ቻርተር ስታንዳረድ መሰረት ለ96.5% ተገልጋዮች በተቀመጠው መስፈርት አገልግሎቶች መስጠት፣
- የመረጃ መስጫ ስርአቱን ማዘመንና ተደራሽን ማድረግ፣
- መረጃ ፈልገው ወደ ተቋሙ ለሚመጡ 100% ተገልጋዮች በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት መረጃ መስጠት፣
- የቅሬታና አቤቱታ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ የአሰራር ማሻሻልና መተግበር፣ ለተገልጋይ ግልጽ የማድረግ፣
- የሚቀርቡ ቅሬታና አቤቱታዎች 77 % በተቀመጠው ስታንዳረድ መሰረት ምላሽ መስጠት፣
- ልዩ ትኩረት የሚፈልጉ ጉዳዮች የጥራትና ቅልጥፍናና የመለኪያ ስታንዳርድ መቅረፅና መተግበር፣
- የወንጀል ክስ መቋረጥ የሚመራበት የአሰራር ስርዐትና ማንዋል ማሻሻልና መተግበር፣

**የሚጠበቅ ውጤት- ያደገ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትና ቅልጥፍና ፡፡**

## ንዑስ ግብ 10.2. በፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግ

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- የግሉ ዘርፍ በፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ (በተናጠል ወይም ከመንግስት ጋር በሽርክና) ስለሚሳተፍበት መስክ ጥናት ማካሄድ፣
- በግሉ ዘርፍ እንዲሰጡ የተለዩ የፍትህ አገልግሎቶች ክትትል ስርዓት መዘርጋት፣
- ሁለት አገልግሎቶችን በመለየት በግሉ ዘርፍ እንዲሰጡ ማድረግ፣

**የሚጠበቅ ውጤት- ያደገ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ፡፡**

## ንዑስ ግብ 10.3. የጥብቅና አስተዳደር እና ክትትል ማሳደግ

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

የጥብቅና ፍቃድ ከመሰጠቱ በፊት የስነምግባር ማጣሪያ ስርዓት መዘረጋት፣ ስነ ምግባር ማጣራት፣

- ጠበቆች ስነ-ምግባር ዲሲፒሊን ዉሳኔ አሰጣጥ ቅልጥፍና ጥራት ማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር መቅረፅ፣
- ከጠበቆች ማህበራት ጋር በመተባበር የጠበቆች የሙያ ብቃት ማረጋገጫና ሰርቲፊኬሽን ስርዓት መቅረፅና መተግበር፣
- ጥብቅና ፍቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ከጠበቆች ካዉንስል በጋራ ለመስራት የሚያስችል ጥናት የአሰራር ስርዐት መቅረፅና መተግበር፣
- ለ1100 ጠበቆች የሙያና ስነ-ምግባር ስልጠና መስጠት፣
- ለ500 ጠበቆች በሚሰሩበት ቦታ ክትትል ማድረግ፣
- መስፈርቱም ላሟሉ ጠበቆች 100% የጥብቅና አገልግሎት መስጠት(አዲስ ፈቃድ፣ ዕድሳት፣ የጠበቃ ረዳት መመዝግብ፣ በአደራ ማስቀመጥ...)፣
- የጠበቆች ዲሲፕሊን ክሶች በተቀመጠው የጊዜ ስታንዳርድ መሠረት 62% ዉሳኔ ማሰጠት፣
- የጠበቆች የዲሲፕሊን ክስ ዉጤታማነት 76% ማረጋገጥ፣
- በጠበቆች አገልግሎት የደንበኞች እርካታ 81% ማድረስ፣

**የሚጠበቅ ውጤት- በጥብቅናው አገልግሎት አሰጣጥ ያደገ**

## የተገልጋዮች/ደንበኞች እርካታ፡፡

**ንዑስ ግብ 10.4. የወንጀል ምስክሮች፣ ጠቋሚዎች፣ ተጎጂዎች አገልግሎት አሰጣጥን ማሳደግ የሚከናወኑ ተግባራት፦**

- ጠቋሚዎች ምስክሮችና የወንጀል ተጎጂዎች ተሳትፎ፣ አያያዝና ጥበቃ አገልግሎት ለማሻሻል የሚረዳ አሰራር (የምስክሮችና የወንጀል ተጎጂዎች ቻርተር) መቅረፅና መተግበር፣
- ጠቋሚዎች ምስክሮችና የወንጀል ተጎጂዎች አያያዝና ጥበቃ አገልግሎት ተሳትፎ የሚኖራቸዉ አካላትን መለየትና በቅንጅት መስራት፣
- የወንጀል ተጎጂዎች የተሳተፉባቸው መዛግብት ምጣኔ 55% ማድረስ፤
- ጠቋሚና ምስክሮች ለጥቃት የሚያጋልጡ ክፍተቶችን የሚያርም አሰራር መዘርጋት፣ (ለምሳሌ የምስክሮች በጣቢያ፣ በዐ/ህግና በፍርድ ቤት መመላለስ ማስወገድ) ፣
- የተጎጅዎች እንክብካቤ ፈንድ ማቋቋም፣ የአጠቃቀም ስርአቱ መቅረፅና መተግበር፣
- በተጎጅዎች እንክብካቤ የሚሰሩ መንግስታዊና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተግባራትና አሰራር ማቀናጀት፣
- የጥበቃ ጥያቄ ለሚያቀርቡ ለ86% የጥበቃ ጠያቂዎች በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ምላሽ መስጠት፣
- አጠቃላይ በመዝገቦች ላይ ዉሳኔ በመስጠት ከማጥራት ምጣኔ አንፃር የጥበቃ ጥያቄ ካቀረቡት አቤቱታ አቅራቢዎች ዉስጥ ለ95% ምላሽ መስጠት
- ጥበቃ ለሚያስፈልጋቸው ጠቋሚና ምስክሮች 80% ጥበቃ ማድረግ፣
- የከለላ ዉሳኔዎችን የማይቀበሉ ወይም የሚያደናቅፉ ሰዎችን 100% በህግ እንዲጠየቁ ማድረግ
- የወንጀል ተጎጂዎችን የሚመለከት አጠቃላይ ሕግ ማውጣት
- ድጋፍና መልሶ ማቋቋም ለሚያስፈልጋቸው 81% ወንጀል ተጎጂዎች መደገፍና መልሶ ማቋቋም፣

**የሚጠበቅ ውጤት-ያደገ የወንጀል ምስክሮች፣ ጠቋሚዎች፣ ተጎጂዎች እርካታ፡፡**

### 10.5 የተጠሪ ተቀማትን አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማሳደግ

- ☞ በህግና ፍትሕ ጉዳዮች ላይ ወቅታዊ ጉዳዮች የጥናትና ምርምር ስራዎች ውጤታማነት ማግኘት □□□□ □□□□ □□□□□ □□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□
- ☞ □□□□□ የፍትህና የህግ ስልጠና ውጤታማነትን በማሻሻል የአመራሮችና የባለሙያዎችን አቅም ማጉልበት

- ☞ ለህግ ታራሚዎች የሚሰጠውን የማረም ማነፅ አገልግሎት ጥራትና ተደራሽነት □□□□
- ☞ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ህግን አክብረው እንዲንቀሳቀሱ ክትትልና ድጋፍ
- ☞ በማድረግ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እንቅስቃሴ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፡፡
- ☞ የፌዴራል ታክስ ይግባኝ የቅሬታ መዛግብት አከራክሮ ውሳኔ የመስጠት አቅም (100%) ማድረስ፣
- ☞ ሰነዶችን የማረጋገጥና የመመዝገብ አገልግሎት አሰጣጥ ጥራትና ቅልጥፍናን ማሻሻል

**የሚጠበቅ ውጤት- ያደገ የተገልጋዮች/ደንበኞች እርካታ፡፡**

## ግብ 11፡ በአገልግሎት አሰጣጥ አካታችነትን ማሳደግ

**የሚከናወኑ ተግባራት፦**

- ☞ ሴቶች ህፃናት እና ባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች የስራ ክፍሎች በእቅድ ተይዘው መተግበራቸውን ማረጋገጥ፣
- ☞ አራት የህፃናትና የሴቶች ፍትህና እንክብካቤ ማዕከላት ማቋቋም፣
- ☞ በህፃናት ላይ የሚፈፀሙና ከሴቶች ጾታዊ ጥቃት ጋር የተያያዙ ወንጀሎች፣ የህግ ተጠያቂነትን በተሟላ ለማረጋገጥ የሚያስችል ስርአት መዘርጋትና መተግበር፣
- ☞ በህፃናት ላይ የሚፈፀሙና ከሴቶች ጾታዊ ጥቃትጋር የተያያዙ ወንጀሎች ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት መዘርጋት፣
- ☞ የህፃናትና የሴቶች ፍትህና እንክብካቤ ማዕከላትና ቅብብሎሽ አሰራርና አደረጃጀት ስርዓት ውጤታማነት በመፈተሽ ማሻሻል፣ የወጣት ጥፋተኞች መገንቢያ ማዕከላት በአሰራር፣ በአደረጃጀትና በግብዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ማጠናከር፣
- ☞ ተቋሙ ያለበትን ማሕበራዊ ኃላፊነትና ግዴታ ለመወጣት የሚያስችሉ መስኮች መለየት፣ ፕሮግራም መቅረጽና መተግበር፣

**የሚጠበቅ ውጤት ተካተው የተፈፀመ የሴቶች፣ ሕፃናትና ባለብዙ ዘርፍ ተግባራት፡፡**

## ግብ 12. የትብብርና አጋርነትን ማሳደግ

**የሚከናወኑ ተግባራት፦**

- ከተጠሪ ተቋማት ጋር 4 የክትትልና ድጋፍ መድረክ ማከሄድ፣
- አንድ ጊዜ ለተጠሪ ተቋማት ሱፐርቪዥን ድጋፍ (ለሁሉም ተጠሪ ተቋማት) ማድረግ፣

- ለ 300 መርማሪዎችና ለፖሊስ አመራሮች ስልጠና መስጠት፣
- ለወንጀል ምርመራ አጋዥ የሚሆኑ 5 ግብአቶችን ሟሟላት፣
- ከ 2 ፍትህ አካላት ጋር በቅንጅት ስራዎች መስራት፣
- ከ 4 መንግስት ተቋማት ጋር የአጋርነት እና ትብብር መድረኮችን ማካሄድ
- ከ 4 ክልል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ጋር የአጋርነት እና ትብብር መድረኮችን ማካሄድ
- ከ 2 ማስረጃ ሰጪ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነዶችን መፈራረም፤
- ከ 4 ለጋሽና አጋር ድርጅቶች ጋር የመግባቢያ ሰነዶችን መፈራረም፤
- ከለጋሽ አካላት የቴክኒክና የብር 20,000,000 የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት፤
- የተጠሪ ተቋማት ቅንጅታዊ አሰራርና ቋሚ የክትትልና ድጋፍ ስርአት መዘርጋት፣
- ለፖሊስና ዐቃቤ ህግ ቅንጅታዊ አሰራር ማነቆዎች በማጥናት መፍታትና ቀጣይነት ያለው የተቀናጀ አሰራርና አደረጃጀት መተግበር፣
- ከክልል ያለው ቅንጅታዊ አሰራርና የጋራ መድረክ ቋሚ እንዲሆን አሰራር ስርዓት መዘርጋት፣
- በክልሎች የተቋሙን አገልግሎት ተደራሽነት ጉዳይ ማጥናት፣ በዉክልና የተሰጡ ጉዳዮችን ክትትልና ድጋፍ ስርአት መቅረፅና መተግበር፣
- ከባለድርሻና አጋር አካላት ጋር ያለዉ የትብብርና ቅንጅት አሰራር መስኮች መለየትና የመግባብያ ስምምነቶች መፈራረም፣
- የማስረጃ ጥራትና ተደራሽነት ለማስፋት የማስረጃ ሰጪ አካላት የትብብርና አጋርነት ስርአት መዘርጋት፣
- የአጋርና ለጋሽ አካላት የትብብር መስኮች ማዕቀፍ መዘጋጀትና መተግበር፣

**የሚጠበቅ ውጤት- ያደገ ትብብርና አጋርነት፡፡**

## ከመማማርና ዕድገት እይታ አንፃር

**ግብ 13 የስትራቴጂክ አመራር ብቃት ማሳደግ**

**ንዑስ ግብ 13.1. የስትራቴጂክ ዕቅድ አፈፃፀም ውጤታማነት ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት፦**

- ☞ ስትራቴጂያዊ ዕቅድን በሁሉም ዘርፍና የስራ ክፍል መሸንሸንና መተግበር፣
- ☞ የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም መከለስ፣

- ቋሚና የተሟላ የክትትልና ድጋፍ ስርአት በመቅረፅ መምራትና ማስፈፀም፣ ጥራት

- ባለው መረጃ ላይ የተመሰረተ የክትትልና ድጋፍ ስርአት መተግበር፣ በየደረጃው አራት ጊዜ የክትትልና ድጋፍ ማድረግ
- የስትራቴጂክ ዕቅድ አፈጻጸምን ወደ 85% ማሳደግ፣
- የተሞክሮ መቀመርያ ስርአት መቅረፅ፣ ሁለት ምርጥ ተሞክሮ መቀመረና ማስፋት፣
- የመልካም ተቋማዊ ባህል ግንባታ ማዕቀፍ መቅረፅና መተግበር፣
- እሴቶችና የስነምግባር ደንቦች ማስረጽና ማስፈጸም የሚያስችሉ ስልቶች መንደፍና መተግበር፣ ዘላቂ ተቋማዊ እሴት ለማዳበር የተስተካከለው ተቋማዊ ራእይና እሴቶች ማስረፅ፣
- ወጥና ቋሚ የሆነ የዐቃቤያነ ህግ የስራ አፈፃፀም ምዘናና የሽልማት ሥርዐት መቅረፅና መተግበር፣
- የተቋሙ የተሟላና ሳይንሳዊ የግለሰብና የተቋም የስራ አፈፃፀም መለኪያ በመስኩ በታወቁ ተቋማት ማስጠናትና መተግበር፣

**የሚጠበቅ ውጤት- ያደገ የስትራቴጂክ ዕቅድ አፈፃፀም ፡፡**

**ንዑስ ግብ፡- 13.2. የተተኪ አመራር ብቃት ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- የተተኪ አመራር መመልመያ መስፈርት መከለስ፣
- የመረጃ ቋት ማደራጀትና ተተኪ አመራር ማፍራት፣
- ሴቶችን ወደ አመራርነት ለማብቃት የሚያስችል ስርዐትመቅረፅና የተለዩና ያደጉ ተተኪ አመራሮች ብዛት 10 ማድረስ፤
- የአመራርነት ስልጠና ያገኙ ተተኪ አመራሮች ብዛት 10 ማድረስ፤
- የሴቶች አመራር ስብጥር ጥምረታ በሬሾ 36፡64 ማድረስ፤
- የሴቶችን የአመራርነት ተሳትፎ ከ 31% ወደ 40% ማሳደግ፣
- ቋሚ የተተኪ አመራር ማብቂያ ስርአት መቅረፅና 20 ተተኪ አመራር መመልመል፣ መለየትና ማሳደግ፣
- ለ80% አመራሮች የአመራርነት ስልጠና መስጠት፣
- የመካከለኛ አመራር ምልመላ፣ ማብቂያ፣ ምደባና የጥቅማጥም አሰጣጥ ስርዓት መቅረፅ መተግበር፣

**የሚጠበቅ ውጤት- ያደገ የተተኪ አመራር ፡፡**

**ንዑስ ግብ- 13.3. አሰራርና አደረጃጀትን ማሻሻል**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- የለውጥ መሳሪዎችን በሁሉም የስራ ክፍሎች ተግባራዊ ማድረግ፣
- የተሻሻሉ ወይም አዲስ የወጡ የአሰራር መመሪያዎች እና ማኑዋሎች ብዛት 2 ማድረስ፤
- የተሻሻሉ ወይም አዲስ የተዘረጉ አደረጃጀቶች ብዛት 1 ማድረስ፤
- 10 የአሰራረ መመሪያዎች እና ማኑዋሎች ማሻሻል፣
- አዳዲስና ዘመናዊ የለውጥ መሳሪያዎች አገር አቀፍና አለምአቅፍ ልምዶች በመቀመር ከተቋሙ ተልእኮ አንፃር መከለስና መተግበር፣
- የካይዘን አሰራር ተግባራዊ የሚሆንባቸው የስራ መስኮች (መዝገብና ሪከርድ አስተዳደር፣ ንብረት አስተዳደርና የቢሮ አስተዳደርና ሌሎች) በጥናት መለየትና መተግበር፣
- የተጠናው ተቋማዊ መዋቅርና አደረጃጀት መተግበር ውጤታማ እንዲሆን ክትትል ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣
- የሕግና ፍትሕ አማካሪ ምክር ቤት አሰራር መፈተሽና የህግና ፍትህ ማሻሻያዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ድጋፍ ማድረግ

**የሚጠበቅ ውጤት-ውጤታማ አሰራርና አደረጃጀት፡፡**

**ንዑስ ግብ፡- 13.4.የሰው ሃብት የማስፈፀም አቅምን ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- ሰው ሐብት ልማትና አስተዳደር ስትራቴጂ መቅረጽና መተግበር፣
- ሞያዊ ብቃትና መልካም ስነ-ምግባር ያለው ባለሙያ ማሰማራት የሚያስችል የሰው ሃብት ምልመላ ስርአት መቅረጽና መተግበር፣
- የሰው ሃብት ስምሪትና ምርታማነት ማሻሻያ ስርዓት መቅረፅና መተግበር፣
- በተጠናው ተቋማዊ መዋቅርና አደረጃጀት የአመራርና የፈፃሚ ድልድል ማካሄድ፣
- ዘመናዊ የሠዉ ሀይል መረጃ አያያዝና ስርጭት ስርዓት መቅረጽና መተግበር፣
- የሠዉ ሀይሉ የጥናትና ምርምር ክህሎቱን ለማሳደግ የተሟላና ደረጃዉን የጠበቀ ቤተ መፃሕፍት ማደራጀት፣
- በ2 ዘርፍና በ4 ጽ/ቤት መለስተኛ ቤተ መፃሕፍት ማደራጀት፣
- የአገልጋይነት መንፈስ፣ የስነ-ምግባርና የሙያ ክብር ለማሻሻል ለ85%) ሰራተኞች የሙያ ስነ-ምግባር ስልጠና መስጠት፣ የስነ-ምግባር ጥሰት መቀነስ፣
- ዐቃቤ ሕግ ስነ-ምግባር ደንብና ሌሎች የአሰራር ስርአቶች ተግባራዊ

መደረጋቸውን መከታተል፣ ተጠያቂነት ማረጋገጥ፣

- የስራ አፈፃፀም ውጤት በመረጃ ላይ የተመሰረተ፣ የተቋሙን ውጤት ያገናዘበና እውነተኛ እንዲሆን መከታተያ ስርአት መዘርጋት፣
- በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ለ70% ሰራተኞች እና መካከለኛ አመራሮች ሙያዊ ሥልጠና መሰጠት፣
- የአቅም ግንባታ ስልጠና የሚያገኙ ሰራተኞች ብዛት 920 ማድረስ፤
- ሁሉም አዲስ የሚመለመሉ ዐቃብነ ሕግ ተግባር ተኮርና ሞያ ብቃት ማረጋጫ የቅድመ ስራ ስልጠና እንዲወስዱ ማድረግ፣
- የተቋሙ አዲስ ሰራተኞች ስለተቋሙ ተልዕኮና አሰራር ሁኔታ የማስተዋወቂያ ፕሮግራም መንደፍና መተግበር፣
- ከሕግ ትምህርት ቤቶች በትብብር ለመስራት የሚስችል ስምምነት መፈጸምና መተግበር፣
- የሰራተኞችን የሚስብ፣ የሚያቆይ፣ የሚያበረታታና ፍልሰትን የሚቀንስ የማትጊያ ስርዐት በመቅረፅ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ሰራተኛው ለሙያውና ለተቋም ያለዉ ተቆርቋሪነትና ፍቅር፣ መሰጠትና እርካታን ማሳደግ የሚያስችል ስርአት መቅረጽና መተግበር፣
- የስራ ሁኔታና አካባቢ ምቹነት ሁኔታ ማጥናትና ውጤቱን መተግበር፣
- የሰዉ ሀብት የግል አቅም መገንቢያ ስርዐት መቅረጽና መተግበር፣
- የሰራተኞች የአለባበስ ስርዐት(Dressing code) መቅረጽና መተግበር፣
- የግለሰብ የሥራ አፈፃፀም ዉጤት መመዘኛ ስርዐት ማሻሻልና መተግበር፣
- ሰው ሃብት እርካታና የመሰጠት ሁኔታ መለኪያ ስርአት መቅረጽና መተግበር፣ የሰራተኛ እርካታ የሰራተኛውን እርካታ 76% እና መሰጠት 71% ማድረስ፣
- የሰራተኞች ፍልሰት 7.6% መቀነስ፣

**የሚጠበቅ ውጤት፡- ያደገ የማስፈፀም አቅም**

**ግብ 14. የመረጃ አያያዝ፣ አጠቃቀምንና ስርጭትን ማሻሻል**

**የሚከናወኑ ንዑስ ተግባራት፡-**

- ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ተግባራዊ 91% የስራ ክፍሎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማድረግ፣
- በበጀት ዓመቱ የተከፈቱ መዛግብት 100% ወደ ዲጂታል እንዲቀየሩ ማድረግ
- ወደ ዲጂታል የተቀየሩ መዛግብት እና ሰነዶች ብዛት 40000 ማድረስ፤
- የተዘረጉ ዘመናዊ የመረጃ መያዣና ማሰራጫ ስልት ብዛት3 ማድረስ፤
- የሪከርድና መዛግብት አስተዳደርና ቅብብል ማንዋልና አሰራር መቅረፅና መተግበር፣
- የተማከለ የሪከርድና መዛግብት አደረጃጀትና አያያዝ ማደራጀትና

መተግበር፣
- ☞ የመረጃዎች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የተሟላ ስርዓት መቅረፅ፣

**የሚጠበቅ ውጤት ያደገ የመረጃ እቀባና ልውውጥ ፡፡**

**ግብ 15. ዘመናዊ አሰራርና የቴክኖልጂ አጠቃቀምን ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- ለ750 ፈጻሚዎች በዘመናዊ የቴክኖልጂ አጠቃቀም ላይ ስልጠና መስጠት፣
- ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተዘረጋላቸው 91% የስራ ክፍሎች በዘመናዊ የቴክኖልጂ የታገዘ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣
- 6 አገልግሎቶችን ከወረቀት ነጻ በሆነ መልኩ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ኦንላይን እንዲሰጡ ማድረግ፣ ሁለት የቴክኖልጂ መሰረተ ልማት መዘርጋት፣
- የሁለት የሶፍት ዌርና ዳታ ቤዝ ማልማት ስራን ማከናወን፣
- የኢንፎርሜሽን ቴክኖልጂ መሰረተ ልማቶችን ደህንነት 100% የመጠበቅ ስራን ማከናወን፣
- ዘመናዊ አሰራርን፣ አጠቃቀም ባህልን ለማሻሻል የሚያስችል ፕሮግራም መተግበር፣
- የተቋሙን ድረ-ገፅ (ዌብ ሳይት) በሙሉ አቅሙ ጥቅም ላይ ማዋል፣
- በተቋም ውስጥ የኢንተርኔት አጠቃቀም ፖሊሲ መቅረፅና መተግበር፣
- የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን አይነትና ብዛት የመለየት፣ የመመዝገብና የማስተዳደር ስርዐት መቅረፅና መተግበር፣
- የዉጤት ተኮር የመለኪያ ስርዐትን አዉቶሜት ማድረግና ተግበር

**የሚጠበቅ ውጤት፡- ያደገ ዘመናዊ አሰራርና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም**

**ግብ 16. የተግባቦትና ገፅታ ግንባታ ስትራቴጂ አፈፃፀም ውጤታማነትን ማሻሻል**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- ☞ የተግባቦትና ገፅታ ግንባታ ስትራቴጂ መቅረፅና መተግበር፣
- ☞ የተቋም መረጃና መግለጫ አሰጣጥ ፖሊሲ መቅረፅና መተግበር፣
- ☞ የሰው ሃይል የለውጥ ባለቤት እንዲሆን የውስጥ የተግባቦት መተግበር፣ ለ86% ሰራተኞች የለውጥ ግንዛቤ መረጃ መስጠት፣
- ☞ ቋሚ የኤሌክትሮኒክስና ሕትመት ሚዲያ (የቴሌቪዥን፣ ሬድዮ፣ ጋዜጣ፣ መፅሄትና ማህበራዊ ሚድያ) የተግባቦትና ገፅታ ግንባታ ማበልፀያ ዘዴዎች ማጥናትና መተግበር፣ ከ4 ሚዲያዎች ጋር ቋሚ ትስስር ማድረግ፣
- ☞ የሚዲያና መረጃ ቅብብሎሽን ተደራሽነት ስርአት መቅረጽና መተግበር፣

- የህብረተሰቡን መረጃ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ ቋሚ አሰራር መቅረፅና መተግበር፣
- ነፃ የጥቆማና የህግ ጥያቄ አቀባበልና ግብረ መልስ ስርዓቱን ፈትሾ ማሻሻል፣
- በመደበኛነት በወር ሁለት ጊዜ መረጃዎችን ለሚዲያ ተደራሽ ማድርግ፣
- ለቀረቡ ጥቆማዎችና ጥያቄዎች 91% በስታንዳርዱ መሰረት ምላሽ መስጠት፣

**የሚጠበቅ ውጤት፣-** **ያደገ ተግባቦትና የተሻሻለ ገጽታ፡፡**

# ክፍል አራት

## 4.1. የተቋሙ የ2014 በጀት ዓመት ፕሮጀክቶች እና ለዓመቱ የተመደበ በጀት

ተቋሙ የተሰጠውን ዘርፈ ብዙ ኃላፊነቶች መንግስት በሚበጅትለት ውስን ሐብት ሙሉ በሙሉ ማሳካት ስለማይቻል ችግር ፈቺ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅና ሀብት በማፈላለግ የተቋሙን ሥራ ያስፈልጋል፡፡

### 4.1.1. የተቀረፁ አዲስና ነባር ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች

በመሆኑም ባለፈው በጀት ዓመት በእቅድ ተይዘው የነበሩ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በመገምገም ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንዲፈፀሙ ከማስቻል ባለፈ በበጀት ዓመቱ ተቋማዊ ፋይዳ ያላቸውና ከተለዩትን ጥቅል አሥራ ስድስት ስትራቴጂክ ግቦች ሊያሳኩ የሚችሉ አስራ አራት ፕሮጀክቶች ተለይተዋል፡፡

እነዚህም፡-

| ተ.ቁ | የተቀረፁ አዲስና ነባር ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች |
|---|---|
| 1. | የስትራተጂያዊና ተተኪ አመራር ማበልፀግያ ፕሮጀክት |
| 2. | የወንጀል መከላከል ስትራተጂ፣ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲና የወንጀል ስነስርአትና ማስረጃ ሕግ ማስፈፀምያ ፕሮጀክት |
| 3. | የአገልግሎት አሰጣጥ እርካታና አመኔታ ማሳደግያ ፕሮጀክት |
| 4. | የግል ዘርፉን በፍትህ ስርዓቱ የማሳተፍ ፕሮግራም |
| 5. | የወንጀል ጠቋሚዎች፣ ምስክሮችና የወንጀል ተጎጂዎች አያያዝና አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ፕሮጀክት (No Witness No Justice Project) |
| 6. | የጠበቆች አስተዳደርና የነፃሕግ ድጋፍ ስትራተጂ ማስተግበርያ ፕሮጀክት |
| 7. | የሕግና ፍትሕ ማሻሻያ ፕሮግራም |

| | |
|---|---|
| 8. | የንቃተ ህግ ትምህርትና የሕ/ሰብ ተሳትፎ ማበልፀግያ ፕሮጀክት |
| 9. | የህገወጥ የሰዎች ዝውውርና የፍልሰት ፖሊሲ ማስተግበርያ ፕሮጀክት |
| 10. | የዘመናዊ ክቴኖሎጂ መሰረተ ልማት ማስፋፍያ ፐሮጀክት |
| 11. | ዘመናዊ የመረጃ ፣የማህደርና ፋይል አያያዝና አስተዳደር ማጠናከርያና የካይዘን ማስተግበርያ ፐሮጀክት |
| 12. | የህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት፣ |
| 13. | የሃብት ማመንጫና ማስፋፊያ ፕሮግራም |
| 14. | የመጀመርያ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት መርሃ ግብር ፕሮጀክት |

እነዚህ ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ ሊያመጡ የምችሉት ፋይዳና በፕሮጀክቱ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት እንዲሁም የፕሮጀክቱ የአፈፃጸም ደረጃና ፕሮጀክቱን በባለቤትነት የሚመራው ሥራ ክፍልም ተለይቶ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 4.1.2. በትግበራ ላይ ያ ሉ ፕሮጀክቶች

| ተ•ቁ | የፕሮጀክቱ መጠሪያ(Project Identification) | በፕሮጀክቱ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት Project Main Activities | ፕሮጀክቱ የሚጠናቀቅበት Duration of the Project | የፕሮጀክቱ አፈፃጸም ደረጃ በ2013 የተደረሰበት Project Performance | በ2014 የሚደረስበት Project Achievement | ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልግ በጀት Project Cost in Birr | የፕሮጀክቱ ክትትል ባለቤት Project Implementers | ፕሮጀክቱ ሲሣናቀቅ ሊያመጣ የመሚችለው ፋይዳ Project Impact |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ህጎችን የማሰባሰብና የማጠቃለል ፕሮጀክት | ከ1934-2012 የተሰባሰቡ የእንግሊዝኛ ቅጂ ህጎችን ማሰባሰብና ማሳተም | ቀጣይነት ያለው | የአማርኛ ቅጂ ከ1934-2011 ያሉ ህጎችን የማሰባሰብ ሥራ ተጠናቋል | በ2014 ይቀጥላል | --- | ህግ ጥናት | ህጎችን በአንድ ላይ በማሰባሰብ ለህብረተሰቡ በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ ያስችላል፡፡ |
| 2 | የብሔራዊ ነፃ የህግ ድጋፍ ስትራቴጂክ ኘሮጀክት | ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት መስጠት፣ ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎትን ማስተባበር፣ | ቋሚ ነው | ስትራቴጂው ተዘጋጅቷል፡፡ | በ2014 ይቀጥላል | --- | ህግ ጥናት | የህግ አገልግሎትን ተደራሽነት በማስፋት ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡ |
| 3 | አምስተርዳም የትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት | የማስተርስ ትምህርት ለዐቃቤያነ ህግ መስጠት አጫጭርና ረጃጅም ስልጠናዎች መስጠት | 2012 | በ2011 አዲስ ተጀምሯል | በ2014 ይጠናቀቃል | --- | ህግ ጥናት | የአቃቤያነ ህግን እውቀትና ክህሎት ለማሳደግ ያግዛል በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ስፔሻላይዝ ያደረገ ባለሙያዎችን ለማፍራት ያስችላል |
| 4 | የዴን ማርክ ሥልጠና ፕሮጀክት | የንቃተ ህግ ትምህርት መስጠት ለፌዴራልና ክልል ፍትህ አካላት ስልጠና መስጠት፣ | ቀጣይነት ያለው | ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል | በ2014 ይቀጥላል | --- | ህግ ጥናት | ህገወጥ ገንዘብን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀልን ለመከላከል ያስችላል |
| 5 | በህጻናት ላይ የሚፈፀም ጥቃት መከላከል ፕሮጀክት | (5) የተለያዩ ጥናቶችን ማስጠናት | - | ተጀምሯል | በ2014 ይቀጥላል | --- | ሴቶችና ህጻናት | |
| 6 | ያለእድሜ ጋብቻና ግርዛት (Violence agenist children (VAC) ending child marrage & FGM project | ያለእድሜ ጋብቻና ግርዛት በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና መከላከል ስራዎች መስራት፣ የሀገር አቀፍ መረጃዎች አያያዝ ላይ ጥናት ማካሄድ | - | ተጀምሯል | በ2014 ይቀጥላል | --- | ሴቶችና ህጻናት | በህጻናት ጥቃትና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ማስወገድ ዙሪያ ሀገር አቀፍ ጥናቶችንና ወጥ አሠራሮችን ለመዘርጋት ያስችላል፡፡ |
| | የሪከርድ፣ ማህደርና ፋይል | ዘመናዊ የሪከርድ አያያዝና መረጃ ስርዓት | አልተጀመረም | አልተጀመረም | በ2014 | --- | | ዘመናዊ የመዛግብት |

| ተ•ቁ | የፕሮጀክቱ መጠሪያ(Project Identification) | በፕሮጀክቱ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት Project Main Activities | ፕሮጀክቱ የሚጠናቀቅበት Duration of the Project | የፕሮጀክቱ አፈፃጸም ደረጃ |  | ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልግ በጀት Project Cost in Birr | የፕሮጀክቱ ክትትል ባለቤት Project Implementers | ፕሮጀክቱ ሲሠናቀቅ ሊያመጣ የመሚችለው ፋይዳ Project Impact |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
|  |  |  |  | በ2013 የተደረሰበት Project Performance | በ2014 የሚደረስበት Project Achievement |  |  |  |
|  | ማሻሽያ ፕሮጀክት | መዘርጋት |  |  | የሚጀመር |  |  | አስተዳደርና የመረጃ ስርዓት ለመዘርጋት ያስችላል |
| 7 | የፍትህ አካላት ህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት |  |  |  |  |  |  |  |
| 7.1 | ነባር ግንባታ ፕሮጀክት |  |  |  |  |  |  |  |
| 7.2 | አዲስ ከተማ የፍትህ አካላት ህንጻ ግንባታ | ግንባታ ማካሄድ | 2012 | 96.13% | 100% | -- | የዕቅድዝ/ፕሮጀክት ክትትል | ለዜጎች ፍትህን አገልግሎት አሰጣትን ምቹና ተደራሽ ማድረግ ያስችላል፡፡ |
| 7.3 | አራዳ የፍትህ አካላት ህንጻ ግንባታ | ግንባታ ማካሄድ | 2012 | 99% | 100% | -- | ፕሮጀክት ክትትል |  |
| 7.4. | ኮልፌ ቀራኒዮ የፍትህ አካላት ህንጻ ግንባታ | ግንባታ ማካሄድ | 2012 | 9.37% | 50% | -- | ፕሮጀክት ክትትል |  |
| 7.5 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ የፍትህ አካላት ህንጻ ግንባታ | ግንባታ ማካሄድ | 2012 | 87 | 100 | -- | ፕሮጀክት ክትትል |  |
| 7.6 | የዋናው መ/ቤት ህንጻ ዕድሳት/ግንበታ/ | ግንባታ ማካሄድ | 2013 | 57% | 100% |  | ፕሮጀክት ክትትል |  |
| 7.7 | ብሔራዊ የተቀናጀ የፍትህ ሥርዓት መረጃ ፕሮጀክት (NIJIS) | የማልማት ሥራ | 2012 | 5% | 45% | -- | ICT | ብሔራዊ ዘማነዊ የተቀናጀ የፍትህ መረጃ ስዓት እንዲኖር ያስችላል |

### 4.1.3. የ2014 እቅድ ማስፈፀሚያ በጀት

የየፕሮግራም በጀት አሠራር ሥርዓትን በመከተል ውጤትን ለመለካት ተጠያቂነትን ለማስፈን ተቋማዊ ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ እቅድን ከበጀት፣ በጀትን ከውጤት ጋር ለማስተሳሰር ለማቀናጀት ያመች ዘንድ ከ (2014-2015) የሁለት ዓመት ተቋማዊ የፕሮግራም በጀት ስትራቴጂክ እቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ከተዘጋጀው የሁለት ዓመት የፕሮግራም እቅድ የ2014 በጀት ዓመት በተቋም ደረጃ ለታቀዱ ዋና ዋና ስትራቴጂካዊ ግቦችና ተግባራት ማስፈፀሚያ ከፌዴራል መንግስት ለየታቀደ የመደበኛና የካፒታል በጀት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

| | ለ2014 በጀት ዓመት ከበጀት ስሚ በኋላ የተጠየቀ በጀትና የጸደቀ | | |
|---|---|---|---|
| ፕሮግራም በጀት /የጪ ዓይነት | ለ2014 የተጠየቀ | ለ2014 የጸደቀ | የፋይናንስ ምንጭ |
| ጠቅላላ የፕሮግራሞች ድምር | 852,205,626.00 | 750,757,619 | ከመንግስት ግምጃ በት |
| የመደበኛ ወጪ | 626,855,626.00 | 525,407,619 | ከመንግስት ግምጃ በት |
| የካፒታል ወጪ | 225,350,000 | 225,350,000 | ከመንግስት ግምጃ በት |
| ፕሮግራም- 1- (አመራርና ድጋፍ) | 389,671,179.00 | 359,827,628 | ከመንግስት ግምጃ በት |
| መደበኛ ወጪ | 164,321,179.00 | 134,477,628 | ከመንግስት ግምጃ በት |
| የካፒታል ወጪ | 225,350,000 | 225,350,000 | ከመንግስት ግምጃ በት |
| የፕሮግራም -2 -( የክርክር ጉዳዮች) | 391,595,462.00 | 350,934,533 | ከመንግስት ግምጃ በት |
| መደበኛ ወጪ | 391,595,462.00 | 350,934,533 | ከመንግስት ግምጃ በት |
| የካፒታል ወጪ | 0.00 | 0.00 | ከመንግስት ግምጃ በት |
| የፕሮግራም -3- የህግና አስተዳደር ጉዳዮች | 70,938,985.00 | 39,995,458 | ከመንግስት ግምጃ በት |
| መደበኛ ወጪ | 70,938,985.00 | 39,995,458 | ከመንግስት ግምጃ በት |
| የካፒታል ወጪ | 0.00 | 0.00 | ከመንግስት ግምጃ በት |

2014 በጀት ዓመት የፊዚካል ተግባራት ማስፈጸሚያ በጀት መርሃ ግብር

| ተ.ቁ | መደበኛ በጀት | የዓመቱ የማስፈጸሚያ በጀት | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ደመወዝ | 335,798,334 | 73,556,304 | 89,836,761 | 89,836,761 | 82,568,508 |
| 2 | ሥራ ማስኬጃ | 189,609,258 | 91,864,756 | 32,252,991 | 31,858,4999 | 33,633,012 |
| 3 | ካፒታል | 225,350,000 | 67,605,000 | 67,605,0000 | 45,070,000 | 45,070,000 |
| ጠቅላላ ድምር | | 750,757,619 | 233,026,060 | 189,694,752 | 166,765,260 | 161,271,520 |

# ክፍል አምስት

## 5.1. እስትራቴጂያዊ የአፈፃፀም አቅጣጫዎች እና ክትትልና ድጋፍ ስርዓት

በበጀት ዓመቱ የታቀዱ ግቦችና ስትራቴጂያዊ ተግባራትን ውጤታማ ለማድረግ የማስፈፀሚያ አቅጣጫዎችንና የተጠናከረ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ በዚሁ መሠረት በየደረጃው ያለው አመራር እስከ ፈፃሚው ድረስ በክትትልና ድጋፍ ሥርዓቱ ዋና ተሣታፊ በመሆኑና የባለቤትነት ድርሻ መወጣት የሚገባ ሆኖ አተገባበሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 5.1.1. ስትራቴጂያዊ የአፈፃፀም አቅጣጫዎች

- ወንጀል መከላከልን፣ የህግ የበላይነትን በሚያረጋግጥና የሰብዓዊ መብት ጥበቃን ዋና የትኩረት መስክ በማድረግ፣
- የለውጥ አመራርና ቀጣይነት በሚያረጋግጥ መልኩ በመምራት፣
- ተቋማዊና ሙያዊ ባህልን በሚገነባ ዘላቂ ተቋማዊ አሰራር በመከተል፣
- በሂደቱ የሰው ሃይሉን ሙያዊ ብቃትና ሙያዊ ስነምግባር ማሻሻልን ማዕከል በማድረግ፣
- ህብረተሰቡንና ሲቪል ማህብረተሰቡን አሳታፊ የሆነ አሰራር በመከተል፣

- የግሉን ዘርፍ የሚያሳትፍ አሰራር በመከተል፣
- በመረጃ ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት በመዘርጋት፣
- ልምድ ልውውጥን፣ ተሞክሮ በመቀመር (scale up) እና በማስፋት፣
- የሃብት ምንጮችን በማስፋት፣ የዕቅድ አፈፃፀምና የሃብት አጠቃቀምን ቅደም ተከተል በማውጣት፣
- የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ክትትል ስርዓት በመዘርጋት፣
- ዘመናዊ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም በማጎልበት፣ እና የትብብርና አጋርነትን አሠራር በማጎልበት፡፡

## 5.2. የክትትልና ድጋፍ ስርዓት

በስትራተጂያዊ ዕቅዱ የተካተቱ ተግባራትን በአግባቡ ለማስፈፀም የተቋሙ የስራ አካላት በጋራና በተናጠል የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጡ መሆኑን ለመከታተልና ተገቢውን ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው።

### 5.2.1. የበላይ አመራሩ ኃላፊነት

የበላይ አመራሩ በየጊዜው የዕቅዱን አተገባበር የመምራት፣ የመቆጣጠር፣ የመገምገም እና ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት ይኖረዋል። በዚህ መሰረትም የሚከተሉን ያከናውናል፤

- ዕቅዱን በየስራ ክፍሉ በመሸንሸን (ካስኬዲንግ) መተግበር፣
- የዕቅዱን አፈፃፀም ለመከታተል፣ ለመገምገምና ሪፖርት ግብረ መልስ ለመስጠት የመረጃ አያያዝ ስርዓት መገንባት፣
- መረጃዎች በወቅቱ፣ በጥራትና በተሟላ ሁኔታ እንዲሰበሰቡና ተተንትነው ለሚወሰዱ የውሳኔ እርምጃዎች፣ አቅጣጫዎች ግብዓት እንዲሆኑ ማድረግ፣
- የየሩብ ዓመቱን የተጠቃለለ ሪፖርት ማዘጋጀትና ለቀጣይ የዕቅዱ አፈፃፀም በግብአትነት መጠቀም፣
- የተጠናከረ የሱፐርቪዥን ስርዓት መቅረፅና መተግበር፣

- የዘርፍ፣ የስራ ክፍል፣ የአመራርና የፈፃሚ ጠንካራ የምዘና ስርዓት መቅረፅና መተግበር፣
- በየበጀት አመቱ ማጠቃለያ እውቅናና ማበራታቻ ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ፣
- በዕቅድ፣ ፕሮጀክትና በጀት ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይይሬክሬት አማካኝነት ተጠናቅሮ የሚቀርብለትን የተቋም አፈጻጸም ሪፖርቶችን በመገምገም፣ ተገቢ አቅጣጫ መስጠት፣
- ዘርፎች ያከናወኗቸው ተግባራት የሚገመገምበት መድረክ በዓመት 4 ጊዜ እንዲዘጋጅ ማድረግ፤
- ማሕበረሰቡ፣ የብዙኃንና የሙያ ማህበራት፣ የሲቪክ ማህበራት እና አጋር ድርጅቶች በዕቅዱ አተገባበር የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ድጋፍ መስጠት፤
- እንደ አስፈላጊነቱ ዕቅዱን እንዲሻሻልና እንዲከለስ ያደርጋል፤

## 5.2.2. የዘርፎች ኃላፊነት

- በስራቸው ያሉት የስራ ክፍሎች የተሰጣቸውን ተግባራት በእቅዳቸው መካተታቸውን ማረጋገጥ፣
